
# ማዕዶት





ጥር ፲፱፻፹፫ ዓ/ም

ቍጥር ፴፫

www.ethiopianorthodox.org

ዘጸአት ሪታና ቤተሰቡ
የግል ቤተ መጻሕፍት

# ማዕዶት

ጥር ፲፱፻፹፫ ዓ/ም

ቍጥር ፴፫

www.ethiopianorthodox.org

# ማ ዕ ዶ ት

«ማዕዶት የሚለው ቃል መሠረታዊ አመጣጡ ከልሳነ ግዕዝ ሲሆን ትርጓሜው መሸጋገሪያ ማለት ነው ይህ መጽሔት በዚህ በሽግግር ወቅት በተሐድሶ ላይ የምትገኘውን የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን እምነትዋንና ሥርዓቷን ወቅታዊ እንቅስቃሴዋን ዜናዋንና ታሪካዊ ልዕልናዋን ሁሉ የሚገልጽ ስለሆነ «ማዕዶት» ተብሉ ተሰየመ ፡

ዋና አዘጋጅ

ሊ/_ትጉሃን ገ/ ክርስቶስ ኃ/ ማርያም

የስልክ ቍጥር 11 26 63

ወይም 55 00 99 ×28

ፓ/ ሣ/ ቍ/ 1283

አዲስ አበባ

ማ ው ጫ


| ተ.ራ ቍ. | አርእስት | ገጽ |
|---|---|---|
| ፩ | ርእሰ አንቀጽ | ፭ |
| ፪ | የቅዱስ ፓትርያርክ ቃለ ምዕዳን | ፯ |
| ፫ | ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ መርቆሬዎስ ስድስት ኤጲስ ቆጶሳት በአንብሮተ እድ ሾሙ | ፱ |
| ፬ | የቡልቡላ ፈለገ ሕይወት አቡነ ገ/መንፈስ ቅዱስ ቤ/ክ/ቅዳሴ ቤት | ፲፩ |
| ፭ | ወደ ጥምቀተ ባሕር እንሂድ | ፲፫ |
| ፮ | በሦስተኛው ቀን በቃና ሠርግ ነበር | ፲፭ |
| ፯ | ሰማዕቱ ቅ/ቂርቆስና እናቱ | ፲፯ |
| ፰ | ሞት በጥር በነሐሴ መቃብር | ፲፰ |
| ፱ | ዮሐንስ ወንጌላዊ | ፲፱ |
| ፲ | በጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የሚጎበኝ ቤት | ፳ |
| ፲፩ | የሕይወት መንገድ እኔ ነኝ | ፳፩ |
| ፲፪ | የአንደራቻ ገዳምና ተሐድሶው | ፳፬ |
| ፲፫ | የመምህር ኪሮስ አጭር የሕይወት ታሪክ | ፳፱ |
| ፲፬ | የአክሱም ሐውልት ይመስከሩ | ፴ |
| ፲፭ | የአባ ገ/መስቀል ተ/ሕይወት | ፴፫ |
| ፲፮ | ሐኪሙ ለአብያተ ክርስቲያናት ርዳታ አደረጉ | ፴፭ |
| ፲፯ | የምሥራቅ ሐዋርያ | ፴፯ |




ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ መርቆሬዎስ ፓትርያርክ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ

www.ethiopianorthodox.org

## ድርገታተ መላእክት በከዋክብት ዓለም

በግዕዝ ቋንቋችን መልአክ መልእክተኛ መላእክት መልእክተኞች ማለት ነው ። ይህ ቃል ለሁሉም የሚስማማ (የሚያገለግል)ቢሆንም በአማርኛ ቋንቋችን የተለመደው መልአክ ወይም መላእክት የሚ ለው ቃል የእግዚአብሔር መልእክተኛ ( መልእክተኞች ) ወደሚለው ያዘነብላል ። መላእክት ተፈጥሮአቸው ፣ ደረጃቸው ፣ አገልግሎታቸው እንዴት እንደሆነ በቅዱሳት መጻሕፍት ተጽፎአል ። ለምሳሌ የመላእክት ተፈጥሮ ረቂቅ ነው ። ሥጋና አጥንት የላቸውም ፣ አያገቡም ፣ አይጋቡም ፣ ብዛታቸውም በአኀዝ አይወሰንም ፤ ዕውቀታቸው ረቂቅ ፣ መዓርጋቸው ምጡቅ ፣ ኃይላቸው ትልቅ ነው ። መላእክት የእግዚአብሔር ልጆች ፣ ቅዱሳን መናፍስት ይባላሉ ። የፍጥረታት ጠባቂዎች እን ዲሆኑም እግዚአብሔር ሥልጣን ሠጥቶአቸዋል ። መላእክት ከነፋስና ከእሳት እንደተፈጠሩ መምህ ራን ያስረዳሉ ፤ አንዳንድ ሊቃውንትም መላእክት እግዚአብሔር ለይኩን ብሎ እንደፈጠራቸው ይና ገራሉ ።

እንዲሁም መላእክት የሥልጣን ደረጃ እንዳላቸው ከቅዱሳት መጻሕፍት እንረዳለን ። በመጽሐፈ ዳንኤል ስማቸው ጎልቶ የምናገኛቸው ሚካኤልና ገብርኤል ናቸው ። የመላእክት አለቃ የነበረው ሳጥናኤል ስለታበየ ቅ/ሚካኤል ተዋግቶ ድል አደረገው ፤ ሥልጣኑም ከራሱ ሥልጣን ጋር ደርቦ እንዲ ይዝ እግዚአብሔር ፈቅዶለታል ። በዚህም መሠረት የኃይላት ሊቃነ መላእክት አለቃ ሆነ ቅ/ገብርኤልም አብሣሬ ፍሥሐ ወሐሴት ስለሆነ መልአክ ብሥራት ተብሎአል ። ከዚህም ጋር የአንዱን ነገደ መላእ ክት አለቃ በመሆኑ ቅ/ገብርኤል ሊቀ መላእክት ተብሎ ይጠራል ። ከነርሱም ቀጥሎ በየነገዳቸው ላይ የተሾሙት ሊቃነ መላእክት አሉ ፤ አንዱ ነገድ የነፋስ ክንፍ የተሰጠው ኪሩቤል ነው ። ሁለተኛው ነገድ ስድስት ክንፍ የተሰጠው የሱራፌል ነገድ ነው ። በመጽሐፈ ሄኖክ ሩፋኤል ፣ በመጽሐፈ ዕዝራ ሱቱኤልና ዑራኤል በመባል የታወቁ ሊቃነ መላእክት እንዳሉ እናነባለን ። መጋቢ ብርሃናት ተብሎ የሚጠራ ቅዱስ ራጉኤልም የአንዱ ነገደ መላእክት አለቃ ነው ።

የመላእክት አገልግሎትና ዓላማ ሰውና እግዚአብሔር ማገልገል ነው ፤ ይልቁንም እግዚአብሔርን ሌት ተቀን ማመስገን ተቀዳሚ ዓላማቸው ነው ። ሰው በኃጢአት የሚሸነፍ ፍጥረት ስለሆነ በጥፋቱ ተጸጽቶ ንስሐ ገብቶ ወደፈጣሪው በሚመለስበት ጊዜ ጸሎቱንና ልመናውን ወደ እግዚአብሔር የሚ ያቀርቡለት ቅዱሳን መላእክት ናቸው ። እግዚአብሔርን የሚፈሩና በአምልኮቱ ጸንተው የሚኖሩም መላእክት ሌት ተቀን ይጠብቁአቸዋል ። ለልበ ትኖች የእግዚአብሔርን ኃይልና ሥልጣን ይገልጣሉ ኃጢአተኞችንም ይቀጣሉ ።

መላእክት ለሰዎች በተለያየ መልክ ይገለጣሉ ፤ ለሚወዱአቸው የእግዚአብሔር ወገኖች ሠይፋ ቸውን መዘው ይከላከሉላቸዋል ። የድል ኃይል ያጎናጽፏቸዋል ። ለምሳሌ ሕዝበ እስራኤል ከግብጽ ወጥተው በሲና ምድረ በዳ ተጉዘው በኢያሪኮ ፊት ለፊት በዮርዳኖስ ማዶ ባለው በሞዓብ ሜዳ ሠፍ ረው ሳለ ባላቅ ወልደ ሶፎር የተባለ ሰው በለዓም የተባለውን ጠንቋይ በብዙ ሺህ ገንዘብ ገዝቶ እስራ ኤልን ርገምልኝ አለው ፤ እግዚአብሔርም በለዓምን ሕዝቤን እስራኤልን እንዳትረግም ብሎ አስጠንቅ ቆት ሳለ በገንዘብ ተታልሎ የእግዚአብሔርን ትእዛዝ ተላልፎ ሕዝበ እስራኤልን ሊረግም ሲሄድ የእ ግዚአብሔር መልአክ በመንገድ ላይ ቆሞ የተመዘዘም ሠይፍ በእጁ ይዞ አየ ፤ ይኸንጠም የእግዚአብ ሔርም መልአክ በለዓምን የእግዚአብሔርን ትእዛዝ ተላልፎ ሄዶ ሊረግም በመሞከሩ «ዛሬ አንተን ገድየ አህያህን ባዳንኳት ነበር» ብሎ እንደገሠጸውና እንዳይራገም እንደከለከለው እንመለከታለን ።

ከዚህም አያይዞ ኢያሱ ሕዝቡን እየመራ የርዳኖስን አሳገር በኢያሪኮ አጠገብ ሳለ የእግዚአብ ሔር መልአክ የተመዘዘ ሠይፍ በእጁ ይዞ እፊቱ ቆሞ አየ ፤ ኢያሱም የጦር መሪና ፊታውራሪ መስሎ የታየው ማን እንደሆነ ለማወቅ ወደ እርሱ ቀርቦ ከእኛ ወገን ? ወይስ ከጠላቶቻችን ወገን ነህ ? ቢለው «አይደለሁም እኔ የእግዚአብሔር ሠራዊት አለቃ ሆኜ አሁን መጥቻለሁ» አለው ኢያሱም በግምባሩ ተደፍቶ ሰገደለት ፤ መልአኩም ኢያሱን ሊያደርገው የሚገባውን ሁሉ ነገረው ኢያሪኮንና ንጉሥዋን ፤ ጽኑአን ኃያላንዋንም ዛሬ በእጅህ ሰጥቸሃለሁ ብሎ በሰጠው ተስፋ መሠረት ኢያሪኮና ሕዝቦችዋ በኢያሱና በእስራኤላውያን እጅ እንደወደቁ በመጽሐፈ ኢያሱ ተዘግቦአል ።

የመላእክት አገልግሎት በዚሁ ብቻ አይወሰንም መልአኩ ቅ/ገብርኤል ዘካርያስ በቤተ መቅደስ ውስጥ በመንፈሳዊ አገልግሎት ላይ ሳለ እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም በቤተ መቅደስ ሆና ሐርና ወርቅ እያስማማች ስትፈትል ያበሰራቸውና የሰጣቸው ተስፋ ተፈጽሞላቸው እነሆ ክብራቸውና ገናናነታቸው ዘለዓለም በቅዱስ ወንጌል ተጽፎ ሲነገርና ሲመሰክር ይኖራል፤ቅዱስ ገብርኤል እመቤ ታችን ቅድስት ድንግል ማርያምን ትጸንሽያለሽ ወንድ ልጅም ትወልጅያለሽ ብሎ ባበሠራት መሠረት

www.ethiopianorthodox.org

በቤተ ልሔም ከተማ መድኅን ክርስቶስን እንደወለደችልን የታወቀ ነው ፤ ይህ የሕይወት ቃልም በቅዱሳት መካናትና በየአደባባዩ የምንመሰክረው መሠረተ እምነታችን ነው ። በዚሁ ዕለት«ድርገታተ መላእክት»(የመላእክት አንድነትና ኅብረት) እንደታየ ቅዱስ ሉቃስ በጻፈው ቅዱስ ወንጌሉ መረዳት ይቻላል « ድንገትም ብዙ የሰማይ ሠራዊት ከመልአኩ ጋር ነበሩ እግዚአብሔርንም እያመሰገኑ ክብር ለእግዚአብሔር በአርያም ይሁን ሰላምም በምድር ለሰውም በጎ ፈቃድ አሉ» ይላል ።

የዚህ ታላቅ ታሪክ መነሻ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በቤተ ልሔም በላሞች ግርግም ተኝቶ ሳሉ መላእክት ከሰማይ ወርደው ለጌታችንና ለአምላካችን ኢየሱስ ክርስቶስ ምስጋናና ጣዕመ ዝማሬካሰሙ በኋላ ከከተማው ወጣ ብለው መንጎቻቸውን ይጠብቁ ለነበሩ እረኞች ሄደው «ዛሬ በዳዊት ከተማ መድኃኒት እርሱም ክርስቶስ ጌታ የሆነ ተወልዶላችኋልና ይህም ምልክት ይሆንላችኋል ሕጻን ተጠቅልሎ በግርግም ተኝቶ ታገኛላችሁ» ብሎ መልአኩ ከነገራቸው በኋላ እረኞቹ ወደ ቤተ ልሔም መጥተው ሁኔታውንም በትክክል ተረድተው ፤ መላእክቱ እንዴት እንደታዩአቸውና ምን ያህሉስ እንደነበሩ ለሌሎች ሰዎች ፤ ሲያስረዱ የተናገሩት ቃል ነው ።

እነሆ ጌታ በተወለደባት ዕለት (ሌሊት) የሰማይ ሠራዊት «ስብሐት ለእግዚአብሔር በሰማያት ወሰላም በምድር ሥምረቱ ለሰብእ »እያሉ ጣዕመ ዝማሬአቸውን በቤተ ልሔም አካባቢ ለነበሩ ሲያበሥሩ አድረዋል ውለዋል፤ በዚሁ ጊዜ ሰውና መላእክት ባንድነት ሆነው አመስግነዋል ዘምረዋል፤ ሰዎቹ ግን እነማን እንደሆኑ ከፍ ብለን ገልጸናል፤ለመሆኑ መላእክቱ ከከተማ ውጭ ሄደው ይህ የምሥራች ለእረኞች የተናገሩት በቤተ ልሔም ከተማ ሰዎች ስላልነበሩ ነው? የሚል መጠይቅ ሊያስከትል ይችላል፤መልሱ ግን ነበሩ እንጂ የሚል ይሆናል፤እንዲያውም የከተማው ነዋሪዎች ብቻ ሳይሆኑ በአውግስጦስ ቄሣር ትእዛዝ ምክንያት ከየወረዳውና ከየቀየው በብዙ ሺህ ሚቈጠሩ ሰዎች ሊመዘገቡ ወደ ቤተ ልሔም መጥተው ስለነበር ከተማይቱ በሕዝብ ብዛት ተጣባ ትታይ እንደነበር ለመገመት አያዳግትም ።

ታዲያ በዓለም ካሉት የክርስትና እምነት ተከታዮች መካከል ስለመላእክት ተፈጥሮ ሁኔታ ስለ ደረጃቸው አቀማመጥ ስለ አገልግሎታቸው ጠቃሚነት አውቀው የሚያሳውቁ በአማላጅነታቸው አምነው የሚያሳምኑ ብዙዎች ናቸው የእመቤታችን፣ የመላእክት ፣ የነቢያት ፣ የሐዋርያት ፣ የጻድቃንና የሰማዕታት አማላጅነት የማይቀበሉ (የማያምኑ ) እንዲያውም የመላእክትን መኖር የሚጠራጠሩና የሚክዱ በዘመናችን እንደአሸን እየፈሉ መታየታቸው የአደባባይ ምሥጢር ነው ። በህልውናቸውና በአማላጅነታቸው የሚታመኑም እንዳላዋቂዎች ሲያፌዙባቸው ይታያል፤ ታዲያ እነዚህ ዝንጉአን ልብ ባሁኑ ጊዜ የመላእክትን ህልውና የከዋክብት ተመራማሪዎች ሊቃውንት (አስትሮኖመርስ ዙብል በተባለችው ግኡዝ ዕቃ የኅዋ ቴሌስኮፕ ተልካ በስፋት ያነሣችውንና ወደ ምድር ያስተላለፈችውን የመላእክት ሥዕል ሲያዩ ከቶ ምን ምክንያት ይሰጡበት ይሆን ?

ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በበዓለ ሆሣዕና ወደ ቤተ መቅደስ ሲገባ ሕጻናት ሆሣዕና በአርያም እያሉ ሲያመሰግኑት አይተው በቅንዓት እሳት የተቃጠሉ ፈሪሳውያን ሕጻናቱ ለምን ዝም እንዲሉ አታደርግም? ቢሉት እነርሱ ዝም ቢሉ እዕባን ይዘምሩልኛል (ያመሰግኑኛል) በማለቱ የቢታንያ ደንጊያዎች አፍ አውጥተው አመስግነውታል ። በዚህ አኳያ ሰዎች መላእክቱን ሲክዱበት ዙብል የተባለችው ሰው ሠራሽ መንኰራኲር የመላእክቱን ህልውና ስታረጋግጥ ልበ ደንዳኖች እናምንም ሲሉ ለነበረው ክርክራቸው አሁንስ ምን ምክንያት ይሰጡበት ይሆን ?

ዙብል ከአንድ አስደናቂና አንጸባራቂ ኮከብ ብሩኃንና ነጭኃነ ቁመት የሆኑ ሰባት ባለትላልቅ ክንፍ ድርገታተ መላእክት ሲወጡ አግኝታ ሥዕላቸውን እያነሣች ወደምድር በምትልክበት ጊዜ የከዋክብት ተመራማሪዎች በቴሌስኮፕ ሁኔታቸውን እያዩ እጅግ እንደተደሰቱና ብሩህ ገጻቸውና ፈገግታቸው አይተውም ምናልባት ሰላም ፍቅርና አድንድነት ፣ ረሀብ ፣ እርዛትና ልዩ ልዩ የበሽታ ዓይነቶች ለሚፈራረቁበት በምድር ላይ ላለው ፍጥረት ሁሉ መላእክት በጌታ ልደት ቀን «ክብር ለእግዚአብሔር በአርያም ይሁን ፣ ሰላምም በምድር ለሰውም በጎ ፈቃድ» እያሉ የዛሬ ሁለት ሺህ ዓመታት ገደማ በቤተ ልሔም የተናገሩለት የምህረት ዓዋጅ ዛሬም ሊያውጁለት ይሆናል ሲሉ ተንብየዋል ።

ስለዚህ ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ «እንግዲህ ለምኞቱ እንድትታዘዙ በሚሞት ሥጋችሁ ኃጢአት አይንገሥ ብልቶቻችሁንም የዓመጻ የጦር ዕቃ አድርጋችሁ ለ ኃጢአት አታቅርቡ ነገር ግን ከሙታን ተለይታችሁ በሕይወት እንደምትኖሩ ራሳችሁን ለእግዚአብሐር አቅርቡ» እንዳለው ከኃጢአት እንከርዳድ ርቀን የጽድቅ ስንዴ አፍርተን እንድንገኝ ቸር አምላካችን በቸርነቱ ይጠብቀን በኃይሉ ይርዳን ።

ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ መርቆሬዎስ ፓትርያርክ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ የ፲፱፻፹፫ ዓ/ም በዓለ ... ምክንያት በማድረግ ለመላ የኢትዮጵያ ሕዝብ በሬድዮ ፣ በቴሌቭዥንና በጋዜጦች ያስተላለፉት ቃለ ...

# በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ አሜን

በገጠርና በከተማ የምትገኙ ምእመናን

የሀገራችንን ዳር ድንበር ለማስከበር ነፃነትዋንና አንድነትዋን ለመጠበቅ በመሐል አገር በሥራ ላይ የምትገኙ ፣ ሠራዊት በሕማም ምክንያት በሐኪም ቤት ያላችሁ ምእመናን

የዓለም ቤዛ መድኃኒታችን ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ እንኳን ለብርሃን ልደቱ በሰላም አደረሳችሁ ።

«ኢትፍርሁ እስመ ናሁ እዜንወክሙ ዐቢየ ዜና ፍሥሐ ዘይከውን ለክሙ ወለኵሉ ዓለም እነሆ ለእናንተና ለዓለም ሁሉ የሚሆን ታላቅ ደስታ የምሥራች እነግራችሁ አለሁና አትፍሩ» (ሉቃ ፡ ፪ ፡ ፲፩)

የሰው ልጅ በኃጢአት ከወደቀ በኋላ ከፈጣሪው በመራቁ ፈጣሪውም ከርሱ በክብርና በረድኤት በመለየቱ በፍርሃት መኖር ጀመረ፡ መንፈሳዊ ሕይወቱ ጨለመ ደስታው ወደ ኀዘን ተለወጠ፡ከፈጣሪውና ከባልንጀራው ጋር ሰላሙን አጣ፡ ስለዚህ ሥጋዊውም ሆነ መንፈሳዊው ሕይወቱ ጥላቻን የተመላ ሆነ ፣ ከእግዚአብሔርም ከሰውም ጋር ስምምነትን ሊያገኝ አልቻለም» ኃጢአት በእግዚአብሔርና በሰው መካከል እንደ መጋረጃ ሆኖ አለና» (ኢሳ ፶፱ ፡ ፩—፪)

ነገር ግን የሰው ልጅ ከእግዚአብሔር ተለይቶ ሰላምና ደስታን አጥቶ በፍርሃትና በጨለማ ተውጦ ለዘለዓለም እንዲኖር እግዚአብሔር አልፈቀደም ። ከሰማየ ሰማያት ወርዶ ከቅድስት ድንግል ማርያም ተወልዶ እንደሚያድነው ተስፋ ሰጠው ። የተስፋው ዘመን ፍጻሜም በደረሰ ጊዜ በበደሉ ምክንያት ከተፈረደበት ፍዳ ነፃ ያወጣው ዘንድ እግዚአብሔር ወልድ ወደዚህ ዓለም መጥቶ ከንጽሕት ቅድስት ድንግል ማርያም ሰው ሆኖ ተወለደ ። በተወለደበትም ዕለት በቤተ ልሔም አካባቢ መንጎቻቸውን ይጠብቁ ለነበሩ እረኞች የእግዚአብሔር መልአክ «አትፍሩ ለእናንተና ለዓለም ሁሉ የሚሆን ታላቅ ደስታ እነግራችሁአለሁና» በማለቱ የክርስቶስ ልደት ለዓለም ታላቅ ደስታ መሆኑን ፤ በክርስቶስ ልደት በሰው ልጅ መንፈሳዊ ሕይወት ላይ የነበረው ፍርሃት መወገዱን አብስሮአል ።

ከመልአኩም ጋር የነበሩ የሰማይ ሠራዊት ከሰዎች ጋር በኅብረት «ስብሐት ለእግዚአብሔር በሰማያት ወሰላም በምድር ሥምረቱ ለሰብእ» ክብር ለእግዚአብሔር በሰማያት ይሁን ፤ ሰላም በምድር ፤ ለሰውም በጎ ፈቃድ ይሁን ብለው በመዘመራቸው በክርስቶስ ልደት በእግዚአብሔርና በሰዎች መካከል ሰላም መመሥረቱን ፤ ዕርቅ መጀመሩን ከፈጣሪው ርቆ የነበረው የሰው ልጅ ወደ ፈጣሪው መቅረቡን መስክረዋል ።

እንደዚሁም «ሕዝብ ዘይነብር ውስተ ጽልመት ርእየ ብርሃነ ዐቢየ ወለእለ ይነብሩ ውስተ ጽልመት ወጽላሎተ ሞት ብርሃን ሠረቀ ሎሙ»በጨለማ የሚኖር ሕዝብ ታላቅ ብርሃን አየ ፡ በጨለማና በሞት ጥላ ውስጥ ለሚኖሩም ብርሃን ወጣላቸው ተብሎ በነቢዩ ኢሳይያስ አስቀድሞ እንደተነገረ እውነተኛው የዓለም ብርሃን ክርስቶስ ወደዚህ ዓለም በመምጣቱ ከሰው ሕይወት ላይ የኃጢአትና የሞት ጨለማ ተወግዶ (ኢሳ ፱ ፡ ፩—፪) የሰው መንፈሳዊሕይወት ብሩህ ሆነ በክርስቶስ ብርሃን ልደት ሰው እግዚአብሔርን ለማየት ቻለ በክርስቶስ ልደት መላእክትና የሰው ልጆች አንድ ማኅበር ሆኑ ፣ በአንድ ድምፅ እግዚአብሔርን አመሰገኑ በአንድ ቃል ሰላምን ለዓለም ዐወጁ ፣ ለሰውም በጎ ፈቃድን ተመኙ ። ስለዚህ የጌታችን የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ልደት ሰላምና ፍቅር ድኅነትና ደስታ ብርሃንም ነው ። በመሆኑም በዓሉን በምናከብርበት ዕለት እነዚህን ነገሮች ልናስታውስ ይገባል።

ክርስቶስ በተወለደበት ዕለት የታወጀው የዓለም ሰላም«አትፍሩ» የሚለው አጽናኝ ቃል ዛሬ እንዴት ነው ? በዓለም ላይ ደስታ አለወይ? ሰዎች ያለ ፍርሃት መኖር ችለዋል ወይ ?

የሰው ልጅ በክርስቶስ ለተጎናፀፈው ነጻነቱ ምክንያት እየሰጠ እንደገና በራሱ ላይ የኃጢአት ቀንበርን በመጫኑ የሰላም ባለቤት ከመሆን ወጥቶአል ። በሰላምና በነጻነት እንዲኖርባት በተሰጠችው ዓለም ላይም ከሰላም ይልቅ ጥላቻና ጦርነት ፍርሃትና ሽብር ሥጋትና ጭንቀት በዝቶ ይታያል ።

ይሁን እንጂ ሰላም ወዳዶች የዓለም መንግሥታትና የአብያተ ክርስቲያናት መሪዎች ሰላምን በዓለም ላይ ለማስፈን ከፍተኛ ጥረት ማድረጋቸው አልቀረም ፡ ነገር ግን «ለክፉዎች ሰላምየላቸውም»ተብሎ እንደ ተጻፈ (ኢሳ ፡ ፶፯ ፡ ፳፩ ፡) ሰላምንና አንድነትን የማይሹ ከበጎ ነገር ይልቅ ክፋትን የሚከተሉ የሰላም ተቃዋሚዎች በየጊዜው በመነሣታቸው በሰው ልጆች መካከል ጥላቻ ገኖ ፣ ጦርነት ሰፍኖ ሰላም መንምኖ ይታያል።ይህም ሁኔታ ሰላም አፍቃሪዎች ሁሉ እያሳዘነ ነው ።



www.ethiopianorthodox.org

ዛሬ ያለንበት ዘመን የሰው ልጅ በጥበብ ተራቆ ፣ በዕውቀት መጥቆ የሚገኝበት ወቅት ሲሆን በዚሁ አንፃር ደግሞ የከፍተኛ ጥፋት ባለ ቤት ሆኖ መገኘቱ እጅግ አሳዛኝ ነው ።

በተለይም በአሁኑ ወቅት እጅግ አስጊና አሰቃቂ የሆነው በፋርስ ባሕረ ሠላጤ ላይ የተመዘዘው ሰይፍ በሰላም ወደ አፎቱ እንዲመለስ ካልተደረገ በአካባቢውና በሌላውም ላይ የሚደርሰው ጥፋት ከዚህ በፊት በዓለም ላይ ከታየው ጥፋት ያላነሰ እንደሚሆን ግልጥ ሆኖ ይታያል ።

ይህ እንዳይሆን የመንግሥታት መሪዎች በውይይታቸው ፣ የሃይማኖት መሪዎች በጸሎታቸው እጅግ ለከበረውና በእግዚአብሔር አምሳል ለተፈጠረው ለሰው ልጅ ሕይወት ሲሉ ስለ ሰላሙ ከመቼውም ጊዜ የበለጠ ከፍተኛ ጥረት ሊያደርጉ ይገባል ።

የሰላም አምላክ እግዚአብሔር ወልድ ሰው ሆኖ በተወለደበት ዕለት በመላእክትና በሰዎች አንደበት እንደተነገረ ሰላም በምድር ሰላም በባሕር ፣ ሰላም በአየር እንዲሰፍን ምእመናን ሁሉ ከልብ በመነጨ ስሜት ሊጸልዩ ይገባል ።

የተወደዳችሁ ምእመናን

ነገ የምናከብረው የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ በዓለ ልደት የደስታ የሕይወትና የነፃነት በዓል መሆኑን ተገንዝበን ነፃነት እኩልነትና ትክክለኛ ፍትሕ አጥተው ለሚቸገሩት ወገኖች ሁሉ ማሰብ ይገባናል ።

በተለይም በሀገራችን ሰሜናዊ ክፍል በተነሣው ጦርነትና በድርቅ ምክንያት ከቤት ንብረታቸው ተፈናቅለው መጠለያ አጥተው በከፍተኛ ችግር የሚገኙትና ይህን የሰላምና የደስታ በዓል በተለመደው ሃይማኖታዊ ሥርዓት በየሰበካ ቤተ ክርስቲያናቸው ተገኝተው ለማክበር ያልቻሉ ወገኖቻችንን ልናስባቸው ይገባል ። ጦርነቱም በሰላም እንዲለወጥ ተቃዋሚያን ወገኖችም ቤተ ክርስቲያናችን በተደጋጋሚ ያሳለፈቻቸውን የሰላም ጥሪ እንዲቀበሉና ለሰላምና ለአንድነት እንዲጥሩ ችግሮች በውይይት እንዲፈቱ ቤተ ክርስቲያናችን አሁንም የሰላም ጥሪዋን ታስተላልፋለች ። በተለያየ ምክንያት ላዘኑት እግዚአብሔር መጽናናትን እንዲሰጣቸው ኀዘናቸውን ወደ ደስታ እንዲለውጥላቸው መጸለይ አስፈላጊ ነው ።

በረኃብ በእርዛትና በሕማም ተጨንቀው የበዓሉን ደስታ የማያውቁም ብዙዎች ናቸው ፣ ስለዚህ የክርስቶስ በዓለ ልደት የጥቂቶች ብቻ ሳይሆን ለሁሉም እንዲሆን ለተቸገሩት ሁሉ የፍቅርና የርኅራኄ ሥራ ልንሠራላቸው በሩቅም በቅርብም ያሉትን ሁሉ አቅማችን በሚፈቅደውና በዘወትር ጸሎታችን ልናስባቸው ይገባናል ።የመንፈሳዊ በዓል አከባበርም ዓላማው ይህ ነው ።

የምንኖርበት ዓለም ችግሩ አንድና ሁለት ተብሎ ተቈጥሮ የሚያበቃ አይደለም በየ ጊዜው የተለያዩ ችግሮች ይታያሉ ። ከእነዚህም አንድ የሰው ልጅ ሕገ እግዚአብሔርን ባለመጠበቁ ፣ለራሱና ለባልንጀራው ባለመጠንቀቁ በሥነ ምግባሩ ጉድለት ያመጣው የማይሽር ደዌ ነው ። ይህም ከጦርነቱ ከረኃብና ከሌላው ችግር ሁሉ ጋር ተዳምሮ የዓለምን ሕዝብ ከከባድ ፍርሃትና ስጋት ላይ ጥሎት ይታያል ።

ስለዚህም እግዚአብሔር በቸርነቱ ደዌውን እንዲያርቅልን ሰውም ሕግን በመተላለፍ ከሚመጣ ደዌና መቅሠፍት ራሱን እንዲጠብቅ አዘውትሮ ማስተማር መምከርና መጸለይ ያስፈልጋል ።

በእግዚአብሔር ትእዛዝ ጸንቶ ሕገ እግዚአብሔርን ጠብቆ ማለት አንድ ወንድ በአንድ ሴት አንድሴት በአንድ ወንድ ተወስኖ መኖር ራስንና የሚቀጥለውን ትውልድ ከዚህ አደገኛና ቀሣፊ በሽታ መጠበቅ እንደሚገባ ቤተ ክርስቲያን ከጥንት ጀምራ ስታስተምር ኖራለች ። አሁንም ሥጋዊና መንፈሳዊ ሕይወቱ የተስተካከለ ወላጆቹን ተከቶ ያቆዩለትን ቅርስ ተረክቦ ሀገርን የሚያገለግል ጥሩ ጤናማ ዜጋ እንዲገኝ ምእመናን ሁሉ ሕገ እግዚአብሔርን ጠብቀው እንዲኖሩ ቤተ ክርስቲያን ታስተምራለች ።

ከዚህም ጋር የጸና ሃይማኖት የቀና ምግባር ይዞ ራስ ወዳድነትንና ግላዊነትን አስወግዶ በሰላምና በፍቅር ሆኖ ሀገርንና ቤተ ክርስቲያንን ማገልገል ለሀገርና ለቤተ ክርስቲያን ታማኝ ሆኖ መገኘት የጥንታውያን እውነተኞች ኢትዮጵያውያን ባሕርይ ስለሆነ የዛሬዎቹ ኢትዮጵያውያንም ሊዘነጉት አይገባም ።

እግዚአብሔር ወደዚህ ዓለም የመጣውና ሰው ሆኖ ከቅድስት ድንግል ማርያም የተወለደው ሰው በበደሉ እንደጠፋ እንዳይቀር ዮ- ሰው ፍቅር አገብሮት ነው ። እርሱ እኛን እንደወደደን እኛም እርስ በርሳችን እንድንፋቀር እንድንረዳዳ በቃልም በተግባርም አስተምሮናል ። ሰላምንና አንድነትንም እንድናጸና በዕለተ ልደቱ ተለያይተው የነበሩ መላእክትና ሰዎች በአንድነት ሆነው «ሰላም በምድር ለሰውም በጎ ፈቃድ» በማለት ሰላምንና አንድነትን አብስረዋል ።

ስለዚህ እኛም ዛሬ ይህን የምሥራች ደግመን ሰላም በምድር ለሰዎችም በጎ ፈቃድ ፡ በማለት ጥላቻ በዕርቅ ጦርነት በሰላም እንዲለወጥ ችግሮች በሰላማዊ ውይይት እንዲፈቱ የሚጠይቀውን የቤተ ክርስቲያናችንን መልእክት በዚህ ዐቢይ ሃይማኖታዊ በዓል ምክንያት እናስተላልፋለን ።

እግዚአብሔር ሀገራችን ኢትዮጵያን በሰላም በአንድነት ያጽናልን ለዓለም ሁሉ ሰላሙንይስጥልን በዓሉን የሰላምና የደስታ በዓል ያድርግልን ።



# ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ መርቆሬዎስ ስድስት ኤጲስ ቆጶሳት

## በአንብሮተ እድ ሾሙ

ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ መርቆሬዎስ ፓትርያርክ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ ጥቅምት ፲፰ ቀን ፲፱፻፹፫ ዓ/ም በመንበረ ጸባኦት ቅድስት ሥላሴ ካቴድራል ስድስት ኤጲስ ቆጶሳት በአንብሮተ እድ ሾመዋል ። በዚህ በዓለ ሢመት ላይ የመላ ኢትዮጵያ ሊቃነ ጳጳሳት ፤ የወዳጅ አብያተ ክርስቲያናት ተወካዮች ፤ የሰበካ ጉባኤ ም/ሊቃነ መናብርት አያሌ ሊቃውንትና ካህናት እንዲሁም ጥሪ የተደረገላቸው እንግዶችና በብዙ ሺህ የሚቈጠሩ ምእመናን ተገኝተው የበዓለ ሢመቱን ተካፋዮች ሆነዋል ።

ስለ በዓለ ሢመቱ ከኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን መንበረ ፓትርያርክ በወጣው መርሐ ግብር መሠረት ጸሎተ ቅዳሴው የተመራው በብፁዕ ወቅዱስ አቡነ መርቆሬዎስ ፓትርያርክ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ በብፁዓን ሊቃነ ጳጳሳት ተራዳኢነት ነው ።



ብፁዕ ወቅዱስ ፓትርያርክ ከሥርዓተ ሢመቱ ፍጻሜ በኋላ ቃለ በረከት ሲያስተላልፉ

ከጸሎተ ቅዳሴው አጋማሽ ላይ ብፁዓን ኤጲስ ቆጶሳቱ በተዘጋጀላቸው ሥፍራ እንዳሉ ቅዱስ ፓትርያርኩ ከብፁዓን ሊቃነ ጳጳሳትና ከመዘምራን ጋር የሢመተ ጸሎቱን ሥርዓት አድርሰዋል ይህ በዚህ እንዳበቃም ቅዱስነታቸው ለእያንዳንዳቸው የሚገባቸውን የመዓርገ ጵጵስና ልብስ ፤ አክሊል ፤ አርዌ ብርትና የእጅ መስቀል ሰጥተዋቸዋል።ከዚህም አያይዘው በቅደም ተከተል የጵጵስና ስም በመሰየም ሀገረ ስብከትንም በመስጠት የኤጲስ ቆጶስነት ሥልጣን ሲሰጡአቸው ሊቃነ ጳጳሳቱ ሊቃውንቱና ሕዝቡ ይደልዎ ይደልዎ እያሉ በጭብጨባና በዜማ በቅዱስነታቸው የተሰጣቸውን የጵጵስና ማዕርግ የተገባው ነው በማለት ደስታውን ገልጸዋል ።

በኤጲስ ቆጶስነት ተመርጠው የተሾሙት ኤጲስ ቆጶሳት ፤

፩ኛ/ መምህር ተወልደብርሃን ወልደ ሥላሴ በኤርትራ ራስ ገዝ ሀገረ ስብከት የታላቁ የደብረ ቢዘን ገዳም አበምኔት የነበሩ ብፁዕ አቡነ ፊልጶስ ተብለው የመላ ኢትዮጵያ ገዳማት ኤጲስ ቆጶስ ።

፪ኛ/ ሊቀ ሥልጣናት አባ ሀብተ ማርያም ወርቅነህ የሰዋሰወ ብርሃን ቅ/ጳውሎስና ከፍተኛ መንፈሳዊ ት/ቤት ዲን ብፁዕ አቡነ መልከ ጼዴቅ ተብለው የት/ቤቱ ኤጲስ ቆጶስ ፤

፫ኛ/ ሊቀ ሥልጣናት አባ ገ/ሥላሴ ኃ/ማርያም በምድረ ሱዳን የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤ/ክርስቲያን ኃላፊ የነበሩ ብፁዕ አቡነ አረጋዊ ተብለው በምድረ ሱዳን የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤ/ክርስቲያን ኤጲስ ቆጶስ ።

፬ኛ/ መምህር ኅሩይ መንግሥቱ የአ- አበባ መንበረ መንግሥት ቅ/ገብርኤል ቤ/ክርስቲያን አስተዳዳሪ የነበሩ ብፁዕ አቡነ በርናባስ ተብለው የአ-አበባ ሀ/ስብከት ኤጲስ ቆጶስ

፭ኛ/ መጋቤ ኅሩያን አባ ኃይለ ኢየሱስ ከበደ የብፁዕ ወቅዱስ ፓትርያርክ ልዩ ጸሐፊ ብፁዕ አቡነ ጎርጎርዮስ ተብለው የብፁዕ ወቅዱስ ፓትርያርክ ልዩ ጽ/ቤት ኤጲስ ቆጶስ ፤

፮ኛ/ መልአከ ሰላም አባ ሀብተ ማርያም ደምሴ የአ-አበባ ደብረ ብሥራት ቅ/ገብርኤል



www.ethiopianorthodox.org

ቤተ ክርስቲያን አስተዳዳሪ የነበሩ ብፁዕ አቡነ ተክለ ሃይማኖት ተብለው የድሬዳዋ ራስ ገዝ ሀገረ ስብከት ኤጲስ ቆጶስ ናቸው ።

ብፁዕ ወቅዱስ ፓትርያር ከተሾሙት ሐዲሳን ኤጲስ ቆጶሳትና ከብፁዓን ሊቃነ ጳጳሳት ጋር በዓ ውደ ምህረቱ እንደተገኙ መዘምራኑ «ሤመከሙ እግዚአብሔር ፤

ተር ብፁዕ አቡነ ገብርኤል የኤርትራ ራስ ገዝ ሀገረ ስብከት ሊቀ ጳጳስ የበዓሉን ታሪካዊነትና የብፁዕ ወቅዱስ ፓትርያርክን ሐዋርያዊ እንቅስቃሴ በተመለከተ በየ



ብፁዕ አቡነ ተክለ ሃይማኖት



ብፁዕ አቡነ መልከ ጼዴቅ



ብፁዕ አቡነ አረጋዊ



ብፁዕ አቡነ በርናባስ



ብፁዕ አቡነ ጎርጎርዮስ



ብፁዕ አቡነ ፊልጶስ

ከሥርዓተ ሢመቱ ፍጻሜ በኋላ ብፁዕ አቡነ መልከ ጼዴቅ የሰዋሰወ ብርሃን ቅዱስ ጳውሎስ ከፍተኛ መንፈሳዊ ት/ቤት ኤጲስ ቆጶስ በራሳቸውና በተሿሚዎቹ ኤጲስ ቆጶሳት ስም በብፁዕ ወቅዱስ አቡነ መርቆሬዎስፓትርያርክ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ ፊት የሃይማኖት ምስክርነት ቃል ሰጥተዋል። ከዚያም የበዓለ ሢመቱ መርሐ ግብር በዐውደ ምሕረቱ ቀጥሎ

ጳጳሳት - - - » የሚለውን ግሥ ቃኝተው ለሃያ ደቂቃ ያህል አሸብሽበዋል ። ከዚያም የሰንበት ት/ቤት መዘምራን ለበዓለ ሢመቱ የሚስማማውን መዝሙር አሰምተዋል ። እንዲሁም የተፈተደላቸው ሊቃውንት በዓለ ሢመቱን በተመለከተ ቅኔያት አበርክተዋል ።

ይህ በዚህ እንዳበቃም ዶክተር ማርቆስ ወ/ኢየሱስ የጠ/ቤተ ክህነት ዋና ሥራ አሥኪያጅና ዶክ ተራ ንግግር አድርገዋል ።

በመጨረሻም ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ መርቆሬዎስ ፓትርያርክ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ ሁሉንም ማድረግ የሚቻለው የሀገር አንድነትና ሰላም ሲኖር መሆኑን በማስመልከት ስለሀገር አንድነትና ሰላም ያለማቋረጥ መጸለይና የሚቻለውን ጥረት ሁሉ ማድረግ እንደሚገባ ቃለ ምዕዳን ከሰጡና ጸሎተ ቡራኬ ካደረጉ በኋላ ጠቅላላ የበዓለ ሢመቱ ስነ ሥርዓት ፍጻሜ ሆኗል ።



# የቡልቡላ ፈለገ ሕድወት አቡነ ገ/መንፈስ ቅዱስ

## ቤተ ክርስቲያን ቅዳሴ ቤቱ ተከበረ

የቡልቡላ ፈለገ ሕይወት አቡነ ገብረ መፈንስ ቅዱስ በአዲስ አበባ ሀገረ ስብከት በደብረ ዘይት መንገድ በድሮ ከፍተኛ ፲፬ ቀበሌ ፶፫ ክልል የሚገኘውና በመሠራት ላይ የቆየው የቡልቡላ ፈለገ ሕይወት አቡነ ገ/መንፈስ ቅዱስ ቤ/ክርስቲያን ጥቅምት ፩ ቀን ፲፱፻፹፫ ዓ/ም በብፁዕ ወቅዱስ አቡነ መርቆሬዎስ ፓትርያርክ ርእሰሊቃነጳጳሳት ዘኢትዮጵያ ሕንጻ ቤ/ክርስቲያኑ በውስጥና በአፍአ ከተባረከ በኋላ ታቦተ ሕጉ ወደ መንበረ ክብሩ ገብቶአል ።

በዚሁ ዕለት የቅዱስ ሲኖዶስ አባላት ብፁዓን ሊቃነ ጳጳሳት የጠቅላይ ቤተ ክህነት የየመምሪያ ኃላፊዎች ፤ የአድባራትና ገዳማት አስ አስተዳዳሪዎች ፤ ሊቃውንትና ካህናት ታላላቅ የከተማው ነዋሪዎችና በብዙ ሺህ የሚቈጠሩ ምእመናን ተገኝተዋል ።


ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ መርቆሬዎስ ፓትርያርክ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ ከብፁዓን ሊቃነ ጳጳሳት ጋር ለጥቅምት ፩ ቀን ፲፱፻፹፫ ዓ/ም አጥቢያ ከሌሊቱ ልክ ፲ ሰዓት ሲሆን በቤተ ክርስቲያኑ ተገኝተዋል ። በዚሁ ወቅት የደብሩ አስተዳዳሪ መልአከ ሕይወት ወልደ ሰንበት አድሐና ከሰበካ ጉባኤው አባላት ጋር በመሆን ልብሰ ተክህኖ የለበሱ ፤ የሻማ መብራትና መስቀል ጽንሐሕ የያዙ ካህናትና ዲያቆናትን በማሰለፍ የደብሩ ሰንበት ት/ቤት መዘምራን «ባርከኒ አባ እንሣእ በረከተከ» እያሉ በመዘመር በከፍተኛ ክብር ተቀብለዋቸዋል ። ቅዱስነታቸውም ከብፁዓን ሊቃነ ጳጳሳት ጋር ወደ ቤተ መቅደስ ገብተው የሕሊና ጸሎት ካደረሱ በኋላ በተዘጋጀላቸው የክብር ሥፍራ ተገኝተው በበዓሉ ምክንያት ለተሰበሰበው ሕዝበ ክርስቲያን ቡራኬአቸውን አስተላልፈውለታል ።

ልክ ፲፪ ሰዓት ሲሆን በቅዱስ ፓትርያርኩ ሠራዒነትና መሪነት በብፁዓን ሊቃነ ጳጳሳቱ ተራዳኢነት ሥርዓተ ቅዳሴው ቀጥሎ እስከ ቀኑ ሁለት ሰዓት ተኩል ተካሂዶአል ። ታቦተ ሕጉ በሦስት ሰዓት ወጥቶ ሥርዓተ ዑደቱ ተከናውኖ በተዘጋጀለት ሥፍራ እንደቆመ ሊቃውንቱ ለዕለቱ የሚስማማውን ግሥ ቃኝተው ለሃያ ደቂያቃ ያህል አሸብሽበዋል ። እንዲሁም የደብረ ናዝሬት ቅዱስ ዮሴፍና የደብሩ ሰንበት ት/ቤት መዘምራንና የመቀሌ ከሣቴ ብርሃን ሰንበት ት/ቤት ተማሮች በቅደም ተከተል ጣዕመ ዝማሬ አሰምተው እንዳበቁ በብፁዕ ወቅዱስ አቡነ መርቆሬዎስ ፓትርያርክ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ የተቀደሰ ፈቃድ ሊቀ ሥልጣናት አባ ሀብተ ማርያም ወርቅነህ ባሁኑ ጊዜ ብፁዕ አቡነ መልከ ጼዴቅ የሰዋሰወ ብርሃን ቅ/ጳውሎስ ከፍተኛ መንፈሳዊ ት/ቤት ኤጲስቆጶስየዕለቱን የስብከተ ወንጌል ትምህርት ሰጥተዋል።

ይህ በዚህ እንዳበቃም ከደብሩ ሰ/ጉ/ም/ሊቀ መንበር ከአቶ አብርሃም ገብሬ ሪፖርት ቀርቦ በንባብ ተሰምቶአል ። ቀጥሎም አቶ አብርሃም ገብሬ በሰበካ ጉባኤና በቤተ ክርስቲያኑ ሕንፃ ሥራ ተሳትፎ ያደረጉ ፤ በገንዘብ ፤ በጉልበትና በሀሳብ አስተዋጽኦ ያበረከቱ ምእመናን ልዩ ልዩ ስጦታና የምስክር ወረቀት እንዲሰጡላቸው ቅዱስ ፓትርያርኩን በታላቅ ትሕትና ስለጠየቁ ቅዱስነታቸውም ለእያንዳንዱ ተሸላሚ አባል ሁሉ በቅደም ተከተል ስጦታውና ሽልማቱ ሲሰጡአቸው ሕዝቡ በእልልታና በጭብጨባ ደስታውን ገልጾላቸዋል

በተለይም የደብሩ አስተዳዳሪ መመልአከ ሕይወት ወልደ ሰንበት አድሐና ቤተ ክርስቲያኑ ከመመሥረቱ በፊት ፀበል ቤቱን በማዘጋጀት ፤ በኋላም በአስተዳዳሪነት ፤ በጠበል እጥማቂነት ፤ ለቤተ ክርስቲያኑ ሥራ ምእመናንን በመቀስቀስ በማስተባበር ቤ/ክርስቲያኑ ተመሥርቶ እስካለቀ ድረስ እንደ አንድ ተራ ሠራተኛ በአስፈላጊው ሥፍራ ሁሉ ገብተው በመሥራት ፤ በማሠራት ፤ ኃላፊነትን በመወጣት በቅን ልቦና ፤ በንጹሕ ሕሊና ቤ/ክርስቲያኑን ለዚህ ፍጻሜ ያደረሱ በመሆናቸው ከደብሩ ሰበካ ጉባኤ ጽ/ቤት ከወርቅ ሙካሽ የተሠራ የወርቅ ካባ ፤ ከብፁዕ ወቅዱስ አቡነ መርቆሬዎስ ፓትርያርክ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ የእጅ ወርቅ መስቀል በቅዱስነታቸው እጅ ተሸልመዋል ።

ከሽልማቱ ሥነ ሥርዓት ፍጻሜ በኋላም ቅዱስ ፓትርያርኩ «ይህ አስደናቂ ሕንጻ ቤተ ክርስቲያን በጥቂት ዓመታት ውስጥ እንዲህ ተከናውኖ ለማየት በመብቃታችን እግዚአብሔር አምላካችንን እና መሰግናዋለን ። ሆኖም ግን እንዲህ ያለ ቤተ ክርስቲያን ለመሥራት የቻልነው እንዲህ ተሰብስበን በኅብረትና በአንድነት በዓሉን ለማክበር የበቃነው በአካባቢያችን ሰላም ስላለ ነው ሰላም ከሌለ ይህ ሁሉ ለመሥራት ፤ ለመሰብሰብ አንችልም ስለዚህ በሀገራችን ሰላም እንዲሆን ፍቅር አንድነት በመካከላችን እንዲሰፍን ረሀቡ ፤ ጦርነቱ በሽታው እንዲወገድ እግዚአብሔር አምላካችን በጾም ፤ በጸሎት በፍቅርባንድነት ሆነን መለመን አለብን ስለሁላችንም ሰላም በያለንበት ፈጣሪያችንን በጸሎት መጠየቅ ይገባናል ። ለሁሉም እግዚአብሔር አምላካችን በኃይሉ በቸርነቱ ይርዳን» በማለት ጸሎተ ቡራኬ ሰጥተው እንዳበቁ የበዓሉ ፍጻሜ ሆኖአል ።





www.ethiopianorthodox.org

# ስብሐት ለእግዚአብሔር በሰማያት

ጧቱ በማታ ማታው በጧት በተፈራረቀ ቊጥር ስብሐት ለእግዚአብሔር ምሥጋና ለእግዚአብሔር ይገባል የሚለው ዐረፍተ ነገር በእልፍ አእላፍ ፍጡራን አንደበት ይነገራል ልዑል እግዚአብሐር አምላክ ዓሶምንና በውስጧ ያሉትን ፍጥረታት ኮአለመኖር ወደ መኖር አምጥቶ በመፍጠሩ ታላቅ ስሙን በማመስገን ፍጥረታት ክብር ጸጋ ይላበሳሉ ።

ከምድራውያን ፍጥረታት በተለይ ሰማያውያኑ ፍጥረታት የተፈጠሩት እግዚአብሔርን ለማመስገንና ለታላቅ ስሙ ለመስገድ ነው በምድር ላይ የሚኖሩት ፍጥረታት በምግብና በልብስ በመጠለያ አማካኝነት እንዲሚኖሩ ሁሉ ሰማያውያን ፍጥረታት መላእክትም እግዚአብሔርን በማመስገንና ለታላቅ ስሙ ምን ጊዜም በመስገዳቸው እንደምግብ፣ ልብስና መጠለያ ሁኖአቸው ለዘለዓለም ይኖራል ፤

ስለዚህም ነበር ታላቁ ነቢይ ኢሳይያስ «እግዚአብሔር በረጅምና ከፍ በአለ ዙፋን ተቀምጦ አየሁት ሱራፌልም በዙሪያው ቁመው ነበር ። - - - - አንድም ለአንዱ ቅዱስ ቅዱስ ቅዱስ የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር ምድር ሁሉ ከክብሩ ተሞልታለች» እያሉ ሲአመሰግኑ በመንፈስ እግዚአብሔር ተገልጾለት በመጽሐፈ ትንቢቱ ላይ የዘገበው ይገልጻል (ኢሳ ምዕ ፮-፩—፮።)

ቊጥር በማይወስናቸው ሰማያውያንና ምድራውያን እልፍ አእላፍ ፍጥረታት እንደቤት ለዘለዓለም ሲመሰገንና ሲመለክ የሚኖር እግዚአብሔር አምላክ አስቀድሞ በነቢያት ያናገረውን ዓለምን ከኃጢአት መርገም ለማዳን የተስፋ ቃል ለመፈጸም ሲል በብሥራተ መልአክ ከሰማየ ሰማያት ወርዶ ከቅድስት ድንግል ማርያም ከሥጋዋ ሥጋን ከነፍሷ ነፍስን ነሥቶ ሰው ሆኖ በተወለደባት ዕለት የሰማያውያንና የሥጋውያን ደምፅ በአንድነት ተሰምቷል ።

የምሥጋናውም ቃል ስብሐት ለእግዚአብሔር በሰማያት ወሰላም በምድር ሥምረቱ ለሰብእ ክብር



ዘከመ ተወልደ እግዚእነ በቤተ ልሔም

ለእግዚአብሔር በአርያም ፣ ይሁን፣ ሰላምም በምድር ለሰውም በጎ ፈቃድ (ሉቃ ፪፣፲፫—፲፬)በማለት የሰው ልጆችና መላእክት በአንድነት ሁነው በተመረጠችው ቤተ ልሔም የተወለደውን ሕጻን ክርስቶስን አመስግነዋል ።

ስለዚህም ነበር ታላቁ ኢትዮጵያዊ ሊቅ ቅዱስ ያሬድ በመንፈስ ቅዱስ አለባዊነት ሲዘምር «ዮም አሐደ መርዔተ ኮኑ መላእክት ወሰብእ ከመ ይሰብሕዎ ለክርስቶስ በቃለ አሚን» ዛሬ ሰውና መላእክት አንድ ወገን ሆኑ በሃይማኖታዊ ቃል ክርስቶስን ያመስግኑ ዘንድ በማለት የሰውና የመላእክትን የምሥጋና አንድነት በጣዕመ ዝማሬው ላይ አውስቶአል ።

ብዙዎች ጌታ በተወለደባት ዕለት በቤተ ልሔም ዙሪያ «ስብሐተ እግዚአብሔር የተሰማው ከሰዎችና ከመላእክት አንደበት ብቻም አልነበረም ከእንስሳትም የምሥጋና ድምጽ ተሰምቷል» ወአስተማወቅዎ እስትንፋሰ አድግ ወላህም በመዋዕለ ቊር ወአስሐትያ «ላሞችና አህዮች በውርጭ ጊዜ በበረት የተወለደውን ሕጻኑ ክርስቶስን አሟሟቁት በማለት እንደሰዎች መነጋገር የማይችሉት ጌታ በተወለደበት በረት የነበሩት እንስሳት ማለትም ላሞችና አህዮች ፈጣሪያቸው እየሱስ ክርስቶስ በእስትንፋሳቸው አሟሟቂነት ማለት እስትንፋሳቸውን ገበሩለት አመሰገኑት ሲል ሊቁ አባ ሕርያቆስ በደረሰው በቅዳሴ ድርሳኑ ላይ የመዘገበውን ማሥረጃ እናገኛለን።

ከዱር እንስሳት እንደ ሚዳቋም ተወልደ መድኃኔ ዓለም ዮም ተወልደ ኮኩቤ ብርሃን የዓለም መድኃኒት ዛሬ ተወለደ የብርሃናት ገላጭ ተወለደ ብላ ጌታ በተወለደበት ዕለት እንደዘመረች ከቤተ ክርስቲያን ሊቃውንት እንደበትና ከልዩ ልዩ ቅዱሳት መጻሕፍት እንረዳለን

ስለዚህ በሁሉም ፍጥረታት አንደበት መመለክና መመስገን የባሕርዩ የሆነውን እግዚአብሔር አምላካችን ከቂምና ከበቀል እንዲሁም ከተንኮልና ከልዩ ልዩ ነውረ ኃጢአት ነጻ በመሆን ምንጊዜም እናመስግነው ።

መ/ኤፍሬም በየነ



# ወደ ጥምቀተ ባሕር እንሂድ

የመሄጃ መንገድ ሲባል አውሬና ከብት የሚሄድበት ስላች ወይም ሥርጥ መንገድ አለ ። መነሻ እንጂ መድረሻ ስለሌለው አሳስቶ ወስዶ በረሃ ይጥላል ፤ ለቀማኛ ይዳርጋል ፤ የአውሬ እራትም መሆን አለ ። ክርስቶስ ወደተጠመቀበት ወደ ዮርዳኖስ የሚወስደው መንገድ ግን የተስተካከለ አውራ መንገድ ከመሆኑም ሌላ ሰተት አድርጎ ወስዶ ከአሰቡት ያደርሳል ። ክርስቶስ በሚያስተምርበት ጊዜ እኔ እውነተኛ መንገድ ነኝ ብሏልና ።

በዚህ አንጻር በእያንዳንዱ አማኝ በኩል ወደጥምቀት የሚወስደውን መንገድ ሆነ ሥርዓት ያየን እንደሆን የተለያየ ሆኖ እናገኘዋለን ። የብሉይ ኪዳን ጥምቀት ከሥጋዊ ርኩሰትና እድፍ የሚያጠራ የንስሓ ጥምቀት ሲሆን በተጨማሪም ለጸሎትና ለስግደት ከመነሳታቸው በፊት በየቀኑና በየሰዓቱ መታጠብም ጥምቀት አለ ።

የኢ- ኦ- ተ- ቤ- በየዓመቱ ጥር ፲፩ቀን የምታከብረው ጥምቀት ግን ያልተጠመቁ ተጠምቀው የእግዚአብሐር ልጅነት እንዲያገኙ የተጠመቁ ደግሞ ነቢዩ ሕዝቅኤል ጥሩ ውሀ እረጭችኋለሁ ባለው መሠረት ካህናቱ ባሕረ ጥምቀቱን በጸሎት ባርከው በዓሉን ለማክበር የተሰበሰቡት ምእመናንም ጸበሉን ተረጭተው ጸጋና በረከት የሚያገኙበት ጥምቀት ነው ።

ጥምቀትም ማለት ከውኃ ውስጥ መጥለቅ ነው በክርስቶስ ሞትና መቃብር በትንሣኤ ይመሰላል ተጠማቂው በመጠመቁ መንፈስ ቅዱስ ከውኃና ከመንፈስ በመወለድ በሚሰጠው ጸጋ ይገለጻል ከኃጢአትና ከዓለም እንደተሰናበተ ይመሰክራል ። በዚህ ሁኔታ ጥምቀት ወደ ቤተ ክርስቲያን አባልነት የመጨመርን ሁኔታ ያመለክታል (ማቴ ፳፰ ፡ ፲፱ ።)

ማንኛውም ተጠቃሚ የሆነ ሁሉ ከውኃና ከመንፈስ ተወልዶ የቤተ ክርስቲያን አባል መሆን ሲፈልግ ወደ ቤተ ክርስቲያን ሂዶ በምስክሮች ፊት ሥርዓተ ጥምቀትን ይፈጽማል ። የምንፈጽመው ሕግ ነው ያረጀውን የኃጢአት ሕይወት ካረጀው ባህርይ ጋር መቅበራችንን ለዓለም መመስከራችን ነው ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስን መድኃኒታችን አድርገን መቀበላችንና ካለፈው ኃጢአታችን ሁሉ ንስሐ መግባታችን በእግዚአብሔርና በሰው ፊት ማረጋገጣችን ነው ።

በጥምቀት ባረጀው ባህሪያችን ሞትን በውኃ ውስጥ መቀበራችንን እናሳያለን በዚህ ጊዜ ያረጀው ሕይወት በግልጽ ተወግዶ አዲስ ሕይወት ይተካል እንደዚህ ሆነን ስንቀበር ሳለ ትንፋስን እንቆርጣለን ላለፈው የሞትን ስለሆነ ከውኃ ውስጥ ስንወጣ እንደገና እንተነፍሳለን ከዚህ በኋላ አዲስ ሕይወት እንጀምራለን መንፈስ ቅዱስ ባህርያችንን ይለውጣልና ቅዱስ ጳውሎስ ጥምቀት በእኛ ፈንታ የሞተውንና የተነሣውን የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስን ሞትና ትንሣኤ መቀበላችንን የምንመሰክርበት መሆኑን ይነግረናል ።(ወይስ አታውቁምን እኛ በኢየሱስ ክርስቶስ የተጠመቅን በሞት እንደ ተጠመቅን እንዲህ ከእርሱ ጋር ተቀበርን ከሞት ክርስቶስ እንደ ተነሳ በአብ ክብር እንደተቀመጠ እንዲሁ እኛም ደግሞ በአዲስ ሕይወት ወደ ክብሩ እንሄድ ዘንድ ነው (ሮሜ ፯ ፣ ፫፣ ፬) ወደዚህ ክብር እንዲሄዱ ሰዎች ከሕጻንነት ወራት መጠመቅ ያስፈልጋቸዋል ። በቀድሞ ዘመን በሕንድ አገር ትንሽዋ ሕጻን ልጃገረድ ለአንድ እንግዳ በስድስት ወሯ ትታጭ ነበር ከዚያ በኋላ በአሥርና በአሥራ አምስት ዓመት መካከል እጮኛዋ ወደ ነበረው ባሏ ትሄድ ነበር ። ይህም እጅግ በጣም አሳዛኝና ከሥን



ዘከመ ተጠምቀ እግዚእነ
በፈለገ ዮርዳኖስ በእደ ዮሐንስ

ሥርዓት ውጭ ነበር ። በዚህ አኳኋን እንዲህ ያሉ ትናንሽ ልጃገረዶች ለማደግና የራሳቸውን ምርጫ ለማድረግ ዕድል አልነበራቸውም ማለት ነው ጋብቻ ነው እንጂ በህጻንነት ወራት መፈጸም የማይገባው ጥምቀት ግን በሕጻንነት ወራት የወንድ በ፵ ቀን የሴት በ፹ቀን ሊፈጸም ይገባል ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስም የሚቀበለው በዚህ መንገድ ነው ። አንዳንድ የሃይማኖት ድርጅቶች ግን ይህንን በመቃወም ሕጻናት ካደጉ በኋላ ዕድሜያቸው ሲፈቅድ አምነው ከመጠመቅ በፊት መጽሐፍ ቅዱስን ትምህርትና ጸሎት በሚገባ ማወቅ አለባቸው ይላሉ ይህንንም የሚሉበት ዋናው ምክንያት ፈጣሪያቸውን አውቀው ቃሉን ለመወደድና ለማክበር እምነታቸውንም ሆነ ምግባራቸውን ለማጽ



www.ethiopianorthodox.org

ናት ይችላሉ በማለት ነው ይህም
ሲባል ታዳጊ የሆኑት ሕጻናት በአ
ሥር ወይም በአሥራ ሁለት ዓመት
እድሜያቸው መጽሐፍ ቅዱስን
በግልጽ አስተውለው በራሳቸውም
ቁርጥ ሀሳብ አድርገው ለመጠመቅ
ይችላሉ የሚል አስተሳሰብ ስላላ
ቸው ነው ።

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋ
ሕዶ ቤተ ክርስቲያን ግን ክርስቶስ
ሕጻናትን ተዋቸው ወደኔ ይመጡ
ዘንድ ባለው መሠረት በልጅነታ
ቸው ሳይጠመቁ እስኪያድጉ ድረስ
ከቆዩ ዕዳ በደሉ በማን ይሆናል?
በማለት ይህንን በመቃወም የመ
ጀመሪያዎቹ ሊቃውንት የወሰኑት
ንና ፫፻፲፰ ቱ ሊቃውንት በአን
ቀጸ ጥምቀት የደነገጉትን ድንጋጌ
በመከተል ወንዶችን በ፵ ሴቶችን
በ፹ ቀን ታጠምቃለች ይህም
የቤተ ክርስቲያናችን ሥነ ሥርዓት
ሆኖ ሲፈጸም ኖሯል ። ወደፊትም
ሲፈጸም ይኖራል ይህም የሚፈ
ጸመው ጥምቀት ለማዳን አስፈ
ላጊ ሆኖ በመገኘቱ ነው ይኸውም
ክርስቶስን ለበስን ማለት የእርሱን
ሕይወት የእኛ አድርገን መቀበላ
ችንና ምሳሌውን እንደተከተልን
ያሳያል ጥምቀት ከጌታችን ከኢየ
ሱስ ክርስቶስ ጋር ለመኖርና በግ
ልጽ ከርሱ ጋርና ከቤተ ክርስቲያኑ
ጋር መተባበራችንን ለዓለምና ተከ
ታዮች ጠቃሚ መሆኑን የሚያሳይና
ጥምቀት የተቀደሰ ሥነ ሥርዓት
መሆኑን ለመግለጽ ነው ።

ይሁን እንጂ ጥምቀት ከእምነ
ትና ከምግባር ጋር ካልሆነ ብቻ
ውን አያድንም በተጨማሪም ማ
ንም ሌሎችንም ሆነ የመጽሐፍ
ቅዱስን ትምህርት ቢከተል የጥ
ምቀትን ጠቃሚነት እያወቀ ሳይ
ጠመቅ ቢቀር እርሱ የጥፋት ልጅ
ነው ። ለዚህም መረጃ የሚሆነን
በ፫ኛው መቶ ዓመት ግድም በቈ
ስጠንጢኖስ ዘመነ መንግሥት የነ
በሩ አንዳንድ ሰዎች በይበልጥም
ሀብታሞች መጠመቅ ሞትን ያመ
ጣል እያሉ ይፈሩ ነበር ። ከዚህም
የተነሣ በአልጋቸው ላይ ሆነው
እስከ ጊዜ ሞታቸው ለመጠመቅ
ይዘገዩ ነበር ። ከዜና መዋዕሉ
እንደምንረዳው ቈስጠንጢኖስ እን
ኳን ሳይጠመቅ እንደቆየ እናገኛለን
ከጥምቀት ጊዜ በኋላ ደግሞ ሳን
ጠመቅ የሞትን እንደሆነ ይፈረ
ድብናል እያሉ ስለፈሩ ካህኑ እን
ዲያጠምቃቸው በየቤታቸው ይጠ
ሩት ነበር ካህናቱም ሞትን እንዳ
ይፈሩ በማለት በሚያጠምቋቸው
ጊዜ በራሳቸው ላይ ጨርቅ ጠም
ጥመው ውሃ በላያቸው ያፈሱባ
ቸው ነበር ። ይህንንም ጥምቀት
እያሉ ይጠሩት ነበር እነሱ ይበሉት
እንጂ እውነተኛ ጥምቀት ግን አይ
ደለም ።

ጥምቀት ማለት ምን ማለት
ነው? ተብሎ እንደ የግሪክ ካህን
ቢጠየቅ ከውሃና ከመንፈስ ተወ
ልዶ የእግዚአብሔር ልጅ ለመ
ሆን በውሃ ውስጥ ብቅ ጥልቅ
እያሉ መጠመቅ ነው ይህም ማለት
እንደ ነጭ ልብስ በቀይ ቀለም
ውስጥ ሲነከር ቀይ ሆኖ እንደሚ
ወጣ ማለት ነው ብሏል ። በመሆ
ኑም ጥምቀት የእእምሮና የልብ
ሰላም የሚቀበሉትን ምእመናን ያበ
ረክታል በዚህ ሁኔታ በመንፈስ
ቅዱስ ኃይል ለተሰጠው እውነ
ተኛ የመፈወስ ስጦታ ሙሉ ትም
ህርት ይሰጣል ጥምቀት አማናዊ
የሆነውን ከሥላሴ ልጅነትን
ያሰጠናል ። ጌታችን ኢየሱስ ክር
ስቶስ ሕዝብን ለማዳን በፈጸማ
ቸው መልካም ሥራዎች መካከል
አንደኛው ከውሃና ከመንፈስ ተወ
ልዶ የእግዚአብሔርን መንግሥት
ማየት ነው ።

ለምሳሌ ፤— ማንኛውም ልጅ
ሁሉ ለመሄድ በእግሩ መራመድ
ያስፈልገዋል ፤ ይህንንም ለማ
ወቅ ብንሻ ሕጻናት እየተውተረ
ተሩ ለመራመድ ሲሞክሩ እናያ
ለን ይሁን እንጂ አሁንም ይወ
ድቃሉ ቢወድቁም ተስፋ ሳይቆ
ርጡ እንደገና እያለቀሱ ይራመ
ዳሉ ። ክርስቲያንም እንደነዚህ
ሕጻናት ወደ ክርስቶስ በሚራመ
ድበት ጊዜ ብዙ ጊዜ ይወድቃል
ይነሳል ግን ተስፋ ሳይቆርጥ በተ
ጠመቀው በጥምቀት ኃይል በን
ስሐ እያለቀሰ በእምነት ጸንቶ ወደ
ክርስቶስ መራመድ አለበት እንጂ
ተስፋ መቁረጥ የለበትም ስለዚህ
ማንኛውም አማኝ የሆንን ሁሉ
ከወደቅንበት እንነሣ ወደ ጥም
ቀተ ባሕሩ እንሂድ የመንፈስ ተሐ
ድሶ የሚሰጠን ጥምቀት ነውና ።

አለቃ ነቢየ ልዑል ዮሐንስ



# በሦስተኛው ቀን በቃና ሠርግ ነበር ።

ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ
ክርስቶስ ከቅድስት ድንግል ማር
ያም ሰው ሆኖ ሥጋን ለብሶ ተወ
ልዶ በዚህ ዓለም ፴፫ ዓመት ከ፫
ወራት ከኖረ በኋላ ተሰቅሎ ሞቶ
በሞቱ ሞትን ደምስሶ በመነሣት
ለእኛ ለሰው ልጆች ዘለዓለማዊ
ድኅነትን እንዳጎናጸፈን እናምናለን
ክርስቶስ ከልደቱ ጀምሮ እስከ
ዕርገቱ ድረስ የሠራቸው ተአምራት
በጠቅላላው በቅዱሳት መጻሕፍት
ቢመዘገቡ ለመመዝገብ (ቢሞከር)
ደቂቀ አዳም ጸሐፍት አብሕርት
ቀለማት ሰማይና ምድር ወረቀቶች
ሆነው ቢጻፉ እንኳን ባልበቁም
ነበር ።

ቢሆንም አልፈው ለምልክት
ያህል መመዝገባቸው አልቀረም ፤
ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ
ክርስቶስ በላሞች በረት በተ
ወለደ ጊዜ ሰብአ ሰገል በኮከብ
እየተመሩ ከምሥራቅ ሀገር ወደ
ተወለደበት ቤተ ልሔም ደረሱ ፤
ክርስቶስ ከተወለደበት ቦታ ከደ
ረሱ በኋላ ይመራቸው የነበረው
ኮከብ ቀጥ ብሎ ቆመ ሰብአ ሰገል
በዚያው ቦታ ሕጻኑን ኢየሱስን
ከእናቱ ድንግል ማርያም ጋር ስላ
ገኙት ያመጡትን ወርቅ ዕጣንና
ከርቤ ሰጥተው ደስ እያላቸው
ተመለሱ ።

የአይሁድ ንጉሥ ተወለደ የሚ
ለው ዜና ያስደነገጠው የዘመኑ
ገዥ ሄሮድስ ሰብአ ሰገልን ከመ
ንገድ አግኝቶ ስለተወለደው ሕጻን
ጠይቆ ከተረዳ በኋላ ጠይቀው በ
ሚመለሱበት ጊዜ ያለበትን ቦታ
እንዲነግሩት አግዟኖ ሰዶአቸው፤
ነበር ። ነገር ግን መልአከ እግ
ዚአብሔር በሌላ መንገድ እንዲ
ሄዱ ስለአዘዛቸው በሌላ መንገድ
ተመልሰው ወደሀገራቸው ገቡ ።
ሄሮድስ ሳይነግሩት መሄዳቸውን
ከተረዳ በኋላ እስከ ሦስት ዓመት
ያሉትን ሕጻናት አሰባስቦ በሰ
ይፍ አሳረዳቸው ፤ እንደ እርሱ
አስተሳሰብ ጌታችን መድኀኒታችን
ኢየሱስ ክርስቶስ ከሕጻናቱ መካ
ከል አንዱ ሳይሆን አይቀርም መስ
ሎት ነበር ፤ ነገር ግን በመላኩ
አብሣሪ ነት እናቱ ድንግል ማር
ያም በሌሊት ይዛው ወደ ግብጽ
ስለተሰደደች የሄሮድስ ሰይፍ ሕጻ
ኑን ሊያገኘው አልቻለም በስደ
ትም ፫ ዓመት ከ፮ ወራት ኑሯል
በስደት ላይ በቆየበትም ጊዜ እንደ
ሰው ልጆች ረሀብ ድምፅ የሌሊት
የመዓልት ሐሩር ተፈራርቀው
በታል ፤—ከኃጢአት በስተቀረ
ሰው የሚሠራውን ሁሉ ሠርቷል
በሰው ላይ የሚደርሰው ችግርም
ደርሶበት በትዕግሥት አሳልፎታል፤
አንዳንድ ጊዜም ተአምራትን
ያደርግ ነበር ፤— ለምሳሌ በኃ
ይል የተጋፉትን ተንኰለኞች በ
ሞት ቀጥቷቸዋል ፤ የሚጠጡትን
ውኃ እንዲመር የሚመገቡትም በረ
ከትና ጣዕም እንዲነሣው ያደረ
ገበት ጊዜም አለ ፤—ሌሎችንም
ተአምራት ማድረጉ በቅዱሳት መጻ
ሕፍት ተጽፏል ።

ልዩ ልዩ ተአምራትን እየፈጸመ
ችግርንና መከራን እየተቀበለ እን
ደሰው ካደገ በኋላ ፴ ዘመን ሲሞ
ላው የዘካርያስ ልጅ ዮሐንስ ወደ
አለበት ሂዶ በአንተ እጅ ለመጠ
መቅ እሻለሁና አጥምቀኝ አለው
ዮሐንስ ግን እኔ ከአንተ ለመጠ
መቅ እፈልጋለሁ እንጂ አንተን
ለማጥመቅ እንዴት ይቻለኛል?በ
ማለት እንቢ አለው ፤— ጌታችን
መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ
መልሶ የተነገረውን እውነተኛ ትን
ቢት መፈጸም ይገባናል ፤ አንተ
እኔን አጥምቀህ መጥምቀ መለኮት
እየተባልክ ዝናህ ሲነገር ይኖራል ፤
እኔም በአንተ እጅ ተጠምቄ በባ
ሪያው እጅ ተጠምቀ እየተባለ ትሕ
ትናዩ ሲነገር ይኖራል ፤— ባለው
ጊዜ ዮሐንስ ከፈጣሪው ከኢየሱስ
ክርስቶስ ትእዛዝ ሸሽቶ የሚያመ
ልጥበት መንገድ አላገኝም ።

ስለዚህ ሌላውን በአንተ ስም
አጠምቃለሁ አንተን በማን ስም
ላጠምቅህ እችላለሁ ሲል ጠየቀው
ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ
ክርስቶስም «ወልዱ ለቡሩክ ከ
ሣቴ ብርሃን ተሣሃለኒ» እያልክ
አጥምቀኝ አለው ዮሐንስም የፈ
ጣሪውን ቃል ተቀብሎ ወደ ፈለገ
ዮርዳኖስ እጅ ለጅ ተያይዘው ወረ
ዱና አጠመቀው ጌታችን በሚጠ
መቅበት ጊዜ አብ በደመና ሆኖ
ይህ የምወደው የምወልደው ልጄ
ነውና ስሙት ብሎ ሲመሰክር ፤
መንፈስ ቅዱስ በርግብ አም
ሳል ወርዶ ከራሱ ላይ ተቀም
ጧል በዚህ ጊዜ የአንድነትና
የሦስትነት ምሥጢር ተገልጿል ፤
—ሁልጊዜ የምንመለከታቸው በት
ምህርት መልክ ነው ትምህርትና
ተአምራት እጅግም የተራራቁ አይ
ደሉም ዋናው ቁም ነገር ከልብ
አስተውሎ ከመመልከቱ ላይ
ነው ።

ወደተነሣንበት ርእስ እንደገና
መለስ ብለን እንመልከት ጌታ
ችን የተጠመቀው ማክሰኞ ቀን
ነበር ከተጠመቀ በኋላ አልዋ
ለም አላደረም ዕለቱን ወደገ
ዳም ሄዶ ፵ ሌሊትና ፵ መዓ
ልት ጾምአል ዓርባው ቀን ቅዳሜ
ይፈጸማል እሁድ ገብቶ ያድራል
ዓርባውን ቀን እንደ አንድ ቀን
አድርጎ ሳኒታ እሰው ሦስተኛ ቀን
ማለት ነው ማክሰኞ ሣልስነቱ
ለእሁድ ሳኒታ ነቱ ለሰኞ ይሆ
ናል ።

በሦስተኛው ቀን (ዕለት) ሠርግ
ነበር ብለን ከመነሻው የገለጽነ
ውም ይህንን መሠረት በማድረግ
ነው የሠርጉ ድግስ የተዘጋጀው
በገሊላ አጸ ክፍል በቃና ሲሆን
በሰርጉም እምመቤታችን ድንግል
ማርያም ተገኝታለች ቤተ ዘመድ
ናትና ተጠርታ ነው ጌታችን መድ
ኃኒታችን ኢየሱስ ም ከደቀ መዛ
ሙርቱ ጋር ስለተጠራ ተገኝቶ
ነበር ። የተጠራው ሕዝብ ተሰ
ብስቦ ሲመገብ ሳለ የጠጁ አለቃ
በዚያን ጊዜ የሠርጉ ባለቤት በጣም
ደንግጦ ሲጨነቅ ድንግል ማር



www.ethiopianorthodox.org

ያም የሰውን ልጅ ክብሩን እንጂ ውርደቱን ደስታውን እንጂ ኀዘኑን አትወድምና ለልጅዋ ለጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ጠጅ አልቆባቸዋል እኮ አለችው ክርስቶስ የማያውቅ ሆኖ አይደለም ሥራውን የሚሠራበት ጊዜ ስላለው ነው እንጂ «ጊዜ ገቢር ለእግዚአብሔር» እንዲል በነግህ የሚሠራውን በሠለስት በሠርክ የሚሠራውን በነግህ አይሠራውምና በሌላ በኩል ደግሞ ጠጁ ፈጽሞ ስላለቀ ነው ፤ ያልተጨለጠውን አበርክቶት ቢሆን ኑሮ ያኑ አበረከተው ተብሎ ተአምራቱ እጅግ በጣም ባልተደነቀም ነበር ።

እመቤታችን ድንግል ማርያም ለአሳላፊዎች ያዘዘችሁን ሁሉ አድርጉ አለቻቸው በዚያም አይሁድ የሚጠምቁባቸው ስድስት ጋኖች ሲኖሩ ከእነርሱም ሁለት ሁለት ሦስት ሦስት እንስራ የሚይዙ ነበሩ ጌታችንም እነዚህን ጋኖች ውኃ ሙሏቸው ብሎ አዘዘና ከሞሏቸው በኋላ ቀድታችሁ በመጀመሪያ ለአሳዳሪው ስጡት አላቸው አሳዳሪውም ጠጁን ቀምሶ በጣም አደነቀ ሙሽራውን ዶኪማስ ብሎ ጠርቶ በመጀመሪያ መናኛውን ጠጅ ወደኋላ አስቀረህ በማለት ጠጅ የሆነውን መጠጥ አደነቀ ደቀ መዛሙርቱም አመኑበት ጌትነቱንም ገለጠ (ዮሐ - ፪፤ ፲፩) ።

ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከእናቱና ከደቀ መዛሙርቱ ጋር በሠርግ ቤት መገኘቱ ጋብቻ የተከበረ መሆኑን ለማስረዳት ነው በሠርጉ መገኘት ብቻ ሳይሆን ሙሽራው የተቸገረበትንም አሟልቶለታል በሕግና በሥነ ሥርዓት የሚዘጋጅ ጋብቻ በእግዚአብሔር ዘንድም የተፈቀደ ስለሆነ የጎደለው ይሞላል የተሰነካከለውም ይስተካከላል ።

እግዚአብሔር በሥነ ፍጥረት የፈጠረው አንድ ወንድና አንዲት ሴት ብቻ ነበር ፤ እነርሱም ብዙ ተባዙ ምድርንም ሙሏት ተብለው በታዘዙት መሠረት ምድርን ሞልተዋታል ፤ ይህ ተፈጥሮ ወንድና ሴት ተፈቃቅረው በመረዳዳት መኖር እንዳለባቸው የሚያስረዳ ነው፤ የእነርሱም መገናኛ ጋብቻ ስለሆነ ማንኛውም ተጋቢ ለጋብቻ ከፍ ያለ ክብርን መስጠት አለባት ሐዋርያው ጳውሎስ «መጋባት በሁሉ ዘንድ ክቡር መኝታውም ንጹሕ ነው፤ ሴሰኞችንና አመንዝራዎችን ግን እግዚአብሔር ይፈርድባቸዋል ።»

እንዳለው በሕግ ሳይወሰኑ የሚኖሩትን ሴሰኞች እግዚአብሔር በሥጋም በነፍስም ይፈርድባቸዋል በቃና ዘገሊላው ሠርግ ተገኝቶ ጋብቻን የባረከ አምላክ በሕግና በሥነ ሥርዓት ለመጋባት የተዘጋጁትን ሙሽሮች ጋብቻቸውን አሁንም ወደፊትም እንደሚባርክ እናምናለን ።

ሊ/ኅሩያን ልሳነ ወርቅ በዛብህ

## ሕፃኑ ሰማዕትና እናቱ

«እምአፈ ደቂቅ ወሕጻናት አስተዳሎከ ስብሐተ » ከሕጻናትና ከሚጠቡ ልጆች አፍ ምስጋናን አዘጋጀህ ተብሎ ቀደም ሲል በነቢዩ ዳዊት እንደተነገረው እግዚአብሔር ልጅ አዋቂ ሴት ወንድ ሳይባል በሁሉ አፍ ሲመሰገን ይኖራል ። ሆኖም አንድ የ፫ ዓመት ሕጻን ሲከፋው ማልቀስ ደስ ሲለው መጫወትና መቦረቅ እንጂ ስለጽድቅና ኩነኔ መናር አርቆ የማሰብ ችሎታ እንደሌለው በሁሉም ዘንድ የታወቀ ነው ።

ነገር ግን ሕጻኑ ቅስዱ ቂርቆስ በመንፈሰ እግዚአብሔር ተመርቶ ከእናቱ ቅድስት ኢየሉጣ ጋር የፈጸመውን የሰማዕትነት ታሪክ ስንመለከት በጣም የሚያስገርም ነው። ይኸውም ሕጻኑ ቅዱስ ቂርቆስ ገና የሦስት ዓመት ሕጻን ሳለ አርያኖስ የተባለው የሮም መኰንን ስለአምልኮት በጠየቀው ጊዜ በሰጠው መልስ የተፈረደበት ቅጣትና ተጋድሎ ነው ።

የቅዱስ ቂርቆስ እና ቅድስት ኢየሉጣ በሮም ግዛት ውስጥ በምትገኝ እንጌቤን በምትባል ቦታ የምትኖር ክርስቲያናዊት ሴት እንደነበረች ገድሏ ያስረዳል ። በዘመነ ሰማዕታት አምልኮተ ጣኦት የተስፋፋበት ፤ ክርስቲያኖች የሚሰቃዩበትና የሚሰደዱበት ዘመን ስለነበረ ኢየሉጣም ከሮም ተሰድዳ ነበር ። መኰንኑም በሄደችበት ቦታ ሁሉ እየተከታተለ ያሳድዳት ነበር ። በተለይም ሕጻኑ ልጅዋን በተለያዩ ቅጣቶች እያስፈራራ ጣኦት እንዲያመልኩና እግዚአብሔርን እንዲክዱ አስገደዳቸው ።

ሕጻኑ ቂርቆስ ግን እግዚአብሔር በገለጸለት መንፈሳዊ ጥበብና ኃይል በረታ እንጂ ፍርኀትና ድንጋጤ አልተሰማውም ። ምንም ሳያፍር በአደባባይ ላይ ተነሥተው ሰማይንና ምድርን ፍጥረታትንም ሁሉ በፈጠረ አንድ አምላክ እንጂ በሰው እጅ ለተሠሩ ጣኦታት መስገድም ሆነ እነሱን ማምለክ አይገባም በማለት ስለክርስቶስ በሰፊው መሰከረ አማልክትንም ረገመ» ንግግሩንም የሰሙ ሁሉ ከማድነቅና ከመገረም አልፈው ፈሩ ።

መኰንኑም የሕጻኑ ንግግር የሚስብና የሚያሳምን መሆኑን አይቶና እሱ የሚያመልካቸውንም ጣኦታት ስለአዋረደበት የእርሱም ክብር አብሮ እንደተዋረደ በተረዳ ጊዜ ሕጻኑና እናቱ በእሳት ተቃጥለው እንዲሞቱ አዘዘ ፤

ሕጻኑ ቂርቆስ ግን «ጥብአኬ እም ወኢትናፍቂ » እናቴ ሆይ ጨክኚ አትጠራጠሪ ዛሬ ፈጣሪያችን ክደን ዘለዓለም ስንቃጠል ከምንኖር ዛሬ አንድ ጊዜ ሞተን በመንግሥተ ሰማያት ለዘለዓለም ሕያው ሆነን ብንኖር ይበልጣል ። ሥጋችንን እንጂ ነፍሳችንን አያቃጥሏትም ፤ በማለት አጽናናት «ሥጋንም የሚገድሉትን ነፍስንግን መግደል የማይቻላቸውን አትፍሩ ይልቅስ ነፍስንም ሥጋንም በገሃነም ሊያጠፋ የሚችለውን ፍሩ» (ማቴ ፲ ፡ ፳፰ ።)

ከዚህም በኋላ ፈጣሪያቸውን የማይክዱ ለጣኦትም የማይሰግዱ ሆነው በመገኘታቸው ወደነደደው እሳት ተጨመሩ ። በዚህም ጊዜ መልአኩ ቅዱስ ገብርኤል ደርሶ እሳቱን ሲባርከው ሊያቃጥላቸው አልቻለም እንደውሃ ቀዘቀዘላቸው ሥጋቸውን ቀርቶ ልብሳቸውን እንኳ አልነካም ። ይኸንንም ከተመለከቱት ሕዝብ ብዙዎቹ በእግዚአብሔር አመኑ ። ከአመኑትም ውስጥ የቅዱስ ቂርቆስንና የቅድስት ኢየሉጣን አርአያነት በመከተል በእምነታቸው ጸንተው ስለክርስቶስ በመመስከር በሰማዕትነት ሕይወታቸውን በማሳለፍ የጽድቅ አክሊሉን ተቀዳጅተዋል ።

ይህ ብቻ ሳይሆን ቅዱስ ቂርቆስና ኢየሉጣ የተለያዩ ሥቃያትን ሲቀበሉ ቆይተው በመጨረሻ ወደ እግዚአብሔር በመጸለይና ቃል ኪዳን በመቀበል በአረማውያን እጅ አንገታቸውን በመሰየፍ አርፈዋል ። ጥር ፲፭ ቀን በየዓመቱ የቅዱስ ቂርቆስ ቤተ ክርስቲያን ባለበት ቦታ ሁሉ በታላቅ ድምቀት ሲከበር የሚኖረውም ይህንኑ የዕረፍቱን ዕለት መታሰቢያ በማድረግ ነው ። ስለዚህ ይህንን ዕለት በማሰብ የሚያከብሩ ክርስቲያኖች ሁሉ የቅዱስ ቂርቆስና ቅ-ኢየሉጣ በረከትን እንደሚካፈል በተሰጣቸውም ቃል ኪዳን መሠረት በአማላጅነታቸው ዘለዓለማዊ ሕይወትን እንደሚወርሱ በማይሻር ቃሉ አረጋግጦላቸዋል ።

ወርቅ በእሳት ተፈትኖ ጥራቱ እንደሚታወቅ ሁሉ ሰማዕታትም በእሳትና በስለት ተፈትነው የወንጌል ምስክሮች በመሆናቸው ፀስበ ተጋድሎአቸውን የክብር አክሊል ተቀዳጅተዋል ክርስቲያኖችም እውነተኛ ክርስቲያን መሆናቸው የሚረጋገጠው በሥጋዊ ጥቅም የማይታለሉ በገንዘብና በወገን ተደልለው በሐሰት የማይመሰክሩ በእውነት የሚፈርዱ ለማንኛውም ወገንና ሀገር ፍቅር ያላቸው በሕገ እግዚአብሔር የጸኑና ማንኛውም ችግር በደረሰባቸው ጊዜ የማይለወጡ ሲሆኑ ነው ።

በዚህ ዓይነት ተጋድሎ ቅዱሳን አባቶች ያቆዩትን በክብር ተቀብሎ መጠበቅ የማንኛውም ክርስቲያን ተግባር ነው ። ይህ ዓይነቱ የሃይማኖት ጽንዓት ለሁሉም ያስፈልጋል ። ለሞት የሚያደርስ ፈተና ቢደረስብን እንኳ በተስፋ እግዚአብሔርን ከለመን ነው ችግራችን ሁሉ መልአኩን ልኮ እንደሚያቀዘቅዝልን ከነዚህ ቅዱሳን መማር ይገባናል ።

መ/መንክር ዋሴ

## ሞት በጥር ፤ በነሐሴ መቃብር ።

እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም በእግዚአብሔር የተመረረጠች ነቢያትም ትንቢት የተናገሩላት የአምላክ እናት ብትሆንም ሥጋ ለባሽ ሁሉ«መሬት አንተ ወትገ ብር ውስተ መሬት»መሬት ነህና ወደ መሬት ትመለሳለህ ተብሎ በተፈረደበት ፍርድ መሠረት

እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያምም የዚህ የሞት ጽዋዕ እንድትቀምስ የእግዚአብሔር ቅዱስ ፈቃድ ሆነ ፤

ደግም ይሁን ክፉ ጻድቅም ይሁን ኃጢአተኛ ሁሉ ከዚህ ከሞት ጽዋ እንደማይላቀቅ በአምላካዊ ቃል የተነገረና የተረጋገጠ ነው የሕይወት መሠረት የሚል ቅጽል የተቀጸለላት የርእስ ሕይወት እናት የሆነችው እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም በዚች በጥር ፳፩ ቀን ከዚህ ዓለም ወደ ወዲያኛው ዓለም የተሸጋገረችበት ዕለትና ከዚህም ቀንና ሌሊት ብርሃንና ጨለማ በጋና ክረምት እየተፈራረቁበት ከሚኖረው ዓለም የተለየችበት ቀን ነው ።

ስለ እመቤታችን ዕረፍት ያል ተደነቀ ስለ እመቤታችን ከዚህ ዓለም መለየት ያልተገረመ ሰው አልነበረም ።

ምክንያቱም አምላክን የወለደች እንዴት እንደ አንድ ተራ ሰው የሞትን ጽዋዕ ትቀምሳለች በሚል ሐሳብ ነው ።

እንዲያውም አንድ ሊቅ የእመቤታችንን ዕረፍት በማስመልከት ሞትሰ ለመዋቲ ይደሉ ሞታ ለማርያም የአጽብ ለኵሉ ፤

ሞትስ ለመዋች ይገባል የማርያም ሞት ግን ሁሉን ያስደንቃል በማለት በአድናቆት ገልጾአል ።

ሞት በጥር በነሐሴ መቃብር የተባለበትም ዋና ምክንያት እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም በቅዳሴ መላእክት በውዳሴ መላእክት በመዓዛ ገነት ቅድስት ነፍስዋ ከሥጋዋ የተለየችበት ቀን ጥር ፳፩ ቀን ነበር ።

ይሁን እንጂ ያን ጊዜ ቅዱሳን ሐዋርያት እንቀብራታለን ብለው በአጎበር ተሸክመዋት ሲሄዱ የምቀኝነት ባለቤቶች የተንኮል አበጋዞች ሕዝበ አይሁድ በተንኮል ተነሣሥተው ንዑናው እያምነለ ዓራታ እንሆ ከዚህ በፊት እርስዋ የወለደችው ክርስቶስ ሞተ ተነሣ ዓረገ እያሉ እስከ ዛሬ ድረስ እነዚህ ደቀ መዛሙርት እኛን ሲያውኩ ከተሞቻችንን ሲረብሹ ቆይተው ነበር እሱ አልበቃቸው ብሎ አሁንም ድንግል ማርያምን ሊቀብሩ ይዘዋት ይሄዳሉ ፡ ስለዚህ እስዋንም





www.ethiopianorthodox.org

ምቶች ተነሣች ዓረገች እያሉ እንዳያውኩን ኑ ከአልጋዋ ጋር እናቃጥላት ብለው መከሩ ።

መከረውም አልቀሩም ከእነሱ መካከል ታውፋንያ የሚባል ተራምዶ ከሐዋርያት ትከሻ ላይ አልጋውን እገለብጣለሁ ብሎ እጁን ሲዘረጋ ከእስዋ የማይለየው መልአኩ ቅዱስ ገብርኤል በያዘው የእሳት ሰይፍ ሁለቱን እጆቹን ቀጣው

በዚህ ጊዜ የታውፋንያ እጆች ተንጠልጥለው ቀሩ እሱም አሰምቶ ጮኸ በበደለውም በደል ተጸጽቶ በድያለሁ ይቅር በይኝ ብሎ ወደ እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ቢያመለክትና ከእስዋ ምሕረትን ቢማፀን እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ሰው የሚድንበትን እንጂ ሰው የሚጠፋበትን ነገር ስለ ማትሻ የተቆረጡትና በመልአኩ በቅዱስ ገብርኤል ሰይፍ ተቆርጠው ተንጠልጥለው የነበሩትን እጆቹን መለሳ አድነዋለች ።

ወድያውኑ ወንጌላዊው ዮሐንስ ጩምሮ መልአኩ እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያምን በደመና ነጥቆ በገነት መካከል በሚገኘው በዕፀ ሕይወት ሥር እንድትቆይ አደረገ ። ሕስከ ነሐሴ ድረስ ከቆየች በኋላ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ እርሱ የቀመሰውን የመቃብር አፈር እንድትለብስ ፈቃዱ ስለነበረ ነሐሴ ለሐዋርያት ሰጥቷቸው ጌቴ ሴማኒ በተባለው ቦታ ቀብረታል ሞት በጥር በነሐሴ መቃብር የተባለበትም ከዚህ የተነሣ ነው ።

የእመቤታችን ዕረፍት እንደማንኛውም ሰው ዕረፍት አልነበረም ሌሎች ሰዎች ነፍሳቸው ከሥጋቸው ስትለይ በየር በጋር በድካም ነው የእመቤታችን ዕረፍት ግን ከዚህ የተለየና የማይመሳሰል ነው ምክንያቱም እመቤታችን ከዚህ ዓለም ስትለይ በመዓዛ ገነት ተመስጣ በቅዳሴ መላእክት እነ ቅዱስ ዳዊት በበገና እነ ነቢዩ ዕዝራ በእንዚራ ቅዱሳን መላእክትም በቀኝ በግራ በፊት በኋላ እየዘመሩ ነውና

ከዚህም ሌላ ሌሎች ሰዎች በሚሞቱበት ጊዜ በውድ ሳይሆን በግድ ነው ከዚች ምድራዊትዋ ዓለም የሚለዩት እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ግን ከልጅዋ ከወዳጅዋ ከክርስቶስ ጋር ለመኖር ከዚህ ዓለም ተለይቼ መሄድን እናፍቃለሁ በማለት በውድና በፈቃድ ነው ።

ስለዚህም ነው«ሞቶሙሰ ለጻድቃን ሕይወቶሙ ውእቱ ወእመሰ ሞትኩ ርቡኅ ሊተ ብሞት ደስታዬ ነው በማለት ነውና ሰውና መላእክት ሊብዙ ዘመናት ተራርቀው ሰውና እግዚአብሔር ለአምስት ሺህ አምስት መቶ ዓመታት ተለያይተው ከኖሩ በኋላ ፈጣሪያችን የታረቀን በእስዋ አማካይነት ነውና ኢትዮጵያውያን ክርስቲያኖች ለእመቤታችን የሚሰጡት ክብርከሌላው የተለየ ነው ።

ከዚህም የተነሣ በተለያዩ ጊዜያት የእመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያምን በመንፈሳዊ ስሜት በደመቀ ክብር እናከብራታለን የእመቤታችን በዓላት ብዙዎች ቢሆኑም ከብዙዎቹ በገናና ክብር ከምናከብራቸው በዓላት ጥር ፳፩ ቀን ነው ።

ይኸውም እንዲሁ በከንቱ አይደለም ራስዋ ይህንን ቀን በበለጠ የምትወደው መሆንዋን በመገንዘብ ነው ።

አንድ ጊዜ ከሰው ተለይቶ ከበዓት ተከቶ ድምፀ አራዊቱንና ግርማ ሌሊቱን ታግሶ የሚኖረው ባሕታዊ ስለ እመቤታችን በዓላት ጠይቆ እንደተረዳ እንገነዘባለን ።

ባሕታዊው እመቤታችን እንድትገለጽለት በጾም በጸሎት ተወስና ሲጸልይ ከቆየ በኋላ እመቤታችን ስትገለጽለት ከበዓላቶችሽ ሁሉ የትኞቹን ትወጃያለሽ ቢላት ኪዳነ ምሕረትን ልደታን አስተርእዮን ፍልሰታን አለችው ።

እንግዲህ ከእነዚህ ከተጠቀሱት አራት በዓላት እንዱ አስተርእዮ መሆኑን እንገነዘባለን ። ስለዚህ ነው አስተርእዮን በየዓመቱ በደመቀ ሁኔታ ስናከብረው የምንኖረው ፣ የክርስቲያኖች አለኝታና የሕይወት ዋልታ እመቤታችን ናት የክርስቲያኖች እናትና ለሰው ልጆች የምሕረት አማላጅ ድንግል ማርያም ናት እንግዲህ በክርስቶስ አምላክነት አምና በእመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም የተማፀነ ሰው እያፍርም በአደጋም አይወድቅም ቢወድቅም እንኳ ይነሣል።

የሕያው እናት የምሕረት መሠረት ናትና

ከነፈ ርግብ ማርቆስ

## ዮሐንስ ወንጌላዊ ።

ዮሐንስ ወንጌላዊ ከ፲፪ቱ ሐዋርያት አንዱ ነው አባቱ ዘውዴዎስ እናቱ ማርያም ባውፍልያ ይባላሉ ፤ ሁለቱም ጻድቃን ናቸው። ዮሐንስ እየተባለ የሚጠራ ስም በቅዱሳት መጻሕፍት በብዛት ይገኛል ለዮሐንስ ወንጌላዊ ከሁሉ ልዩ የሚያደርጉ ብዙ የቅጽል ስሞች አሉት ለምሳሌ ጥቂቶቹን ብንጠቅስ «ዮሐንስ ታዎጐሎስ ነባቤ መለኮት ነው» ዮሐንስ ፍቁረ እግዚእ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ የሚወደው ወይም ጌታን የሚወድ ማለት ነው ። ከወደዳችሁኝ ሕጌን ጠብቁ ያለውን እንደሱ አድርጎ የጠበቀና የፈጸመ ሌላ የለምና እንዲሁም ስለ ንጽሕናውና ስለ ቅድስትናው ከባለሟልነቱም የተነሣ ወደጌታችን ወደ ኢየሱስ ክርስቶስ አጠገብ ቀርቦ ጌታ ሆይ የሚያሲዝህ ማን ነው ? ብሎ ስለ ጠየቀ «ዘረፈቀ ውስተ ጎጽኑ ለኢየሱስ» ተብሎአል ።

እንዲሁም በአርስቱ እንደ ተገለጸው ካራቱ ወንጌላውያን አንዱ እሱ በመሆኑ ዮሐንስ ወንጌላዊ ዮሐንስ ወልደ ነጐድጓድ ይባላል ። ለዚህም ማስረጃ እንዲህ ሲል ይገኛል የዘብዴዎስ ልጅ ያዕቆብንና ወንድሙ ዮሐንስን» ቦአኔርጌስ ብሎ ጠራቸው የነጐድጓድ ልጆች ማለት ነው » ደቂቀ ነጐድጓደ አለ ። ደቂቀ ምሥጢር ደቂቀ መለኮት ሲል ነው ደቂቀ ነጐድጓድ ማለተ ግን በምሳሌ ነው እርጥብ ጢስ ከርጥብ ምድር ይቡስ ጢስ ከይቡስ ምድር ከርጥብ ምድር ይቡስ ጢስ ከይቡስ ምድር ወጥቶ አንድ ደመና ይሆናል ከውቅያኖስ ውሀ ጠልፎ ሲወጣ የነጐድጓድ ድምጽ ያሰማል እነዚህም ከቤተ ክህነት ከቤተ መንግሥት ተወልደው ግሩም የሆነ ነገረ መለኮትን ሲያስተምሩ ተሰምተዋልና ደግሞም «አባሰብሐ ለወልድከ» አባቴ ሆይ ልጅህን ግለጸው ወመጽአ ቃል እምሰማይ ዘይብል ሰባሕኩከ ፤ በዮርዳኖስ በደብረ ታቦር ገለጽኩህ ወዓዲ እሴብሐከ ዳግመኛ በመስቀል በተአምራት ገለጽኩህ የሚል ቃል ተሰማ ወሕዝብሰ እለ ይቀውሙ ወይሰምኡ ይቤሉ ነጐድጓድ ውእቱ ቆመው የሚሰሙት ሕዝብ ግን ነጐድጓድ ነው አሉ የሚል ኃይለ ቃል እሱ በጻፈው ወንጌል በምዕራፍ ፲፪ ላይ ይገኛልና በኔ በኩል ወልደ ነጐድጓድ መባል ስሙ ከግብሩ ጋር የተስማማ ነው ።

ዮሐንስ ወንጌላዊ ከጌታችን ከኢየሱስ ክርስቶስ ዘንድ ወንጌልን እየተማረ ከዋለበት እየዋለ ከአደረበት እያደረ ፫ ዓመት ከሦስት ወር አብሮ ስለኖረ ከጌታ ቃል ሲቃል የተማረውን በጆሮ የሰማውን በዓይን ያየውን በእጅ የዳሰሰውን አውቆና ተረድቶ ሲመሰክር በመልእክቱ መጀመሪያ እንዲህ ብሎ ጸሕፎታል«ስለሕይወት ቃል ከመጀመሪያ የነበረውንና የሰማነውን በዓይናችችንም ያየነውን የተመለከትነውንም እጆቻችንም የዳሰሱትን እናወራለን ሕይወትም ተገለጠ አይተንማል እንመሰክርማለን ከአብ ዘንድ የነበረውንም ለእኛም የተገለጠውን የዘላለምን ሕይወት እናወራላችኋለን እናንተ ደግሞ ከእኛ ጋር ኅብረት እንዲኖራችሁ ያየነውንና የሰማነውን በእናንተ ደግሞ እናወራላችኋለን ኅብረታችንም ከአባት ጋር ከልጁም ከኢየሱስ ክርስቶስ ጋር ነው ደስታችሁም እንዲፈጸም ይህን እንጽፍላችኋለን።» በማለት ከጌታ መማሩን በተጨባጭ ያስመሰክራል በተጨማሪም«የእግዚአብሔር ልጅ እንደመጣ እውነተኛም የሆነውን እናውቅ ዘንድ ልቡናን እንደሰጠን እናውቃለን እውነተኛም በሆነው በእርሱ እምነትን ጸንተን እንኖራለን። የእርሱ ልጅ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው እውነተኛ አምላክና የዘላለም ሕይወት ነው ልጆች ሆይ ከጣኦታት ራሳችሁን ጠብቁ» እያለ እውነተኛ ምስክርነቱን መስክሯል (፩ኛ ዮሐ ፭ ፡ ፳—፳፩ ።)

የቅዱስ ዮሐንስ ሀገረ ስብከቱ እስያ ነው እሱም ከዚያ ገብቶ ጌታ ከዕንስም ጀምሮ እስከ ዐረገበት ቀን ድረስ ያደረገውን ተአምራት ያስተማረውን ትምህርት የሠራውን ትሩፋት ቢነግራቸው ከአምልኮተ ጣኦት ወደ አምልኮተ እግዚአብሔር ከገቢረ ኃጢአት ወደ ገቢረ ጽድቅ ፈጥነው ሊመለሱለት አልፈቀዱም ። ይልቁንም ስፍር ቁጥር የሌለው ፀዋትወ መከራ አደረሱበት በተለይ የኤፌሶን ሰዎች እጅግ ከፉዎች ስለ ነበሩ አብሮ ኮሮስና እርሱ ወደ ሀገራቸው ገብተው ማስተማር አልቻሉም ፤ የሚገቡበት ምክንያት ቢያጡ ሮምና የምትባል ግፈኛ ሴት ነበረች እንደ ኤልዛቤል ጣኦት አምላኪ ናት የእርሷ የእያቷ የቅድመ አያቷ ባሮች ነን ከጠፋን በብዙ ዘመን ተገኘተናል እያሉ ያስወሩ ጀመር እሷም ውዳሴ ከንቱ ሽታ አምን ናቸው ይግቡልኝ ብላ አስገብታቸዋለች ዮሐንስን እንጨት ፈላጭ እሳት አንዳጅ አብሮ ኮሮስን ዕቃ አጣቢ አድርጋቸዋለች እሷ ግን ስትወጣ ስትገባ ሥራ አይሠሩም እያለች ቅዱስ ዮሐንስን ፊቱን በጥፊ መታችው ስደበችው እዋረደችው እሱ ግን ይህን ሁሉ ግፍ ታግሶ ተቀበለ እንጅ አልተቀየመም ።

ከዚህ በኋላ ሮምና ሞግዚትሆና ከምታሳድጋቸው ልጆች አንዱ የንጉሥ ልጅ ነበር እርሱን አስከትላ ወደ ቤተ ጣኦቱ ገባች ዮሐንስና አብሮ ኮሮስም ተከትለዋት ሄዱ በእነሱ አድር ያለ መንፈስ ቅዱስን ባየ ጊዜ በጣኦቱ አድሮ ያለ ሰይጣን ወጥቶ ሲሄድ የንጉሡን ልጅ አንቆ ገደለው መለስ ብላ ብታይ ተከትለዋት አየች እነዚህ ከመጡ ጀምሮ ኃዘን እንጅ ደስ ብሎኝ አላውቅም ብላ እንደ ልማዷ ዮሐንስን በጥፊ መታችው አስነሡት ይባላል እንጅ ሰው ይመታልን ? እላት ደግሞ ሰው ከሞተ በኋላ ይነሣልን ? ብላ እደግመዋለሁ ስትል አድርጋችሁ አሳዩኝ ይባላል አላት በሉ ከቻላችሁ አስነሡት አለቻቸው ወዲያው በጸሎት አስነሥተውታል ማን ገደለህ ብትለው በዚህ አድሮ ያለ ዐይነ ፈጣጣ ጥርስ ገጣጣ እነዚህን ባየ ጊዜ ወጥቼ እሄዳለሁ ሲል ረግጦ አንቆ ገደለኝ እነዚህ ግን አስነሡኝ እንጅ ምንም አላደረጉኝ ብሎ መስክሮላቸዋል ። ንጉሡም ይህንን ባየ ጊዜ በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ከነሠራዊቱ አምኖ ተጠምቋል ይልቁንም ሮምና ይቅርታ ጠይቃ አምና ተጠምቃለች ።

ቀጥሎም ቅዱስ ዮሐንስ ሦስት መቶ ሙታን አስነሥቷል ይህንንም ባዩ ጊዜ በኤፌሶን ያሉ ሕዝብ በሙሉ አምነው ተጠምቀዋል ። ከዚህ በኋላ በእስያ ውስጥ በሚገኙ ሦስት አህጉር እየተዘዋወረ አስተምሯል በዚሁ ምክንያት አብያተ ጣኦታት ፈርሰዋል በምትካቸው ሰባት አብያተ ክርስቲያናት ተሠርተዋል በነዚህም ለተሾሙ ሰባት አለቆች መንፈስ ቅዱስ ስለ አዘዘው የተገለጸለትን ምሥ





www.ethiopianorthodox.org

ጢር ጽሮላቸዋል ። እንዲሁም መንፈሳዊ አባት እንደ መሆኑ መጠን በቃል ያለ ይረሳል በመጽሐፍ ያለ ይወረሳል ብሎ ለኤፌሶን ሰዎች ያስተማረውን ወንጌል ጽፈዋል ፤ ዳግመኛም ሦስት መልእክታትንና በደሴተ ፍጥሞ ያየውን ራእይ ጽፎ እልና ፡ ምሳሌ ከአራቱ ወንጌላውያን ብዙ-ምሳሌ አላቸው ቤተ ክርስቲያን የገኑት ምሳሌ ስለሆነች የኢትዮጵያ ሊቅ ቅዱስ ያሬድ እነዚህን አራቱን እፍላጋት ለአራቱ ወንጌላውያን ምሳሌ አድርጎ ሲናገር ወኃይዝተ ወንጌል የዐውዳ በቤተ ክርስቲያን እምአርባዕቱ አፍላጋት እንተ ትሰቀይ ትምህርተ ለስጽባሔ እማቴዎስ ልደቶ ወእማርቆስ መንክራቶ እምሉቃስ ዜናዊ ተሰምዮ ለሀም ወእም ዮሐንስ በግዐ ወዘንተ ሰሚዓ ትገብር በዓለ በፍግዓ ።

ትርጓሜ

የሰቱ ትምህርትን የምትቀበል ቤተ ክርስቲያንን የወንጌል ፈሳሾች ከአራቱ አፍላጋት ምሳሌ ተነሥተው ያረኳታል ከማቴዎስ የጌታን ልደት ከማርቆስ ጌታ ያደረገውን ተአምራት ከሉቃስ ላህም መባሉን ከዮሐንስ በበግ አምሳል ሲሠዋ መምጣቱን ቤተ ክርስቲያን ይህንን ሰምታ በፍስሐ በደስታ በዓልን ታከብራለች ።

በማለት ተናግሯል የዚህም ምሥጢር ማቴዎስ የዳዊት ልጅ የአብርሃም ልጅ ብሎ የጌታን ልደት በጽሕፈት ማስረዳቱን ሲያይ እማቴዎስ ልደቶ አለ ፪ኛ ማርቆስ ጌታ ጋኔን በማውጣት ድውይ በመፈወስ ለምጽ በመንጻት ያደረገውን ተአምራት እምልቶ አለ ፍቶ መጻፉን ሲያይ እማርቆስ መንክራቶ አለ ፫ኛ ሉቃስ ጌታ በአምሳለ ላህም መሠዋቱን ተመልክቶ የጻፈውን ሲያይ እምሉቃስ ዜናዊ ተሰምዮ ላህም አለ ዮሐንስ ነዋ በግዑ ለእግዚአብሔር ዘየአትት ኃጢአተ ዓለም ብሎ የተናገረ ምንም ዮሐንስ መጥምቅ ቢሆን ይህንኑ ቃል በጽሕፈት አጉልቶ የገለጠው ዮሐንስ ወንጌላዊ በመሆኑ ወእምዮሐንስ በግዐ አለ(ማቴ ፡ ፩ ፡ ፩ ፡ ማር - ፩ ፡ ፳፫ ። ፵፭ ም ፡ ፫ ! ፩—፲፪ ሉቃ- ፲፭ ፡፳፪ ዮሐ ፡ ፩ ፡ ፳፱) ። ወንጌልን የተረጎሙ ሊቃውንትም አራቱ አፍላጋት ካንድ አጠጥተው አትክልትን አዝርእትን ከይብሰት ወደ ልምላሜ ከልምላሜ ወደ ጽጌ ከጽጌ ወደፍሬ እንዲያደርሱ አራቱ ወንጌላውያንም ካንድ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ተምረው «ሰውን ከይብሰተ ኃጢአት ወደ ልምላሜ ንስሐ ከልምላሜ ንስሐ ወደ ጽጌ ትሩፋት ከጽጌ ትሩፋት ወደ ፍሬ ክብር ያደርሳሉ በማለት ምሳሌውን አጉልተው ያሳያሉ እስከዚህ ድረስ በመጠኑ ከታሪኩ ሰምተናል ።

ከዚህ ላይ ለአንባብያን ልናስገነዝብ የፈለግነው የሐዋርያትን በዓል ማክበር የሚገባ መሆኑን ለመግለጽ ነው የቀድሞ ሊቃውንት የሐዋርያት በዓል በዓመት አንድ ቀን ይከበር ዘንድ ወስነዋል፤ በየጊዜውም የተነሡ ቀሳውስት በዓሉ እንዳይሻር የሚውልበትን ቀን ለማያውቁ በማሳወቅ እንቢ ያለውን በውግዘት ጭምር እየከለከሉ መኖራቸው በኢትዮጵያ ክርስቲያኖች ዘንድ የተለመደ ነው ስለ ምን ይከበራል ? የሚል ሰው ቢኖር ፩ኛ ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስን ልናውቅ የቻልነው በእነሱ ስብከት በመሆኑ ነው ፪ኛ እናንተን የሚቀበል እኔን ይቀበላል እኔንም የሚቀበል የላከኝን ይቀበላል ። ነቢይን በነቢይ ስም የሚቀበል የነቢይን ዋጋ ይወስዳል ጻድቅንም በጻድቅ ስም የሚቀበል የጻድቁን ዋጋ ይወስዳል ማንም ከነዚህ ከታናናሾቹ ለአንዱ ቀዝቃዛ ጽዋ ውኃ ብቻ በደቀ መዝሙሬ ስም የሚያጠጣ እውነት እላችኋለሁ ዋጋው አይጠፋበትም ፤ ብሎ ፈጣሪያችን ኢየሱስ ክርስቶስ ቃል ኪዳን ስለ ሰጣቸው በዓላቸውን እከብረን ዝክራቸውን ዘክረን በስማቸው ስለ አምላከ ዮሐንስ ስለ አምላከ ጴጥሮስ እያልን ርኁባንን ብናበላና ብናጠጣ ዋጋ እንደምናገኝ የታመነ ነው ። በዚሁ መንገድ እንንድመራም ቅዱስ መንፈሱን ይላክልን ።

መ/ጌታ- ይባቤ መልአክ

## በጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የሚጎበኝ ቤት

ቤተሰቡ የተባረከ ከሆነ ቤቱም የተባረከና የሚጎበኝ ሰላም የሚገኝበት ቤት ይሆናል ። ይህንንም ለማወቅ ብንፈልግ ወንጌላዊው ሉቃስ በጻፈው በም ፲ ፡ ፴፰—፵፪ ያለውን እንብቦ መረዳት ያስፈልጋል ።

ይኸውም ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በዚህ ዓለም ሲመላለስ በነበረበት ዘመን እየሄደ ሲያየውና ሲጎበኘው የሚያስደስተው አንድ ቤት ነበር ። በዚህም ቤት ሁለት እኅትማማቾች ከወንድማቸው ጋር አብረው የሚኖሩ ጥሩ ቤተሰቦች ነበሩ። እነዚህም እርስ በእርሳቸው የሚዋደዱና የሚከባበሩ ቤተሰቦች ስለነበሩ ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በኼደ ቁጥር ደስ ብሏቸው ይቀበሉትና ያስተናግዱት ነበር ።

አንድ ቀን ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ይህንን ቤት ለመጎብኘትና እነዚህን ጥሩ ቤተሰቦች ለመጠየቅ ኼደ ። ደርሶም እንዳረፈ የእግዚአብሔርን ቃል ለማርያም ያስተምራትና ይነግራት ነበር ። እርሱም የሚናገረው ቃል እንዱ እንኳን እንዳያመልጣት በፊት ለፊት ተቀምጣ ታዳምጥ ነበር ። ትምህርቱ በጣም ስለአስደሰታት እኅቷን ማርታን በቤት ሥራ ጥቂት ልትረዳትና ልታግዛት ፈቃደኛ ካለመሆኗም በላይ በዚህ ምክንያት ጥቂት እንኳ ጊዜዋን ልታጠፋ አትፈልግም ነበር ።
እኅቷም ሁኔታዋ ስለ አሳዘናት እንዲመከራት ለጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ነገረችው ።

ጌታችን ግን እሷን መውቀስ ትቶ ማርታን ወቀሳት «ለእኔ ብዙ ምግብ ከምታዘጋጅ ይልቅ የእግዚአብሔርን ቃል እየሰማሽ ጥቂት ብታዘጋጂ ይበቃ ነበር ። ማርያም ግን መልካም ዕድል መርጣለች ይህም ከእርስዋ አይወሰድም» አለና በቤተሰቡ መካከል የነበረውን አለመግባባት ወደ ሰላም ለወጠው።

ይህንንም ጌታችን ለደቀመዛሙርቱ በሰጠው መልስ ልንረዳ እንችላለን ። ደቀመዛሙርቱ ወደ ከተማው ምሳ ገዝተው ከተመለሱ በኋላ መምህር ሆይ ! ብላ አሉት። እሱ ግን እናንተ የማታውቁት የምበላው መብል አለኝ ይኸውም የላከኝን ፈቃድ አደርግ ዘንድ ሥራውንም እፈጽም ዘንድ ነው» አለ። የዮሐንስ ወ ፡ ም ፡ ፬ ፡ ቁ ፡ ፴፩-፴፭

ጌታችን ወደዚህ ዓለም የመጣው እራሱን ለመርዳትና ለማገልገል ሳይሆን የተቸገረውን ቤተሰብ ለመርዳትና ለማገልገልነው። በተጨማሪም ሥርቶ ለማሠራት የላከውን የአባቱን ፈቃድ ለመፈጸም ፡ ቃሉን ላልሰሙት ለማስማት የተራበውን ዓለም የሕይወት እንጀራ ሆና ለማጥገብ እንጂ በብዙ ድካም የተዘጋጀውን ምግብ እማርጦ ለመመገብና በምግብ ብዙ ወዳጅና ዘመድ ለማፍራት እንዳይደለ ለማርታም ሆነ ለደቀ መዛሙርቱ በተናገረው ቃል የክርስቲያኖችን ሕይወት ተስፈኛ ሊያደርገው ይችላል ።

የአልአዛርና የማርታ እኅት ማርያም እንተእፍረት ግን ትምህርቱን ስለሰማች ቃሉንም ከልብ ስለአዳመጠች በክርስቶስ ዘንድ ታላቅ ምስጋና አገኘች ። ይህንንም መልካም ዕድል ያገኘችው «ሰው ከእግዚአብሔር አፍ በሚወጣው ቃል እንጂ በእንጀራ ብቻ አይኖርም ።» ሲል ቅዱስ ቃሉ ስለሚናገር ነው ። በዚህ አንጻር እግዚአብሔር የሚገባበት ቤትና የሚጎበኘው ቤተሰብ ሁሉ መልካም ነገር ስላለው ቢቸገርም ሁሉ ነገር ይሟላለታል ። አንድ ነገር አይጎድልበትም የመንፈስ እረፍት ! የመንፈስ ደስታ አለው የልብ ሰላምም አለ ። ኃዘን የለም ፤ ልቅሶ የለም ፤ ሁከት የለም ፤ ጭቅጭቅ የለም ፤ ከመግባባት በስተቀር መለያየት አይኖርበትም ። ጌታ የማይገባበት ቤት አምላክ የማይጎበኘው ቤተሰብ ግን ኀዘን አለ ፤ ችግር አለ ፤ የልብ ሰላምም ሆነ የመንፈስ ደስታ አይገኝም ከጥል ከጭቅጭቅ በቀር መግባባት ፍቅር የለም እሱም የሴሰበት ቤት መጽናናትን አያገኝም።

ይህንንም በታላቁ አባታችን በያዕቆብ ቤተሰብ ለማየት ይቻላል ። እግዚአብሔር ከያዕቆብ ቤት ባልተለየበት ጊዜ ቤቱ ሁሉ ሰላም ይሆናል ። በቤተሰቡም መካከል መግባባት መረዳዳት የእርስ በእርስ መዋደድ ይኖራል ኃጢአት በርክቶ እግዚአብሔር ሲለይ ግን የእርስ በርስ ጭቅጭቅ ይበዛ ነበር።

ያዕቆብ ፲፪ ልጆች ቢኖሩትም እንኳ ከእነርሱ መካከል ዮሴፍን አብልጦ ይወደው ስለነበር አዳዲስ ቀሚስ በየጊዜው እየገዛ ያለብሰው ነበር ። ሁሉንም ባንድ ዓይን ከማየት ይልቅ ዮሴፍን ጧት ማታ በፍቅር ዓይን ከማየቱ ባሻገር ልዩ ልዩ ስጦታም ያደርግለት ነበር ። ወንድሞቹም እንዲህ ያለው አድልዎ ጠዋት ማታ ሲፈጸም ስላዩ እርስ በርስ ይለያዩ ጀመር ።

በዚህም ምክንያት ልጅና ልጅ እርስ በእርሳቸው እየተጣሉ የያዕቆብ ቤት ሰላም አጣ ።ይህም ማለት ባለቤቱ ራሄል ከልጆቹ ጋር ዮሴፍ ከወንድሞቹ ጋር እየተጨቃጨቁ ያዕቆብን ከትልቅ ኃዘን ላይ ጣሉት በመጨረሻም ቤቱ ሰላም ስለአጣ በቤተ ሰቡም መካከል ኅብረት በመጥፋቱ ነገሩ ከቀን ወደ ቀን እየተበላሸ ይኼድ ጀመረ ። እግዚአብሔርም ፍቅርን እንጂ ጥልን ለማይወድ ሁሉንም ተለያቸው ። ዮሴፍን ለነጋዴ ሸጡት በኋላም አውሬ በላው ብለው ልብሱን ደም ቀብተው መሞቱን ለአባታቸው አረዱት ቤታቸውም የደስታ መሆኑ ቀርቶ የኃዘን የልቅሶ ቤት ሆነ ። (ኦሪ ፡ ዘፍ፡ ም ፡ ፴፯ ፡ ፲፰—፳፭።)

ከጽሑፉ እንዳየነው እግዚአብሔር የተለየው ቤተሰብ እርስ በርስ ይለያያል እግሩ ደም ለማፍሰስ ይሮጣል ። ከክፉ ነገር በቀር መልካም ነገር ማድረግ ደስ አይለውም ። እግዚአብሔር የማይጎበኘው ቤት የኃዘን የልቅሶ ዋሻ ይሆናል ። የሙት ቤት ይሆናል ። ከጭቅጭቅ በቀር ሰላም

አይገኝበትም ። በያዕቆብ ቤተሰብ ይህ ከሆነ የልብ ሰላም የመንፈስ እረፍት እንዲገኝ ማንኛውም ቤተሰብ ቤቱን እግዚአብሔር እንዲጎበኝለት ወደልቡም እንዲገባለት ንጹህ አድርጎ መጠባበቅ ያስፈልገዋል ። እሱም ከገባበት ከደስታ በቀር ኃዘን የለም ፤ ከእርጋታ በቀር የመንፈስ ብስጭት የለውም ።

ይህንንም በያዕቆብ ቤተሰብ ተረድተናል ። በማርታና በእኅቷ በማርያም እንተእፍረት ሁኔታ ተገንዝበናል ባሁኑም ወቅት የተመለከትን እንደሆነ ታሪክ ራሱን ይደግማል እንደሚባለው በዘመናችንም በእያንዳንዱ ቤተሰብ ይህ ሁኔታ ሲፈፀም ይታያል ። ወላጆች ጧት ማታ እርስ በርሳቸው መነታረኩ እንኳቸው ልጆቻቸውን በትምህርትም ሆነ በምክር ተንከባክበው ማሳደግ ሲገባቸው አባትየው ሴቷን ልጅ ሲወድ እናትየዋ ደግሞ ወንዱን ልጅ ትወዳለች ሁሉም ልጆቻቸው ሲሆኑ ሁሉንም በአንድ ዓይን ከማየት ይልቅ ልዩነት በማሳየት አንዱን ይወዳሉ ሌላውን ይጠላሉ ።

በልብስ አገዛዝም ሆነ በጌጥ አሰጣጥ በኩል የፈለጉትን በመጠየቅ ጭምር ዓመትበዐል በመጣ ቁጥር ለሚወዳቸው ልጆች ሲገዙ ሌሎችን ለይተው ይተዋቸዋል ። በትእዛዝና በሥራ በኩልም ሁሉም በትክክል እንዲሠሩ ወዲያ ወዲህ እንዲላላኩ ካለማድረጋቸው





www.ethiopianorthodox.org

የተነጣ ወልጆች መካከል መለያየት ይፈጠራል ። ቲም በቀል አብሮ ያድጋል ። በመጨረሻም ተስፋ ስለሚቆርጡ ሴቶቹ ትምህርታቸውን አቋርጠው ወደሴተኛ አዳሪነት ወንዶችም ኪስ ወደማውለቅና ወደስርቆት ይሰማራሉ ።

እነዚህም ሀገሪቷንና ወገንን ይረዳሉ ተብሎ እምነት የተጣለባቸው ልጆች የሀገር ሸክም ይሆናሉ ።

ቤቱ የተባረከ እንዲሆንና ቤቱ ክርስቶስ እንዲጎበኘው ከተፈለገ ወላጆች ልጆቻቸውን በእኩልነት እየተመለከቱ ያለአድልዎ ካሳደጉ ቤቱ የሰላም ቤት ከመሆኑም ሌላ ሀገሪቷም የተባረከ ፍሬ ታገኛለች እግዚአብሔርን የሚያምን ሀገሩን የሚወድ የተባረከ ቤተሰብ ስለሚገኝ ክርስቶስ በምህረት ይጎበኘዋል ሰላምንም ያገኛል ። ረድኤቱም በረከቱም እንደማርያም እንተ እፍረትና እንደሌሎቹ ከቤቱ ድረስ ይመላለታል ።

እንግዲህ የማርያም ታሪክ እንዳየነው ቃሉን ለመስማት ፈቃደኛ በመሆኗ ክርስቶስን የመቀበል ዕድል አግኝታለች ።

እንዲህ ያለው ዕድል የተሰጣት ማርያም እንተእፍረት የካቲት ፮ ቀን እንዳረፈች መጽሐፈ ስንክሳር ይናገራል ። ከመልካም ሥራዋም የተነሣ በተጉለትና ቡልጋአውራጃ እሞያ ከምትባል ቀበሌ በሌሎችም ቦታዎች በስሟ የታነጸ ቤተ ክርስቲያን ይገኛል ።እኛም ስማችን በሕይወት መጽሐፍ እንዲጻፍ መልካም ሥራ ለመሥራት እንበርታ ።

መዓዛ አስማማው

# «የሕይወት መንገድ እኔ ነኝ»

«መንገድም ጽድቅም ሕይወትም እኔ ነኝ በእኔ በኩል ካልሆነ በቀር ወደ አብ የሚመጣ የለም» ይላል መድኃኒታችን ክርስቶስ ዮሐ ፲፬ ፮ ። ይህ ቃል ከተነገረበት ጊዜ ጀምሮ እስከ ፍጻሜ ዓለም ... ለሚነግሠው ትውልድ የሚያገለግል ነው ቃሉ እውነት ነው ። እውነተኛ ስለራሱም ቢሆን ቢመሰክር እያፍርም ማንም ቢሆን ከሌላው ይልቅ ራሱን የሚያውቀው ራሱ ነው ። እውነቱን መመስከር ከፈለገ የራሱ ከራሱ ሊሠወር አይችልም ። ስለዚህ የሕይወት መልእክተኛ ክርስቶስ ምን መሆኑን ስለሚያውቅና ቃሉን በሥራው ለማጽደቅ ችሎታ ስለማያጥረው ስለ ራሱ መናገርን ከተመጻዳቂነት አልቆጠረውም ቢሆንም ከመንፈስ ዳግ ነት ከልብ ምስክርነት ውጭ ሆነው በሥጋዊ ሥርዓት የሚመሩትን ለመግታት ሲል ስለማንነቱ ምስክሮችን ለማዘጋጀት ተገድዶ ነበር ። (ዮሐ ፭፡፴፫—፴ ፣ ፰፡፲፯—፲፱)ሆኖም፣ ሌላዎቹ እም፡ው እንዲጠቀሙ ነበር እንጂ እንደዚህ ዓለም ሥርዓት ራሱን ለማጽደቅና ለመጥቀም አልነበረም ። ስማይም ምድርም ምስክሮቹ ናቸው እሱ ምን ጊዜም እሱነው ራሱን አይክድም (፪ ጢሞ ፪፡፲፫ ።)

ፍኖት (ምንገድ) የአለው ቃል በዚህ ዓለም ሳለን እንዴት መመላለስና መመራት እንደሚገባን የሚያመለክት ቃል ነው እንዴት መኼድ እንደሚገባንም ራሱ ተዋርዶ አስተምሮናል ፤ አሳይቶናልም ። ስለዚህ ለጉድለታችንም ለምልዐታችንም በእግዚአብሔር ፊት ሚዛን ይኖረዋል «መጥቼ ባልነግራቸውና ሰው ሊሠራው የማይችለውን ሥርቼ ባላሳያቸው ኖሮ በደል ባልሆነባቸውም ነበር»የአለው ስለዚህ ነው(ዮሐ፡፲፭፡፳፪-፳፫)

ደግሞም ይህ ቃል ከዚህ ከአላፊው ዓለም ወደ ማያልፈው ሕይወት ለመድረስ ልንመራበት የሚገባን ልዩ አቅጣጫ የአለው መንገድ መኖሩን ያመለክተናል ። መንገዱ እያሳስትም ሆኖም እሱ እንደኼደ በእውነት ለመኼድ ለሚፈልጉነው እንጂ ለማይፈልጉ የተሠወረ ነው ስለዚህ እኔ እኼዳለሁ ትፈልጉኛላችሁ አታገኙኝም በኃጢአታችሁ ትሞታላችሁ እኔወደምኼድበትለመምጣት አትችሉም» ብሎአል (ዮሐ ፰፡፳፩ ወደሕይወት ለመምጣት መንገድ ነበረን ወደ ሕይወት ለመኼድ መንገድ አለን መንገዱ ያው አንድ ብቻ ነው ይኸውም ከቅድስት ድንግል ማርያም የተወለደው ሕይወቱን ስለ ሰው ሕይወት አሳልፎ የሰጠው የዓለም መድኃኒት ክርስቶስ ነው ።

መንገድ ቅን ነው ነገር ግን እንደልብ ለመራመድ የመንገዱ ቀናነት ብቻ አይጠቅምም ሙሉ ጤናማ መሆንም ያስፈልጋል ይህ በሥጋ ነው በመንፈስም በኩል ልበ አንካሣ ሐሳበ ጠማማ ከተሆነ የዚያኑ ያህል ነው ።

ስለዚህም «ጻድቃን ይኼዱበታል ኃጥአን ይወድቁበታል» ተባለ(ሆሴ ፲፬ ፱) የሕይወት መንገድ እኔ ነኝ ሲል ሌላ የሞት መንገድ መኖሩን እንረዳለን ነገር ግን በሕይወት መንገድም ሆነ በሞት መንገድ ለመኼድ ምርጫው የራሳችን ይሆን ዘንድ አስቀድሞ ይህ ቃል ተነገረን እስራኤል በሙሴ መሪነት በዚህ ዓለም በትንቢት የተነገረላቸውን በተስፋ የተጠበቀላቸውን ርስት ለመውረስ ከግብጽ ተነሥተው ይጓዙ በነበረበት ጊዜ የተሟላ ሕይወት አልነበራቸውም ጉዞአቸው ፤ ሥጋዊ እንጂ መንፈሳዊ ስለአልነበረ ለሌላዎችም ለራሳቸውም ጥፋት ምክንያት ሆና ነበር ቃሉን አልሰሙምና መልእክተኛውንም አሳዝነዋልና ብዙዎቹ በምድረ በዳ ወድቀው ቀሩ (ዘኍ ፣ ፲፬፡፳፱) አሁንም «ቃሌን የሚሰማ የላከኝንም የሚያምን የዘለዓለም ሕይወት አለው ከሞትም ወደ ሕይወት ተሻገረ» እየአለ ያበሥረናል (ዮሐ ፭፡ ፳፬ ።) እንግዲህመልሳችን ምን ይሆን? ለክ ስብሐት ለእንተ ምስጋና እየአልን በደስታ እንቀበለውምን? በቤቱና በመጋቢው ፣ ላይ የተደረገው እንጉርጉር ያን ያህል የአስፈረደ ከሆነ በባለቤቱና በመጋቢው አለቃ ላይ የተደረገው (የሚደረገው) እንጉርጉር የሚያስከትለው ውድቀት ምን ያህል ይሆን? የእግዚአብሔር ቃል ብርቱ ነው ሁለት ልሳን ከአለው ሰይፍ ይስላል »(ዕብ ፬፡፲፪ ።)

አሁን የምንተርከለት መንገድ ከሁለቱ መንፈሳውያት ዓለማት ግብራችን ወደ መራን ወደ አንዱ ለመኼድ የሥጋዊ ሞትን ድልድይ ከተሻገርን በኋላ ከሚገጥሙን መንታ መንገዶች ወደ ሕይወት ስለሚያመራው የመንፈሳዊ ዓለም መንገድ ነው ፤ የመንገዱ መሪም ራሱ ክርስቶስ ነው መቼም ከዚያ ከሁለቱ በቀር ሌላ ማግረሚ መንገድ አለመኖሩን ቅዱሳት መጻሕፍት ይነግሩናል።እነዚህም አንዱ የሕይወት አንድም የሞት መንገዶች ናቸው ፍኖተ ክልኤቲ አሐቲ እንተሞት ወአሐቲ እንተ ሕይወት የተባለው ስለዚህ ነው ። «ሕይወት» የአለውም ቢወዱት ከሚጠላው ቢጠጉት ከሚገፋው ቢያምኑት ከሚከዳው ከዚህ ዓለም ሕይወት በኋላ ስለሚተካው መንፈሳዊና ዘለዓለማዊ ስለሆነው ሕይወት የሚያመለክት ቃል ነው ፣ በአሁኑ ክፍለ ጊዜአችን ለማብራራት የአለን ሙከራ «የሕይወት መንገድ» በሚለው በአንዱ ዘርፍ ያለ ብቻ ላይ ቢሆንም በቅዱሳት መጻሕፍት ውስጥ ይህን የመሳሰሉ በርከት የአሉ ቃላት ይገኛሉ ለማሳየት ያህል የሕይወት ውኃ የሕይወት እንጀራ ፤ የሕይወት ቃል የሕይወት ብርሃን እሊህን የመሳሰሉ ናቸው በዚህ ላይ የተደጋገሙ ቃላትን እንመለከታለን ይኸውም «ሕይወት» የሚለው ቃል ነው ። የዚህ ቃል ወሰን በዚህ ብቻ ሊጠቃለል የሚችል ቃል አይደለም እንዲያውም የሃይማኖታዊ ህልውና ትርጉም የመንፈሳዊ ድርሰት ሁሉ ዓላማ ስለዚሁ ነው ብንል በከፊልም ቢሆን የምንሳሳት አይመስለኝም ይህም የሕይወት ብርሃን በሆነው በክርስቶስ በኩል የአገኘነው አዲስና መንፈሳዊ ሕይወት ነው ወደዚህ ሕይወት ለመድረስ የሚቻለው በእሱ ብቻ ስለሆነ «የሕይወት መንገድ እኔ ነኝ»አለ ።

ሕይወት በላይ በሰማይ በታች በምድር ተስፋ ከምናደርገው ነገር ሁሉ የበለጠ አስፈላጊ ነገር ነው ሕይወት ከአመለጠች በኋላ በከንቱ አልተመለሰችም ክርስቶስ ስለ እኛ ሥጋዊ ሕይወቱን የአሳለፈላት ደሙን የአፈሰሰላት ስለዚች ሕይወት ነው የክርስቶስ ሕይወት ደግሞ ከሁሉም የከበረ ዋጋ የማይገኝለት መሆኑን እንዘነጋም ሕይወት ምን ያህል ዋጋ የአላት መሆኑን ለአለመርሳት ያህል ተቃራኒውን «ሞት» የሚለውን ቃል በአንጻርዋ ብናስቀምጥ ምሬቱንም በጣዕምዋ ብናነጻጽር ለማግረጥ ይቀርበናል ፤ ይጠቅመናልም ነገር ግን የዚህ ዓለም ሕይወት ከወዲያኛው ዓለም ሕይወት የሥጋዊ ሞት ከነፍስ ሞት ልዩነት የተራራቀ ነው ። ሰው ዓለሙን ሁሉ ቢያተርፍ በነፍሱ ከተጎዳ ምን ይረበዋል?(ማቴ ፲፮-፳፮) ከሥጋዊ ሞት ለመዳን አይቻልም እንጂ የሚቻል ሆኖ ዋጋ የሚያስፈልግ ቢሆን ኖሮ ምን መስጠት በተገባን ነበር? ስለ ወዲያኛው ዓለም ሕይወት ይህን ዓለም የለወጡ ሰዎች ምሥጢሩ የገባቸው ናቸው ሥጋዊ ሞትን ከመፍራት የተነሣ የምንጨነቀውን ያህል ለመንፈሳዊ ሕይወታችን ጥንቃቄ የምንጨነቅ ቢሆን ኖሮ የእግዚአብሔርን ውለታና የሕይወትን ዋጋ ማወቃችን ነበር ይህን ማለቴ የመንፈሳዊ ሕይወት ምሥጢር ከሁሉ ተሠውሮአል ማለቴ አይደለም ከበጎ ምግባር ስለወጡ ከሃይማኖት ስለአፈነገጡ ኢተነሣሕያን ይህን አላሉ ።

መቼም ቢሆን ክፉ አድራጊዎች እውነተኛ ፍርድ በሚሰጥበት በወዲያኛው ዓለም ይቅርና ጻድቅና ኃጥእ ተባብረው በሚኖሩበት በወዲሁ ዓለም እንኳ የሚጠቀሙ እጅግም አይደሉም የገዛ በደላቸው ጠላት ሆና ተነሥቶ በመንፈስ ዳኝነት በከሰባቸው ጊዜ ዓየሩ በቀዝቃዛው ይፈጃቸዋል ፤ ዓለሙ በሰፊው ይጠባቸዋል ፤ ጭንቅ ጭንቅ ይላቸዋል ፤ ተስፋ ይቆርጣሉ ራሳቸው ይበቀላሉ በዚህም ምክንያት ሥጋዊ ሕይወታቸው የአለቀንዋ ከዚህ ዓለም ትቆረጣለች ፤ መንፈሳዊ ሕይወታቸውም ከወዲያኛው ዓለም ትለያለች ይህም ሁለት ሞት ነው ።

በዓለም ላይ ከዚህ ዓለም ሕይወት በኋላ ሌላ በማመሳሰል የሚያሳስቱ የዓዋቂ አጥፊዎች አይታጡም በዚህ ዓለም እንደፍላጎታቸው መኖርን ም ከፈለገ ዘንድ የወዲያኛወን ዓለም ሕይወት የመሰከሩ እንደሆነ በዚያ እውነትአርግጥ (የግድ) አለና ግብራቸው እንዳይገለጥባቸው ስለሚፈሩ የመንፈሳዊ ሕልውናቸውን አለመኖሩ መመስከርን መረጡ ይህም የስሕተት የበደል በደል ነው ።

ለመሆኑ የወዲያኛው ዓለም ሕይወት ባይኖር ኖሮ በዚህ ዓለም ላይበድለውየተበደሉ በምንይካሡ ነበር? እንዲሁም መንፈሳዊ ሕግ መሠራቱ ትእዛዛት መስጠታቸው ለምቀኝነት እንጂ ለሕይወት እንደአይደለ አድርገው የሚቄጥሩ እንደ ሰው ሠራሽ ነገርም የሚገመቱ አንድ አንድ የመንፈስ ምስኪኖች አይታጡም እሊህም ልባቸው ከሕይወት ብርሃን የጨለመ ህሊናቸውም ወደክፋት የአዘነበለ ስለሆነ ምሥጋና ይድረሰውና የአምላክነቱን አሳብ እንደራሳቸው አድርገው የሚተረጉሙ ሕይወት የተሰጠውን ቃሉንም የሚያስተባብሉ





www.ethiopianorthodox.org

ድይዙ ባደረጉት ቅስቀሳ ከሀገረ ስብከቱ ጀምሮ እስከ ምእመናኑ ድረስ አንዳንድ መስኮት እናሠራ ለን እያሉ በበጎ ፈቃዳቸው ቃል ስለገቡና ቅስቀሳውም በጣም አስ ደሳች ስለነበር ለበዓሉ ከፍተኛና ተጨማሪ ድምቀት ሰጥቶት ውሎ አል ከዚህም አያይዘው የሀ/ስብ ከቱ ሥራ አስኪያጅ መ/ጌታ ዓለም አታላይ የገዳሙን ታላቅነትና ታሪ ካዊነት በሰፊው አስረድተው ከፍ ተኛ ቅስቀሳ በማድረጋቸው ከም እመናኑ ከፍተኛ ገንዘብ ተገኝቶ አል ።

ከዚህም ቀጥሎ ከጅማ የዕድ ሳት ኮሚቴ ሊቀ መንበር ከአቶ ሥዩም ወልደ ማርያም ሪፖርት ቀርቦአል አቶ ሥዩም ካቀረቡት ዘገባ እንደተመለከትነው በበዓሉ ዕ ለት ብር ፪ሺ፰፻፺፱ ከ፹ መገኘቱንና ኮሚቴው ከተቋቋመበት ጊዜ ጀምሮ እስካሁን ድረስ የኮሚቴው ማኅ በረተኞች ሰብስቦ ገቢ ያደረገው ብር ፴፫ሺ፮፻፵፰ ከ፴ (ሠላሳ ሦስት ሺህ ስድስት መቶ አርባ ስምንት ብር ከሠላሳ ሣንቲም ጠቅላላ ገቢ ብር ፴፮ሺ፭፻፴ ከ፹፩ሳ (ሠላሳ ስድስት ሺህ አምስት መቶ ሠላሳ ብር ከሃምሳ አምስት ሣንቲም) መድረሱን ይገ ልጿል የኮሚቴው ሊቀ መንበር ሪፖርታቸውን በማራዘም ሲያብ ራሩ በዚህ ቤተ ክርስቲያን እድሳት እኛ ካወጣነው ገንዘብ ይልቅ ብፁዕ አቡነ ማትያስ ከ፡ሁ ያላነሰ ወጭ እንዳደረጉ አውስተው ብፁዕነታ ቸው ያወጡትን ወጭ ሲተነትኑም አንደኛ ፪ ቢዮጆ ድንጋይ (ገል ባጭ መኪና ከነነዳጁና ለሹፌሩ የሚከፈለው ን አበል ጭምር ችለው ሁለተኛ ሃምሳ ሦስት ጭነት በገል ባጭ መኪና ኢሸዋ ጠቅላላ ወጭ ውን ችለው ማቅረባቸውን ገል ጸዋል ። አያይዘውም ይህ ሁሉ በአካባቢ ዋጋ ሲተመን ከላይ የዕ ድሳት ኮሚቴው ከሰበሰበው ገቢ ቢበልጥ እንጂ እንደማያንስ ለመ ገንዘብ ችያለሁ ብለዋል ፤

በበዓሉ ዕለት በሥፍራው ተገ ኝተን ስለዕድሳቱ እያያን እንደተ መለከትነው ውብና ድንቅ ሥራ ይዞ እንደሚገኝና ባሁኑ አያያዝና በዕቅዱ መሠረት ከተፈጸመ የቤ/ ክርስቲያኑ ሕንጻ ለትውልደ ትው ልድ ሲተላለፍ እንደሚኖር አያ ጠራጥርም ብለን እንገምታለን ፤ በቅደም ተከተል ይሠራል ይተ ከላል ተብሎ በብፁዕ አቡነ ማት ያስ የከፋ ሀገረ ስብከት ሊቀ ጳጳ ስና በዕድሳት ኮሚቴው የወጣው ዕቅድ ሁሉ ለፍጻሜ ከደረሰም ገዳሙ በኢትዮጵያ ካሉት ታላላቅ ገዳማት ከፍ እንደሚል እንጂ እን ደማያንስ ለማረጋገጥ ይቻላል ።

በበዓሉ ዕለት በከፋ ሀገረ ስብ ከት በዴቻ አውራጃ ካሉት አብ ያተ ክርስቲያናት ለዚህ ታሪካዊ ቤተ ክርስቲያን ዕድሳት የሚውል ገንዘብ ለመስጠት ቃል የገቡት ፤

| | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| ፩ኛ/ | የደቻ በሐ ቅ/ጊዮርጊስ | ቤተ | ክርስቲያን | ብር | - - - - | ፩ሺህ |
| ፪ኛ/ | የጊዲ ጊዮርጊስ | » | » | » | ---- | ፭፻ |
| ፫ኛ/ | የዴቻ እኩት ሚካኤል | » | » | » | ---- | ፭፻ |
| ፬ኛ/ | የዴቻ አውራጃ ቤ/ክህነት | | » | » | ---- | ፪፻ |
| ፭ኛ/ | የሺታ ቅዱስ ገብርኤል | | » | » | ---- | ፪፻ |
| | | | | ጠቅላላ ድምር | | ፪ሺህ፬፻ |

ይህ ከዚህ በላይ የተጠቀሰው ገንዘብ የአብያተ ክርስቲያናቱ ኃላፊዎች በበዓሉ ዕለት በከፋ ሀገረ ስብከት በዴቻ አውራጃ ካሉት አብያተ ክርስቲያናት ለዚህ ታሪካዊ ቤተ ክርስቲያን ዕድሳት የሚውል ገንዘብ ለመስጠት ቃል የገቡት ናቸው ፤

ከላይ ከፍ ብለን እንደጠቀስነው የአንደራቻ መድኃኔ ዓለም ቤተ ክርስቲያን ሃያ ስምንት መስኮት እንዳለው ገልጸናል መስኮቱ ክፍት ከመሆኑ የተነሣ ርግቦችና ሌሎች አዕዋፍ እየገቡ ቤተ ክርስቲያኑ ስላበላሹት መዝጊያ እንዲገባለት አስፈላጊ ሆኖአል በዚሁም መሠረት ዘመናዊ የመስኮት መዝጊያ እንዲያሰሩ በተደረገው የበጎ ምግባር መንፈስ ያደረባቸው ምእመናን የተቻላቸውን ያህል እንዲይዙና እንዲሠሩ በተደረገው ቅስቀሳ ፤

| | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| ፩ኛ/ | የከፋ ሀገረ ስብከት ፰ የመስኮት መዝጊያ ለማሠራት ቃል ገብቶአል | | | መንበር | ሁለት | ከጅማ |
| ፪ኛ/ | አቶ ሥዩም ወ/ማርያም | የእድሳት | ኮ/ሊቀ | » አባል | ሁለት | » |
| ፫ኛ/ | » ግዛቸው ተክሌ | » | | « ጸሐፊ | አንድ | » |
| ፬ኛ/ | « ታደስ ወ/ሚካኤል | « | | « ገንዘብ | ያዥ አንድ | » |
| ፭ኛ/ | « ብርሃኑ ተ/ማርያም | « | | « ገንዘብ | ተቀባይ አንድ | » |
| ፮ኛ | « ስሜ ቡልቻ | « | | « አባል | አንድ | » |
| ፯ኛ/ | « ተሾመ አሰፋ | « | | | | |



| | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| ፰ኛ/ | « ደምሴ ቱሬ | « | « | « | « | « |
| ፱ኛ/ | « ጌታሁን አደመ | « | « | « | « | « |
| ፲ኛ/ | « ፍሥሐ ዓለማየሁ | « | « | « | « | « |
| ፲፩ኛ/ | « ኃይሉ በረዳ | « | « | « | « | « |
| ፲፪ኛ/ | « ስማቸው ሊታወቅ ያልፈለጉ | « | « | « | « | « |
| ፲፫ኛ/ | « « « | « | « | « | « | « |
| ፲፬ኛ/ | « ግራዝማች ደበበ ይመር | « | « | « | « | « |
| ፲፭ኛ/ | አቶ ኃይሉ አየለ | « | « | « | « | ከቦንጋ |
| ፲፮ኛ/ | ወ/ሮ አሰገደች | « | « | « | « | « |
| ፲፯ኛ/ | « ታየች/ወ/ኢየሱስ | « | « | « | « | « |
| ፲፰ኛ/ | « ተዋበች ባዩ | « | « | « | « | « |
| ፲፱ኛ/ | « ቦጋለች ስለሺ | « | « | « | « | « |
| ፳ኛ/ | « ስብለ ባዩ | « | « | « | « | « |
| ፳፩ኛ/ | « ቦጋለች ወ/ጻድቅ | « | « | « | « | « |
| ፳፪ኛ/ | « አሰገደች | « | « | « | « | « |

እነዚህ ከዚህ በላይ ስማቸው በዝርዝር የተጠቀሱት ምእመናን ታቦተ ሕጉ በቆመበት ፊት ቀር በው ቃል የገቡ መሆናቸውንና የመስኮቱ አሠራርም መሐንዲሱ ባወጣው ዲዛይን በአንድ ዓይነት ወጥ እንዲሆን ኮሚቴው ማስታወቁን ዘገባው ያለመክታል ።

የአንደራቻ መድኃኔ ዓለም ገዳም ዓመታዊ ክብረ በዓል ከዚህ በላይ በተዘረዘረው መርሐ ግብር መሠረት ተከናውና በብፁዕ አቡነ ማትያስ የሀገረ ስብከቱ ሊቀ ጳጳስ ጸሎተ ቡራኬ የበዓሉ ፍጻሜ ከሆነ በኋላ በበዓሉ ላይ ለተገኙ እንግዶች በብፁዕ አቡነ ማትያስና በእድሳት ኮሚቴው አማካይነት የተዘጋጀውን ጠበል ጠዲቅ እየቀመሱ ወደየቤታቸው ተመልሰዋል ።

## ከፋ ሀገረ ስብከትና ልማቱ ።

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን በቃለ ዓዋዲ ደንብ በእያንዳንዱ አጥቢያ ቤተ ክርስ ቲያን ሰበካ ጉባኤ እንዲቋቋም ከተ ደረገበት ጊዜ ጀምሮ እስከ ዛሬ ድረስ ከእያንዳንዱ ምእመን የሚፈለ ገውን አስተዋጽኦ ደረጃ በደረጃ እያ ደገ መጥቶአል አስተዋጽኦው ደ ረጃ በደረጃ ከማደጉ የተነሣም ባሁ ኑ ጊዜ መንፈሳዊ አገልግሎት በተ ሟላ ሁኔታ በመካሄድ ላይ ይገ ኛል ። ወደልማቱ መለስ እንበ ልና ባሁኑ ጊዜ በየቤተ ክርስቲያኑ አካባቢ የሚታዩ የልማት ተቅዋ ሞች እጅግ ያስደስታሉ ፤ ለቤተ ክርስቲያናችንም ታላቅ ዕድገትና ኩራት ሆኖአል ። በከፋ ሀገረ ስብ ከት በሚዛን ከተማ በቅድስት ማር ያም ቤተ ክርስቲያን ሰፊ የልማት ተግባር እየተካሄደ ነው በፆብሩ ሰንበት ት/ቤት ሳምንታዊ ልማት በሚል መርሐ ግብር ተመርኩዞ በ፲፱፻፸፰ ዓ/ም ሦስት ሺህ ባሕር ዛፍ ተክለዋል እንደዚሁም በ፲፱፻፸፱ ዓ/ም ሦስት ሺህ ባሕርዛፍ አክለውበታል ።

በ፲፱፻፹፩ ዓ/ም ፬ሺ፺ ባሕርዛፍ ጨምረውበታል ።

በ፲፱፻፹፪ ዓ/ም ፲፰ሺህ ባሕርዛፍ አክለውበታል በጠቀላላው ፲፪ ሺ ህ ፰፻፶ አሥራ ሁለትሺህ ስምንት መቶ ሃምሳ ባሕር ዛፍ ተክ ለው ለከንችና በወራጅ ያርሶ አል ወጣቶቹ ይህን ሁሉ በሚ ተክሉበት ወቅት የግብርና ተጠሪ አትክልት በመስጠት ፤ የወባ መ ከላከያ (መቈጣጠሪያ) መኪና በመርዳት እንደተባበሩአቸው ወጣ ቶቹ አስረድተዋል ። ከዚሁ ባሕር ዛፍ ውስጥ ለመንበረ ጵጵስና ማሠ ሪያ ብዛት ፭፻ አግዳሚና ወራጅ በብር፲፫ሺ፯፻(አንድ ሺህ ሰባት መቶ) ተሸጦለ ቤተ ክርስቲያኑ ገቢ ሆኖ አል ሲል የወጣቶቹ የሰንበት ት/ ቤት ተጠሪ መምህር ኃ/ጊዮርጊስ ዳኜላቀረቡት ቃለመ ጠይቅ ሲመ ልስ ገልጾአል ።

በተለይም ከፍተኛ ልማት ያዘ የሚታየው በሚዛን ተፈሪ የመ ንበረ ሊቀ ጵጵስናው ነው በብ ፁዕ አቡነ ማትያስ የሀገረ ስብ ከቱ ሊቀ ጳጳስ ከፍተኛ ጥረት ሕን ጻው የተመሠረተበት ቦታ በአቀ ማመጡና በአሠራሩ በኩል ስንመ ለከተው ካሉት ሀገረ ስብከቶች ልዩ ውበት ያለው ግሩም የሆነ መንበረ ሊጵጵስና ተሠርቶአል ባሁኑ ጊዜ ሕንጻው ሊያልቅ ተቃርቦአል ግቢው እጅግ በጣም ሰፊ ከመሆኑ የተነሣ ለወደፊቱ በዚህ ቦታ ብዙ ልማት እንደሚለማበት ለመተን በይ ይቻላል ።

ብፁዕ አቡነ ማትያስ መንበረ



www.ethiopianorthodox.org



ብፁዕ አቡነ ማትያስ ከእድሳት ኮሚቴ አባላት ጋር

ጵጵስናው ሥራው አልቆ አገል ግሎት ለመስጠት ይችል ዘንድ ባሁኑ ጊዜ በጣም እየቻኮሉት ነው በዚሁ አያያዝም ሥራው ተጠና ቅቆ እንደሚያልቅና በቅርቡ አገ ልግሎት እንደሚጀምርም ይታመ ናል ።

የሀገረ ስብከቱ ጽ/ቤት ከሚ ዛን ቅድስት ማርያም አጥር ጋር የተያያዘ ሲሆን በሀ/ስብከቱ ሥራ አስኪያጅ በመሪጌታ ዓለም አታላይ አንድ በአንድ ጎብኝተናል ። ከጽ/ቤቱ ተያይዞ የጥበበ እድ ሥራ ተከ ፍቶአል ጠበብቱ ከሚሠሩአቸው ዕቃዎች አልጋ ፤ ቁምሳጥን ፤ ወን በር ፤ ጠረጴዛ ፤ ኮሚዲናና የመጻ ሕፍት መደርደሪያ (ሸልፍ) ተመ ልክተናል ነገር ግን ሥራው የሚ ንቀሳቀሰው በሰው ጉልበት ብቻ በመሆኑ አድካሚነት እንዳለው ተገልጾልናል በቅርብ ጊዜ ማ ሽን እንደሚመጣላቸውና ጥበበ እዱም ካለው ይኩት መቶ በመቶ እንደሚያድግ ሀገረ ስብከቱ ዕቅዱን በማስረዳት ግልጸልናልነገርግንማሽ ኑን እሰጣለሁ ያለውየልማት ክፍሉ በቶሎ ቢረዳቸው መልካም ነው።

ከዚሁም ሌላ በቅጽረ ቤተ ክርስ ቲያኑ ውስጥ ከየአውራጃው ለተ ውጣጡ መንፈሳዊ ትምህርት ተከ ታታዮች የተሠራላቸውን ቤት በሞ ግዚቱ አማካይነት ጎብኝተናል ፤ ሕጻናቱ ከቀለም ትምህርቱ ሌላ ጥበብ እድ (ልዩ ልዩ ቅርጻ ቅርጽ ጭምር) በመማር ላይ መሆናቸውን ለማየት ችለናል ሕጻናቱ ምግባቸው መኝታ ቤታቸውና ባጠቃላይ ኑሮ አቸው በቅረጽ ቤተ ክርስቲያኑ ስለሆነ መንፈሳዊ ሕይወታቸው በጣም ጥሩና የተስተካከለ አቋም ሊያስጨብጣቸው እንደሚችል ይገ መታል ።

የመንገድ ሥራ በከፋ ሀገረ ስብከት ፤

«ቦለዘተውህቦ»እንደተባለው ብፁዕ አቡነ ማትያስ የበፋ ሀገረ ስብከት ሊቀ ጳጳስ ለሥራ የታደሉ በመ ሆናቸው ካሁን በፊት በነበሩበት በኢሉባቦር ሀ/ስብከት በሙቱ ከ ተማ ያሠሩት የካህናት ማሠልጠኛ በብዙ መቶ ሺህ የሚቈጠር የ ቡና ተክል ያስተከሉዋቸው አብያተ ክርስቲያናትና ያሰሩት መንበረ ሊቀ ጵጵስና ስንመለከት በጥቂት ዓመታት የተከናወኑት አይመስሉ ም ። ስለዚህም ብፁዕነታቸው ልዩ የማሠራት ስጦታ እንዳላቸው በተ ጨባጭ ማስረጃ ለማወቅ ይቻላል ዛሬ ደግሞ የመኪና መንገድ የሌ ላቸው ታላላቅ አብያተ ክርስቲ ያናት ሕዝበ ክርስቲያኑ እንደልቡ በመኪና ሂዶ ለመሳለምና ከቅዱ ሳንም በረከት ለመቀበል (ለማግ ኘት) ይችል ዘንድ ብፁዕነታቸው በሰፊው ስላሰቡበት ወደባሐ ቅዱስ ጊዮርጊስና ወደ እኩት ቅዱስ ሚካኤል ቤተ ክርስቲያን የሚወ ስደው መንገድ እጅግ አድካሚና ከፍተኛ ገንዘብና የጉልበት ወጭ የሚጠይቅ መንገድ አሠርተው ኅዳር ፪ቀን ፲፱፻፸፫ ዓ/ም ብፁዕ አቡነ ገሪማ የኢሉባቦር ሀገረ ስብ ከት ሊቀ ጳጳስ የከፋ ክልል አካ ባቢ አስተዳደር ከፍተኛ ባለሥል ጣኖችና የሀገረ ስብከቱ ሥራ አስ ኪያጅ መ/ጌታ ዓለም አታላይ እን ዲሁም የከተማው ታላላቅ አዛው ንት በተገኙበት ተመርቅአል ።

ይህ መንገድ ከቦንጋ ፲፫ ኪ/ ሜትር የሚርቅ ነው ፤ መንገዱ ፲፫ ኪ/ሜትር ስንለው አጭር ወይም ትንሽ ይመስለናል ፤ ዳገት ቁል ቁለቱ ደኑ ገደሉ በጣም አስቸጋሪ ስለሆነ በደልዳላ ቦታ ሁለት መቶ ኪሎ ሜትር ቢሠራ እንደሚቀል ከሁኔታው ለመረዳት ይቻላል መን ገዱ ባማረና በተስተካከለ ሁኔታ የተሠራ መሆኑንም በቦታው ተገ ኝተን ተመልክተናልና ነው ብፁዕ አቡነ ማትያስ አስፈላጊ ለሆኑ ቦታ ዎች ጥርጊያ መንገድ ለማስገባት ከቦንጋ ወደባሐ የሚወስደው ብቻ ሳይሆን ከቦንጋ ወደ ማጂና ወደ ሌሎችም አስፈላጊ ቦታዎች መን ገድ ለማስገባት ዕቅድና ጅምር እንዳለ ለመገንዘብ ችለናል ።

ሊ/ት ገብረ ክርስቶስ ኃ/ማርያም



የእድሳት ኮሚቴ አባላት በአንደራቻ ገዳም ከተሳላሚዎቹ ጋር

## የመምህር ኪሮስ አጭር የሕይወት ታሪክ

መምህር ኪሮስ አጽብሐ በ ፲፱፻፲፰ ዓ/ም ከአባታቸው ከብ ላታ አጽብሐ ወልደ ሥላሴ እና ከእናታቸው ከወይዘሮ ወለተ ሥ ላሴ በትግራይ ራስ ገዝ በሽሬ አውራጃ በታች ቆራሮ ወረዳ ልዩ ስሙ ቤት ማርያ በተባለው ስፍራ ተወለዱ ዕድሜያቸው ለትምህርት ሲደርስ በዚሁ በተ ወለዱባት ደብር ለመዐርገ ዲቁና የሚያበቃ ትምህርት ተማሩ ቀጥ ሎም ደብረ ዐባይ ገዳም በመሔድ ከመምህር የኋላሸት መዝገብ ቅዳሴ ተምረው በመምህርነት ተመረቁ ከዚህ በኋላ ወደገዳሙ ማኅበር በመግባት ሥርዓተ ማኅበሩን በማ ጥናት ( በመማር በረድዕነት) ገዳ ሙን ሲያገለግሉ ቆይተው በማኅ በሩና በአበምኔቱ ፈቃድ ዓርዑተ ምንኩስናን ተቀብለዋል ።

መምህር ኪሮስ ባሳዩት መል ካም የሥራ ፍሬና ባላቸው ትጋት መሠረት የገዳሙ መጋቢ ሆነው ሠርተዋል ። በዚሁም ሥራ ፲፫ ዓመት ያህል ገዳሙን አገልግለዋል ብዙ የሥራ ፍሬም አሳይተዋል ከዚህም በኋላ ወደ ዋልድባ ገዳም ኼደው ገዳሙን ለ፶ ዓመታት ያህል አገልግለው ትምህርታቸው ን ለማስፋፋት ወደ ጎንደር በመ ቀጠል ፀዋትወ ዜማንና ቅኔን ተ ምረዋል ከዚህ በኋላ ወደ አዲስ አበባ መጥተው በብፁዕ ወቅዱስ



መምህር ኪሮስ አጽብሐ እኒህ ነበሩ

አቡነ ባስልዮስ ፓትርያርክ ዘኢ ትዮጵያ የነበሩ መልካም ፈቃድና ትእዛዝ ወደ ደብር ቅዱስ ደብረ ጽጌ ገዳም ተልከው በቅዳሴና በሰዓ ታት ተመድበው ሰፋ ያለ ግልጋ ሎት ከማበርከታቸውም ሌላ ከአ ለቃ ይትባረክ መርሻ የቅኔ ትም ህርታቸውን በሚገባ አጠናክረዋል በ፲፱፻፵፩ ዓ/ም ቅድስት ሥላሴ መ/ኮሌጅ ት/ቤት ገብተው የዘመ ናዊና መንፈሳዊ ትምህርት ተም ረዋል በቅድስት ሥላሴ ቤተ ክር ስቲያንም በቅዳሴ አገልግለዋል ፤ በትርፍ ጊዜያቸውም በአርበኞች ትምህርት ቤት ገብተው የሃይማ ኖት እና የግብረገብ ትምህርት አስ ተምረዋል ። በ፲፱፻፵፯ ዓ/ም በዚሁ ት/ቤት በመደበኛ መምህርነት ተ መድበው ለ፪ ዓመታት ያህል መን ፈሳዊ ትምህርት አስተምረዋል ።

ኋላም ልዕልት ዘነበ ወርቅ ይባል ወደ ነበረው የግል ት/ቤት ተዛውረው እስከ ፲፱፻፶፭ ዓ/ም ፤ አስተምረዋል ። መምህር ኪሮስ አጽብሐ በ፲፱፻፶፭ ዓ/ም በግሪክ የመማር ዕድል እስኮላርሺፕ አግ ኝተው አሁን በግሪክ መንግሥት ሥር በሚገኘው ሃልኬ በሚባለው ኮሌጅ ገብተው የግሪክ ቋንቋ አጥንተዋል ከዚያም በ፲፱፻፶፯ ዓ/ም ወደ አቴንስ ዩኒቨርሲቲ ተዛውረው በቲኦሎጂና በፍልስፍና ትምህርት ተመርቀው በ፲፱፻፷፩ ዓ/ም የመጀመሪያ ዲግሪያቸውን ተቀበሉ ።





www.ethiopianorthodox.org

መምህር ኪሮስ አጽብሐ በግሪክ አገር ትምህርታቸውን እንደጨረሱ ወደ አሜሪካ ሀገር ሄደው ፕሪስቶን ኮሌጅ በሚባለው ገብተው ለ፪ ዓመታት ያህል ትምህርታቸውን ከተከታተሉ በኋላ የማስትሬት (ቢ ኤም ኤ) ዲግሪያቸውን ከተቀበሉ በኋላ ወደ ሀገራቸው ተመልሰው በትምህርት ሚኒስቴር መጀመሪያ በዳግማዊ ምኒሊክ አጠቃላይ ፤ ፪ኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተመድበው አስተምረዋል በተጨማሪም በያዙት ሥራ ላይ የመንበረ ፓትርያርክ ቅድስት ቅዱሳን ማርያም ቤተ ክርስቲያን አስተዳዳሪነት ተሾመው ታላላቅ ሥራዎችን አከናውነዋል መጥቀስ ቢያስፈልግም ያሉትን መገልገያ ተቋሞችን ሠርተዋል በዚህች ቤተ ክርስቲያን ሰበካ ጉባኤ በመጀመሪያ ጊዜ ከማቋቋማቸውም በላይ አስተዳደሩን በሕግና በሥነ ሥርዓት እንዲመራ አድርገዋል ።

መምህር ኪሮስ አጽብሐ ቀድሞ ጉቴጌ ሙነን ይባል በነበረው ዛሬ የካቲት ፲፪ በሚባለው ት/ቤት አስተምረዋል ።

ከዚህም በመቀምል በድሮ ሣህለ ሥላሴ ይባል በነበረው በአሁኑ የኅብረት ፍሬ በተባለው ትምህርት ቤት ሲያስተምሩ በ፲፱፻፷፩ ዓ/ም በጥሮታ ተገልለዋል ።

ከዚህ በኋላ በሰዋስወ ብርሃን ቅዱስ ጳውሎስ ከፍተኛ መንፈሳዊ ትምህርት ቤት ተመድበው ለ፫ ዓመታት ያህል ሠርተዋል ።

መምህር ኪሮስ አጽብሐ በአዲስ አበባ በተለያዩ ትምህርት ቤቶች መልካም ሥራን ሠርተዋል ደግ አባት መሆናቸውን ሕያው ሥራቸው ይመሰክራል ።

መምህር ኪሮስ አጽብሐ የተጣሉትን በማስታረት የታረዘውን በማልበስ የተራበውን በማብላት የታመመውን በመጠየቅ የተቸገረውን በመርዳት ርኅሩኅና ደግ አባት መሆናቸውን የሚያውቋቸው ጓደኞቻቸው ይመሰክሩላቸዋል ።

መምህር ኪሮስ አጽብሐ በከፍተኛ ፲፪ ቀበሌ ፲፰ ሲኖሩ በአደረባቸው ሕመም ምክንያት በተለያዩ ሐኪም ቤቶች ሲታከሙ ከቆዩ በኋላ ኅዳር ፭ ቀን ፲፱፻፹፫ ዓ/ም ከዚህ ዓለም በሞት ተለይተዋል የቀብራቸው ሥነ ሥርዓት ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ መርቆሬዎስ ፓትርያርክ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ ብፁዓን ሊቃነ ጳጳሳት የአ-አበባ አድባራት አስተዳዳሪዎች የጠ/ቤ/ክህነት ከፍተኛ ባለሥልጣኖችና ታላላቅ የአዲስ አበባ ነዋሪዎች በተገኙበት በመንበረ ጸባኦት ቅ/ሥላሴ ካቴድራል ተፈጽሞአል ።

አቅራቢ መምህር ገ/ማርያም አጽብሐ የደቡብ አዲስ አበባ ፤ ክፍለ ከተማ ሊቀ ካህናት

## የአክሱም ሐውልቶች ይመስክሩ

የአክሱም ሐውልቶች እደጥበባት ፤ በግዝረት ምልክት የወንድነትን ባሕርይ ፤ በታላቅ አካል አምሳል ተቀርጸው ሲታዩ ፤ ጥበብ ምንድነው? ግዝረትስ? የቀረቡትን ሁለት ጥያቄዎች በተመስጦ እንድንገነዘባቸው ያሳስቡናል ።

ጥበብ እም ኅበ አልቦ የተገኘ አይደለም ። ከሌለ ነገር ላይ ወይም ከባዶ ሁኔታ የመጣ ሳይሆን ከሰው ልጅ መፈጠር ጋር ቀዳማዊነት እንዳለው በጥልቀት ሁኔታውንና አመጣጡን ማሰብ ይቻላል ። ጥበብ ከእግዚአብሔር መምጣቱን ቀዳማዊነትና ዘለዓለማዊነት እንዳለው የሚገልጡ የትምህርተ መለኮት ጠበብት አሉ ።

ጥበብ ከሰው ልጆች ዘር ሕሊና የተገኘ ነው የሚሉ በሕዋው ዓለማት ተፈጥሮ ላይ የተንሳፈፉትን ርቀትና ቅርበት በመገመትና በመቈጣጠር ምክንያት ከምድራውያን ጠበብት የተገኘ የተፈጠረና የተገለጠ የሚያደርጉ አሉ ። ምድራዊ ሰው ምድራዊ ሥራዎችን ማስገኘቱ ነው ። ይሁን እንጂ የሰው ልጅ ሥራ አላፊና ጠፊ መሆኑ በብዙ ዓይነት ታውቀዋል ። በኃያልነታቸው ዓለምን የተቈጣጠሩ ታላላቅ መሪዎችና ሊቃውንት ታላላቅ ሥልጣኔዎች ከተሞችና አስደናቂ ሥራዎች ሁሉ ተለውጠዋል ። ጠፍተው መቅረታቸውም ታውቀዋል ። ሠሪውም ሆነ ተሠሪው ሥራ በጠበብት ህሊና በፍለጋ ቸውና በምርመራቸው ዳግማዊ ትንሣኤ ቢኖረውም የሰው ልጅ ጥበብ የሰው ልጆችን ባሕርይ የወረሰና የለበሰ በመሆኑ ይኖራል ኖሮም ያልፋል ።

የርከበ ሊቃውንት አስተምህሮ ሰው ጥበብን ስለመፍጠሩ ጉዳይ በሰው የተገኘ እንጂ የተፈጠረ አለመሆኑን የቅድመ ተፈጥሮንና የድኅረ ዓለማትን አቀማመጥ ያስገነዘቡ መሆኑ ይታወቃል።ያልታዩአቸው ወይም ያልተገነዘቡአቸውና ያልደረሱባቸው ምድራውንና ሰማያውያን ጥበባት በመኖራቸው ምክንያት ከመኢምንት ፣ ማለት ምንም እንደሌለ ሳይገለጡ የኖሩ ዛሬ በመገለጣቸው ዓለምን ያስደነቁ ፍጥረታት ስለሚኖሩ ይህ ብቻም በቂ ተብሎ ከፍለጋና ከምርምር የቆመ ዓለም ባለመኖሩ ጥበብ በሰማያት ቢያርጉ በውቅያኖስ እመቀ እመቃት ቢጠልቁ ለጥበብ ውስንነትና ዳርቻ የማይገኝለት እጹብ ድንቅ ታላቅ ሥልጣን ያለው ልዩ ነው።(ዮሐ ፣ ራእይ ምዕ ፲፰ ቍ ፩) ጥበብ በባሕርዩ የተፈጠረውን ዓለም በመንፈሳዊ



ጥበብ መምራትና መጋቢነትን ማስተካከል ነው ። ይሁን እንጂ የተፈጠረውን ዓለም ማስተዳደር አለመቻሉና እግዚአብሔር ለሰው ልጅ በሰጠው ጥበብ ተጠቅሞ ጥበብን ለሰላም ሥራዎች አለማዋል ለማንም ሰው የአዳምና የሔዋን ዕፀ በለስ ይሆናል ቢባል ስሕተት አይመስልም

ጥበብ የሚሰጠው ከእግዚአብሔር ነው ስንል አበቦችን በቀልማት ማስጌጥ መቻል ከሰው አይመጣም ። በሰማያት የሚታዩትን ከዋክብት ከሰው ልጅ እደ ጥበብ መሥራት ወይም ማስተጋከል አይቻልም የፀሐይና የጨረቃ የከዋክብትና የልዩ ልዩ ሰማያውያን ተፈጥሮ በጣም የረቀቀና ከፍጡራን ሥራዎች ውጭ ነው።(፩ኛ ቆሮ ፲፭ ቍ ፵፩)በምድራችን ላይ ማንም በቀላሉ ሊገነዘበውና ሲረዳው ሊዳስሰውና ሊያመዛዝነው የሚችለው የሰው ጥበብ ያልሆነ ሥራ አለ ። የዐተር አበባዎች የቢራቢሮ ክንፎች የለበሱትን የመሰለ የቀለም ውበት ለብሰዋል ። እነዚህ የውበት ጸጋን የተቀለሙ የአዝርዕትና የቢራቢሮዎች ቀለማት የጥበበኛ ሰው ሥራ አይደሉም ። የጥንት ከለዳውያን ከተማቸው አብርሃም ይኖርበት የነበረው ኡር ነበረ (ዘፍጥ ፲፩፣፴፩) እነዚህ ሰዎች ፍልሥፍናቸውን በከፍተኛ ጥናት ላይ በተመሠረተ ማለት በተለይም የከዋክብት አፈጣጠርና አቀማመጥ የሚሰጡትን የብርሃን ዓመት በተመለከተ የበላይነትንና የበታችነትን በመግለጥና በማወዳደር በባቢሎናውያን ምድር ላይ የከዋክብትን አምልኮ አመጡ (ዳን ፩፥፫-፬) ለጥበብ ጌታዋና ፈጣሪዋ የሰው ልጅ ነው የሚሉ ጠቢብት ቢኖሩ ጥበብን በፈጠረ አምላክ የሚያምለኩት ግን በመንፈሳዊ ባሕርይ ላይ በተመሠረተ ሕይወታቸውንና ጥበባቸውን የሚመሩትን መጽሐፍ ቅዱስ ጥበበኞች ይላቸዋል (ዘጸእ ፤ ፴፭ ፱—፳) መገብተ ሥልጣናት ሁሉ ጥበብ ያስፈልጋቸዋል ። ከሚልዮን ጭፍራ ትንጣት የምታህል

ጥበብ ዓለማትን ማስተዳደርና መመገብ ትችላለችና ነው ። መጽሐፍ ቅዱስ ከእግዚአብሔር መባረክ እንዲሁም ከሺማግሌዎች ቡራኬን መቀበል ጥበብን ይሰጣል ይላል ። (ዘዳግም ፴፬ ፣ ፱ ፤)

ጥበብ በፍቅርና በሃይማኖት ላይ በተመሠረተ ትምህርት የሚገኝ ከመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎች ትልቁ ስጦታ መሆኑን(፩ቆሮ ፲፪፡ ፰)መመልከት ይቻላል ።

ጥበብ በሥጋዊው ዓለም የእግ



መጋቤ ጥበብ የማነ ብርሃን ተሾመ የአክሱምን ሐውልት ሲመረምሩ

ባሕሮች፤የብሶችና ሌሎችም የጥበባት ምንጭ የሆኑት ሁሉ መመርመርና በሕሊና ዓይን መመዘን መገለጥ ከተጀመሩ ወዲህ ጥበብ ከማንም በላይ የተገለጠው በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ መሆኑ ግልጥ ነው ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ አይሁድ ቢሆኑ ፤ የግሪክ ሰዎችም ቢሆኑ የእግዚአብሔር ጥበብ የሆነው ክርስቶስ ነው ማለቱን ከዚህ ላይ በማስረጃ ማቅረብ ይቻላል ። (፩ቆሮ ፩፡፳፬ ፤ )

ኞችም ሆነ የማቴሪያሊስት እደ ጥበብ በአስደናቂነት ይታያል በጥንት ከነዓናውያን ዘንድ ሐውልት ልዩ ልዩ መልእክት ነበረው ለአማልክቶቻቸው መስገጃ ፤ ወይም በመታሰቢያነትና ትምህርት የሆኑ ነገሮችን ለማስተላለፊያ ይሆን ነበረ በተለይም በእስራኤል ልጆች ታሪክ ሐውልቶች ብዙ ምልክቶች ነበሩዋቸው ይኸውም እስራኤላውያን ሐውልቶችን እንዲሰብሩ ታዘዋል ። (ዘጸአ ፳፫፣ ፳፬) የሎጥ ሚስትም



www.ethiopianorthodox.org

የጨው ድንጋይ ሁና በመቆሙዋ ሐውልት የተአምራት መግለጫ ነበረ ማለት ይቻላል ። (ዘፍጥ ፲፱፣ ፳፮ ለምሳሌ በሀገራችን በኢትዮጵያ በአክሱም የሚገኙትን ጥንታውያን ሐውልቶች የሰላምና የመከራ ጊዜያቸውን እሳልፈው ከምድር ተቆፍሮ የተገኙትንና በመቆም ላይ የሚገኙትን እንደተመለከትኩዋቸው የማንንም ሕሊና ለማሳመን ይበቃሉ ብየ አስባለሁ ።

የአክሱም ሐውልቶች ከብሉይ ኪዳን መጻሕፍት ጋር ተዋሕደው የተሠሩ ትእምርተ ዓላማ የተሠራባቸው ሐውልታት መስለው ታይተውኛል ። ከምድር ማኅፀን በቁፋሮ የተገኙትንና ቆመው የሚታዩትን በዓይኔ ተመልክቸ መልእክታቸውን እንደተረዳሁት የመገዘር ምልክት መስለው ታይተውኛል ።

ግኖስቲክ ከግሪኮች ዓለም መዳን የሚገኘው ሰዎች ጥበብን የባሕርይ ግንዛቤ ሲያደርጉ ነው ይሉ ነበር ። የግኖቲክ አሳብን በከፍተኛ ትርጓሜና አባባል ሐዋርያት እስከ ተቃወሙት ድረስ ከቤተ ክርስቲያን ምሁራን ሀሊና በልዩ ልዩ ሁኔታ ገብቶ ቆይቶ ነበረ ይሁን እንጂ ከግኖስቲክ ዋናው እስተሳሰብ ሰው በጥበብ ማለት በማወቅ የሚፈለገውን ማግኘት ይችላል የሚል ሲሆን ለአብርሃም በግዝረት ምልክትነት የተሰጠው የተገዘሩትን የእግዚአብሔር ሕዝብ ናቸውና ከፋትን ከሕይወታቸው ማስወገድ አለባቸው ይላሉ (ዘዳግም ፲፣ ፲፮) ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስም እግዚአብሔር በእምነት መሠረት ስለተቀበላቸው የጽድቃቸው ማኅተም ነው በማለት የግዝረትን አስተያየት አስረድተዋል (ሮሜ ፬፣ ፲፩) በኢትዮጵያ የአብርሃም ግዝረትና የሙሴ ሕግጋት ከትምህርት ደረጃ አልፈው የሀገር ባሕል ወደ መሆን አቅጣጫ መድረሳቸው ይታወቃል ። ይኸም ብቻ ሳይሆን ቀደም ሲል የነበሩትን የቤተ መንግሥት ሕግጋት ከሙሴ መጻሕፍት ጋር የነበራቸውን ግንኙነት ማገናዘብ ያስፈልጋል በተለይም በሙሴ ዘመን ግዝረት ለእስራኤል ሕዝብ ምልክትና መለያ ሆን (ዘፀአ ፲፪ ፣ ፵፫-፵፰ ።)

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ግዝረት ከአባቶች ከሙሴ አለመሆኑና አስቀድሞ የተነገረውም ለአብርሃም እንደነበረ አስተምሮ ስለዚህም መንፈሳዊ ምልክት በመሆን ስለእውነተኛ ፍትህ በቅን ሕሊና መፍረድ እንጂ በሥልጣን ብልግና እውነተኛ ፍርድን ማጣመም የማይገባ መሆኑን አስተምሮአል (ዮሐ፯፣፳፱) የአብርሃም ግዝረትና የሙሴ ሕግ የኢትዮጵያና የእስራኤል ሕዝቦችን በብዙ መልክና ሥርዓት አቀራርቦአቸው ቆይተዋል ። ኢትዮጵያውያን ዛሬም ቢሆን የእስራኤል አምላክ ይመስክር ካሉ ያቀረቡትን እንጀራ አይጎርሱም ።

ከላይ እንደተገለጠው የአክሱም ሐውልቶች የግዝረት ምልክት ነበሩ ፤ ወይም በቅርጻቸው ላይ የሚታየው የወንድ ብልት መሰል የሆነው ቅርጽ እንደ እኔ ምርምር ጥናት ከሆነ ከብሉያትና ከሐዲሳት መጻሕፍት ጋር ኢትዮጵያ ያላትን ግንኙነትና ጥንታዊነት ከመግለጡም ጋር የወንድነት ምልክት ነው ። ስለዚህ የአክሱም ሐውልቶች የግዝረት ምልክትና ምሳሌዎች አሉዋቸው በማለት ተገንዝቤአለሁ ። ግዝረት በኢትዮጵያ የዘመኑ መፈክር ሆኖ ተግባራዊነቱም በወንዶች ታላቅ አካል መልክ ሐውልቶቹ ተቀርጸዋል ። በጫፋቸውም ላይ መገዘር ግልጥ ሁኖ ይታያል ። በውስጣዊ ቅርጹም የዘርዓ ብእሲ ዘር መተላለፊያ ያለው መሆኑን ተገንዝቤአለሁ ።

ከአክሱም ሐዋልቶቹ የቆሙት ብቻ ሳይሆኑ ተሰባብረውና ወዳድቀው ወይም ያርስት ፣ የመንደሮችና የማዘጋጃ ቤት ወሰን እንዲሆኑ የተተከሉት ደንጋይዎች አዕባን ሁሉ ታሪክ የተመዘገበባቸው ናቸው ፤ የነገረመለኮት ምሁራን ዛሬ በአክሱም የሚታየው ቤተ መቅደስ ከዓለም ሰባተኛ ካቴድራል መሆኑን ያስተምራሉ ። ይህ በአጼ ፋሲል ተሠርቶ በልዩ ልዩነገሥታትና መሳፍንት እድሳት እየተደረገለት እስከ አሁን ድረስ ቆይተዋልበውስጡና በአካባቢው ጠረብት ከጠረቡ ዋቸው አዕፃን ጀምሮ የታሪክ ባሕር በአክሱም አለ ።

ኢትዮጵያውያት ፤ እናቶቻችን ፣ ከሐር ፈትል ከቀጤማ ከሕለላና ከአክርማ እንዲሁም ከስንደዶና ከልዩ ልዩ የልምላሜ ተፈጥሮዎች ሰፍተው ሊታቦተ ጽዮን ያበረከቱዋቸው መሶበ ወርቆች እጅግ የረቀቀና አስገራሚ እደጥበብ ከመሆኑ በላይ በብርና በወርቅ የተለበጡ መዘከሮች ሆነው አግኝታቸዋለሁ ።

በሊቃውንቱ የተቀሰሙት ቀይና ጥቁር ቀለማት ብዙ መጻሕፍት ተጽፈውበት ቀለማቱ ሳይደመሰሱ ብዙ ዘመናት አሳልፈው ሳለ እሁንም ሲያበረቀርቁ ይታያሉ ። ባሉት አልባሳት ላይ የሚታየው ጌጥ አሠራሩና አነዳደፉ እጅግ አስደናቂ ነው ። ደግሞ በአንጻሩ ዘለዓለማዊ ሥራ አለመኖሩን ከዚሁ ገዳም ሳልወጣ ተረዳሁ ፤ ግርማዊት እቴጌ መነን ካሠሩት ቤተ ክርስቲያን በስተቀር አጼ ፋሲልም ሆኑ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ያሠሩት ትልቁ ካቴድራል ከሞዛይኩ ማዕከል የሚፈሰው የዝናም ውሃ በቀጥታ ከቅኔ ማኅሌቱ ላይ ሰርጎ ይንቆረቆር ነበር ።

የዝናሙ ውሃ ሰርጎ በመግባት ያደረሰውን ከፍተኛ ጉዳት ለብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ተክለ ሃይማኖት ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ወፓትርያርክ ዘኢትዮጵያ የነበሩት ፲፫ ገጽ ሪፖርት አቅርቤላቸው በሰፊው አስበውበት የእድሳት ጊዜአዊ ኮሚቴ እንዲቋቋም አዘው እኔንም የእድሳቱ ጸሐፊ እንድሆን አዛውኝ ከተወላጆቹና ከመላው ኢትዮጵያውያን ምእመናን ዐቢይ ጉባኤ ተደርጎስለ ሕንጻው መታደስ ዋና አላማ በጠቅላይ ቤተ ክህነት ቋሚ ጽሕፈት ቤት እንዲኖረው በቅዱስነታቸው መፈቀዱ ነው ። በመሆኑም የሕንጻ ማሳደሻ ገንዘብ ከመላው የኢትዮጵያ ምእመናን ተውጣጥቶ መሐንዲሶችና አዋቂዎች ስለ ሕንጻው



መታደስ በጥናት ላይ እንዳሉ በአካባቢው በጸጥታው መደፍረስ ምክንያት የዕድሳቱ ጉዳይ ተቋርጦ ይህንኑ የተቀደሰ ዓላማ ከግቡ ለማድረስ ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ መርቆሬዎስ ፓትርያርክ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ ከፍተኛ ገንዘብ ለዕድሳቱ ሥራ በመፍቀድ አዲስ ምዕራፍ ከፍተውለት ይገኛል ።

የአክሱም ሐውልቶች ገዳማትና ልዩ ልዩ ጥበባት እንደ ሰው ልጆች ሁሉ በመከራ ላይ መውደቃቸውንና በልዩ ልዩ መከራዎች ሁሉ ተፈትነው ከዚህ ዘመን መድረሳቸውን ለመገንዘብ ማን ይሳነዋል ? በዚህ ጽሑፍ እግረ መንገዴን የሕንጻዎቹን በዝናም ፍሳሽና ሐሩር መፈረካከስ አወሳሁት እንጂ የዚህ ጽሑፍ ዋና ዓላማ የአክሱም ሐውልቶች የወንድ ልጆች የግዝረት ምልክቶች ናቸው ። ወይንም በወንድ ልጅ ታላቅ አካል አምሳል ተቀርጸው በእምርታነት ኖረዋል ለማለት ነው ።

በአክሱም ሐውልቶች ላይ የሚታየው ይህ የግዝረት ምልክት ረቂቅ ግንዛቤን የሚጠይቁና በተለይም የአክሱምን ታሪክ ባሕርያት በብዙ ዘርፍ ማጥናት የሚጠይቅ መሆኑ ይታወቃል ። በዚህ ገዳም ውስጥ ለሦስት ጊዜ ያህል ተመላልሼ ነበረ የጉዞዬም ዓላማ የሰበካ ጉባዔን በየአድባራቱና በየገዳማቱ ለማጠናከርና የቅርሶችንም አጠባበቅ ለማስገንዘብ ከዋናው መ/ቤት ተልኬ ነበረና ቅርሶቻችን የወረስናቸው ፤ ቢሆኑ በተለይም የቤተ ክርስቲያን አባቶችና ምእመናን አሁንም ቢሆን መከራዎችን በመቀበል ፣ መከራዎችን በማሸነፍ የጥበቃው ሁኔታ ከእነሱ ላይ ወድቆ ይታያል ።

እኛ ይኸንን ከዓለማት ውበትና ሀብት ሁሉ ልዩ ታላቅና በዘመናት የቅርስ ባለቤቶች ሁነን የምንታይ ኢትዮጵያውያን ሁሉ የወንድነታችንን ምልክት የሆነውን ግዝረት ስንመረምረው ክብሩ የተለየ ነው ። ግዝረት ለአብርሃም ዘር የተሰጠው ወንድነቱን እንዲያውቅ ነው ። ግዝረት ለሴቶች አል ተሰጠም ። የወንድነት ምልክት የሚያኮራው በጦርነት ጊዜ ወይም በመከራ ጊዜ ብቻ ሳይሆን የወንድነት ምልክት በሰላም ጊዜም ያኮራል በማለት በልዩ ልዩ ፎቶግራፎች በተደገፈ ማስረጃ የሐውልቶቹና የየገዳማቱ አቀማመጥ ትምህርቱ ስለቀረበ የብሉይ ኪዳን መምህር የነበሩት በጉባዔው ላይ አስተያየታቸውን ሲሰጡ እኛ የግዝረትን ትምህርት በሐውልቶቹ ላይ የተቀረጸውን የወንድነትና የግዝረት ምልክት አላጤነውም ነበረ መልካም ምሥጢር ገልጠውልናል እርስዎስ መጋቢ ጥበባት ነዎት ሲሉ አድንቀዋል ።

ስለዚህ በአክሱም ጽዮን የሚገኙት ሐውልቶች የአብርሃም ግዝረት ምልክት እንደነበሩ ሊታወቅ ይገባል ። እንዲሁም የዘመኑ የወንድ ልጆች መፈክር ማነቃቂያና ማስተማሪያ ሁነው ቆይተዋል ። በእርግጥ ግዝረት በኢትዮጵያ ከፍተኛ ዓላማና አፈጻጸም ያለው ከመሆኑም በላይ የአሸናፊነት ምልክት ነበር ። ከወንድነት የበለጠ አሸናፊነት የለምና ነው ። ይኸንን ጥናቴንና ምርምሬን የተመለከቱና እንደኔ የሐውልቶቹን ባሕርያትና ቅርጽ ከራሳቸው ባሕርሥጋ አገናዝበው ምሳሌውን ሊረዱልኝ እንደሚችሉ እተማመናለሁ

በጠቅላይ ቤተ ክህነት

ከመጋቤ ጥበባት የማነ ብርሃን

ተሾመ

## የአባ ገ/መስቀል ተ/ሕይወት አጭር የሕይወት ታሪክ

«ዓለምኒ የኀልፍ ወፍትወቱኒ የኀልፍ ወዘይገብር ፍትወቶ ለእግዚአብሔር ይነብር ለዓለም» ። ዓለም ያልፋል ምኞቱም ያልፋል እግዚአብሔር የሚወደውን የሚያደርግ ሰው ግን ለዘለዓለም ይኖራል ። ፩ኛ ዮሐ ፣ ም / ፪ ፣ ቁ ፣ ፲፯ ።

አባ ገ/መስቀል ተ/ሕይወት (ገሠው) በትግራይ ክ/ሀገር በተንቤን አውራጃ ልዩ ስሙ መነዌ ሊባኖስ ደብረ ጽጌ ገዳም እየተባለ በሚጠራው አካባቢ ስመ ጥሩ ከነበሩት ከአባታቸው ከአቶ ተ/ሕይወትና ከእናታቸው ከወ/ሮ ደመቀች ጥቅምት ፲ ቀን ፲፱፻፳፰ዓ/ም ተወለዱ ።

አባ ገ/መስቀል ተ/ሕይወት በአባትና እናታቸው ቤት በእንክብካቤ እና በሥነ ሥርዓት አድገው ዕ… ሜአያቸው ለትምህርት ሲደርስ በ… ወለዱበት አካባቢ በሚገኘው ከላ… በተጠቀሰው መነዌ ሊባኖስ ደብ… ጽጌ ገዳም ዳዊት ውዳሴ ማርያም… መልክዐ መልኮችን ከተማሩ በኋ… በ፲፱፻፵፰ ዓ/ም ከብፁዕ አቡነ ይ… ሐቅ ማዓርገ ዲቁና ተቀብለዋል … ከዚያም ትምህርታቸውንና መ…



www.ethiopianorthodox.org

ቸውን በማበልፀግ ከመምህር ገ/ወልድ መዝገብ ቅዳሴንና ሥርዓተ ምንኩስናን ሲከታተሉ ቆይተው በ፲፱፻፵፱ ዓ/ም ። ከፍ ብሎ በተጠቀሰው ገዳም ቆሞስ ከነበሩት መምህራቸው ከመምህር ገ/ወልድ መዓርገ ምንኵስናን ተቀብለዋል ።

አባ ገ/መሰቀል ተ/ሕይወት በተማሩት ትምህርትና በተቀበሉት ሥልጣን በተወለዱበት ገዳም ውስጥ እግዚአብሔር የሚወደውንና ለሰው ልጅ የሚበጀውን መንፈሳዊ አገልግሎት በድንግልና ተወስነውና «በጐብዝናህ ወራት ፈጣሪህን አስብ» የሚለውን የወንጌል ቃል ተከትለው ደክመኝና ሰለቸኝ ሳይሉ አገልግሎታቸውን ሲፈጽሙ ቆይተው በ፲፱፻፶፰ ዓ/ም ሰኔ ወር ዛሬ የሕይወታቸው ፍጻሜ ሆኖ አጽማቸው ካረፈበት አዲስ አበባ መካነ ሰማዕት ቅ/ቂርቆስ ቤተ ክርስቲያን መጥተው በደጅ ጥናት የተለመደውን መንፈሳዊ አገልግሎት ቀጠሉ ።

«ብእሲ ምእመን ዘበጎዳጥ ምእመን ኮንከ ዲበ ብዙኀ እስይመከ» አንተ ምእመን በትንሹ ታምነሃልና በብዙ እሾምሃለሁ ተብሎ በመጽሐፍ እንደተነገረው አባ ገ/መስቀል ተ/ሕይወት የተወለዱበትን አካባቢ ለቀው ከመጡ በኋላ በዚህ ደብር ውስጥ«ቅናት እንደ ገብሬ ጽሙድ እንደ በሬ » ሆነው የሰጡት መንፈሳዊ አገልግሎት በዘመኑ በነበሩት የቤተ ክርስቲያኑ አስተዳደር ሠራተኞች ለወደፊቱ የበለጠ የቤተ ክርስቲያን አገልግሎት እንደሚሰጡ በግብራቸው መታወቁ መስከረም ፳፰ ቀን ፲፱፻፷ ዓ/ም የቤተ ክርስቲያኑን ጠቅላላ ቁልፍ እንዲይዙ ተደረገ ፤ ቁልፉን ተረክበው በኃላፊነት አገልግሎት ከጀመሩበት ጊዜ አንሥቶ እስከ ዛሬ ድረስ በትጋት ፣ በንቃትና በታማኝነት



አባ ገ/መስቀል ተክለ ሕይወት እኒህ ነበሩ

ስለታዩ የዕቃ ቤቱን ቁልፍ ጨምረው እንዲይዙ ተደርጎ ሲሠሩ ቆይተዋል ። በማገልገል ላይ እንዳሉ አባ ገ/መስቀል ተ/ሕይወት የቅዳሴ ትምህርታቸው በቂ ከመሆኑም በላይ መምህር መሆን የሚያስችላቸው ሆኖ በመገኘቱ የቅስና ሥራ ቢሰጣቸው የበለጠ አገልግሎት እንደሚሰጡ ስለታመነባቸው በቁጥር ፩፻፴፰/ቂ/፰፮ ሚያዝያ ፳፫ ቀን ፲፱፻፷፯ ዓ/ም በተጻፈ ትዕዛዝ በቅስና ሥራ ላይ ተሰማርተው በጡረታ እስከ ተገለሉበት ጊዜ ድረስ በዚሁ ሥራ ቆይተዋል ። አባ ገ/መስቀል ተ/ሕይወት ባላቸው ሠርቶ የማሠራት የመግባባትና የሥራ ችሎታ በቅስና ሥራቸው ላይ ደርበው ለ፰ ዓመታት ያህል በሊቀ ዲቁና ሰርተዋል ።

አባ ገ/መስቀል ተ/ሕይወት ቤተ ክርስቲያንና ተከታዮችዋን ይወዳሉ ያፈቅራሉ በተለይ ይህ ደግሞ የሚታወቀው በአጥቢያችን ከሚገኙት ምእመናን ከ፴ሺህ እስከ ፭፻ሺህ የሚደርሱ የሚያፈቅሯቸው ንስሐ ልጆቻቸውን አስተምረው በቤተ ክርስቲያን መዝገብ እንዲመዘገቡ ማድረጋቸው ሲሆን ይህንኑም የአባ ገ/መስቀል ተ/ሕይወትም ከፍተኛ ጥረት የቤተ ክርስቲያኑ ሰበካ መንፈሳዊ አስተዳደር ጉባኤ ጽ/ቤት አይቶ ከማመስገኑም በላይ ለኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ልዩ ጽ/ቤት ይህ የተቀደሰ ሥራቸው ገልጾ በማሳወቅና የልዩ ጽ/ ቤትም የሥራ ፍሬአቸውንና መንፈሳዊ አባትነታቸውን ገምግሞ መጋቢት ፲፪ ቀን ፲፱፻፸፪ ዓ/ም መዓርገ ቁምስና ከብፁዕ አቡነ ሚካኤል እንዲቀበሉ አድርጓል ።

አባ ገ/መስቀል ተ/ሕይወት ሰው የሚወዳቸውና የሚያፈቅራቸው ከሥራ ባልደረቦቻቸው ጋር በፍቅር በሰላም የኖሩ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያንን እምነትና ሥርዓት ጠብቀው ያስጠበቁ ከልጅነት እስከ እውቀት ያገለገሉና የደከሙ ታላቅ አባት ሲሆኑ ከታኅሣሥ ፩ ቀን ፲፱፻፹ ዓ/ም ጀምሮ በዚሁ ለሞት ባበቃቸው በሽታ ምክንያት በጡረታ እንደ ተገለሉ በሽታው እየፀናባቸውና እየከበደባቸው መሄዱን የተረዱት የቅርብ ወዳጆቻቸውና ወንድማቸው አለቃ ኪሮስ ገ/ሥላሴ ወደ ቤታቸው ወስደው በክብርና በእንክብካቤ ይዘዋቸው ከቆዩ በኋላ ሰኔ ፲፱ ቀን ፲፱፻፹፪ ዓ/ም በተወለዱ በ፶፬ ዓመታቸው ከዚህ ዓለም በሞት ተለይተዋል ። ሥርዓተ ቀብራቸውም በአለቃ ኪሮስ ገ/ሥላሴ እና በመምህር ኃይለ ሥላሴ የደብሩ ሰባኪ ወንጌል እንዲሁም በደብሩ አስተዳዳሪ በመልአከ ሰብሐት ተስፋ መርሻ በደብሩ ካህናት በወዳጆቻቸው አማካይነት ከቀኑ በ፲ ሰዓት በመካነ ሰማዕት ቅዱስ ቂርቆስ ቤተ ክርስቲያን ተፈጽሞአል

እግዚአብሔር ነፍሳቸውን በወዳጆቹ በእነ አብርሃም እና በነ ይስሐቅ ፤ በእነ ያዕቆብ አጠገብ ያሳርፍ ።

ቤተ ሰቦቻቸው



# ሐኪሙ ለአብያተ ክርስቲያናት ርዳታ አደረጉ

ሐኪም መለሰ ማሞ በልዩ ልዩ አውራጃ ላሉት የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያናት ርዳታ አደረጉ ፤ ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ «ብልና ዝገት በሚያጠፉት ሌቦችም ቆፍረው በሚሠርቁት ዘንድ ለእናንተ በምድር ላይ መዝገብ አትሰብስቡ፣ ነገር ግን ብልም ዝገትም በማያጠፉት ፣ ሌቦችም ቆፍረው በማይሠርቁት ዘንድ ለእናንተ በሰማይ መዝገብ ሰብስቡ ፤ መዝገብህ ባለበት ልብህ ደግሞ በዚያ ይሆናልና» ባለው መሠረት ሐኪም መለሰ ማሞ ርዳታ የሚደርጉላቸው (ያደረጉላቸው) አብያተ ክርስቲያናት በርካታዎች ናቸው ።

ሐኪም መለሰ ርዳታ ካደረጉላቸው አብያተ ክርስቲያናት ጥቂቶቹን ብንጠቅስ ፣

፩/ በደቡብ ሸዋ አስተዳደር ክልል በሻሸመኔ ከተማ አካባቢ በመሠራት ላይ ላለው ኩየራ ቅዱስ ገብርኤል ቤተ ክርስቲያን በመጀመሪያ ብር ፪ሺ (ሁለት ሺህ ብር/

፪/ አሁንም ቤተ ክርስቲያኑ ተሠርቶ ሲያልቅ ለመስኮቶች መግገ ብር ፰ሺ (ስምንት ሺህ ብር) የሚገመት አሠርተው እንደሰጡ ገልጸዋል ።

፫/ በሻሸመኔ ከተማ በመሠራት ላይ ላለው ጻድቁ አቡነ ተክለ ሃይማኖት ቤተ ክርስቲያን ማሠሪያ ብር ፩ሺ(አንድ ሽህ ብር።)

፬/ በሻሸመኔ ከተማ ለሚገኘው ቅዱስ ሚካኤል ቤ/ክርስቲያን መንፈሳዊ አገልግሎት የሚውል ፮፻ (ስድስት መቶ ብር)

፭/ በልጆቻቸው ስም አሁንም ለሻሸመኔ ቅ/ሚካኤል ቤ/ክርስቲያን የተሰጠ ብር ፩፻ (አንድ መቶ ብር)

፮/ ለደብረ ሊባኖስ ገዳም ብር ፪፻ (ሁለት መቶ ብር)

፯/ ለአዲስ አበባ ጉለሌ ደብረ መዊዕ ሁለተኛ ካቴድራል አንድ የቀንድ ከብትና ብር ፭፻ (አምስት መቶ ብር)

፰/ በሌላ ጊዜም ለዚሁ ካቴድራል ብር ፶ (ሃምሳ ብር) እና ባለ ብር ፩፻ (አንድ መቶ ብር) ጃንጥላ ።

፱/ ለአሥመራ ደብረ ጽዮን ቅድስት ማርያም ቤ/ክርስቲያን ብር ፩፻ (አንድ መቶ ብር) ርዳታ ማድረጋቸውንና ለወደፊቱም ቤ/ክርስቲያንን ከመርዳት ወደ ኋላ እንደማይሉ ሐኪም መለሰ ማሞ አስረድተዋል ።

ሐኪም መለሰ ማሞ ስለ ኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤ/ክርስቲያን ያላቸውን ፍቅር የቱን ያህል እንደሆነ በሰፊው አዋይተውናል ክርስቲያናዊ ስሜታቸውን ሲገልጹም ምእመናኖቻችን በመጤና በማይረባ ተልከስካሽ እምነት ሲነጠቁ በማየቴ እጅግ እናደዳለሁ በጣምም አዝናለሁ ስለ ሃይማኖቱ ጠለቅ ያለ ትምህርት ባይኖረኝም በእንዲህ ዓይነቱ ስሕተት ለመውደቅ የሚፍገመገሙትን ወገኖች ሲያጋጥመኝ እገሥጻቸዋለሁ። እመክራቸዋለሁ የሆነ ሆኖ ግን የኔ ስጦታ ሰዎችን (በሽተኞችን) ማከም (መፈወስ) ነው ታድያ በዚህ አጋጣሚ ስለቤተክርስቲያናችንየምሰጠው አስተያየት ለእያንዳንዱ ስጦታ አለው ገበሬ በግብርናው ጸሐፊም ጸኖም ፤ አስተማሪም ካህንም ሐኪምም ፤ እያንዳንዱ በዕድሉ ሠርቶ አምርቶ ያድራል ካህን በካህንነቱ ቀድሶ አቍርቦ የንስሐ ልጆቹን አስተምሮ መክሮ በባእድ እምነት እንዳይወሰዱ ካልጠበቀ ሥራውን ረስቶአል ማለት ነው ስለዚህ ቀሳውስት መምህራንና ሰባክያን በርትተው ማስተማር እንደሚገባቸው በዚህም ከባድ አደራና ኃላፊነት እንዳለባቸው ይሰማኛልና ቤተክህነታችን እነዚህ ባለ አደራዎች እንዲያበረታታቸውና በከፍተኛ ደረጃ እንዲያስብበት አሳስባለሁ ።

እኔ በዚህ ዓለም ቢላ ሠርቼ በምኞትና በድሎት በተድላና በደስታ እኖራለሁ ብየ አላስብም የኔ ሀሳብና ምኞት ገንዘብ ባገኝ የፈረሰ አብያተ ክርስቲያናት እድሳት ሲደረግላቸው መርዳት ፣ ንዋየ ቅድሳት ሲያጡ መንፈሳዊ አገልግሎት ሲታጐል በተቻለኝ መጠን እንዲሟላ ጥረት ማድረግ ከፍተኛ ስሜቴና ፍላጎቴ ነው ። አሁንም ከዚሁ ምኞቴ አልወጣም እግዚአብር አምላክ ምኞቴን ያስፈጽመኝ እንጂ እና አሁንም ምን ጊዜም ቢሆን መልሸ መላልሸ በቤተ ክርስቲያናችን በኩል ከፍተኛ ቅስቀሳ እንዲኖር ነው የማሳስበው ፣ እናንተም ቢሆን በጋዜጦቹና በመጽሔቶቹ ምእመናንን በትምህርት መቀስቀስ ማነጽና ማነቃቃት ይገባችኋል እላለሁ ።

ሌላው እግረ መንገዴን ለማሳሰብ የምፈልገው ሰዎች እኔን «ዶክተር» ይሉኛል እኔ ዶክተር አይደለሁም ይህ በሽተኞች የምፈውስበት መድኃኒትም እኔ ተፈላስፌ ፣ ወይም በትምህርት ዓለም ውስጥ ገብቼ ይህ ይሆናል ያ አይሆንም ብዬ በዕውቀቴ ቀምሜ ያዘጋጀሁት ሳይሆን ሚካኤልና ገብርኤል ይህ ለዚህ በሽታ ያ ለዚህ ሕመም መድኃኒት ነውና በዚህ መልክ ሕመምተኞችን ፈውስበት ብለው ነው የሰጡኝ እና ሰዎች እኔን ዶክተር ብለው የሚጠሩኝ ስሕተት ስለ ሆነ ባይሆን እንኳ ሐኪም መለሰ ብለው ቢጠሩኝ የተመረጠ መሆኑን አሳስቡልኝ ብለዋል ።

ሐኪም መለሰ ማሞ በገንዘባቸው በሀሳባቸውም ሆነ ባላቸው ዕውቀት ቤ/ክርስቲያንን ከመርዳት ወደኋላ እንደማይሉ ከፍ ብለን ጠቅሰናል እንደዚሁም ሁሉ ችግረ



www.ethiopianorthodox.org

ኛ የሆነ ኢትዮጵያዊም ምንም ምን እንደሌለው ካረጋገጡ በኋላ ሙሉ ርዳታ እያደረጉ ከቤታቸው ውም እያስቀመጡ አክመው ያዳኑአቸው ብዙዎች ናቸው ካሁን በፊት ባለፉት እትሞቻችን ስለ ዚሁ ጉዳይ በሰፊው መግለጻችን ይታወሳል ።

አሁንም ቢሆን ሐኪም መለሰ ማሞ የተጣለባቸውን አደራ ለመወጣት በነፃ እያከሙ ከሕመማቸው የፈወሱአቸው (የሚፈውሱአቸው) ብዙዎች ናቸው ። ከነዚህ መካከል እነመምሬ ተሰማ መኩሪያ ይገኙባቸዋል ። በእቃቂ በሰቃ የመድኃኔ ዓለም ቤ/ክርስቲያን አገልጋይ ካህን የነበሩት መምሬ ተሰማ መኩሪያበሐኪምመለሰ ቤት አግኝተን አነጋግረናቸዋል ። መምሬ ተሰማ መኩሪያ ከደረሰባቸው ስቃይ ከፍለው ከነገሩን ጥቂቶቹ ከዚህ በታች ተዘግቦአል ። እኔ የመጣሁ ከክፍለ ሀገር ነበር በእቃቂ በሰቃ መድኃኔ ዓለም ቤተ ክርስቲያን አገልጋይ ካህን ሆኜ ገባሁ በመድኃኒት ያሽመደመደኝን ካህን ጓደኛ አደረግሁት አባቱም የጡት አባቴ ሆነው እንደውሉድና ወላዲ አብረን ኖርን አብረን በፍቅር ቤ/ክርስቲያን (ቤተ እግዚአብሔርን) ስናገለግል ብዙ ዘመን ቆየን በመካከላችን ቂም በቀል የለም እንዲያውም እኔ አባቱ እንዳባቴ እርሱ እንደ ወንድሜ አድርጌ ነበር የምኖረው ታድያ የዛሬ ፲፰ ዓመት ገደማ ከዚሁ ጓደኛዬ ጋር አብረን ቀድሰን ወጣን ፥ መከፈልት በልተን ጠላ ስንጠጣ ቆየን የምጠጣበት ብርጭቆውእጉድየወደ ውጭ ወጣሁና ተመልሼ ስገባ ብርጭቆው ሞልቶ አገኘሁት ጥርጣሬ የለኝም፥ሰው ከሰው ጋር ቂም በቀል ሲኖረው ሊጠራጥር ይችላል እኔ ግን ስላልጠረጠርሁ ጠላትም አለኝ ብዬ ስላላሰብሁ ብርጭቆው አነሣሁና ጠጣሁት ፥ ወዲያውኑ አስታውኩኝ ከሆዴ ሲወጣ ልክ የተቀጠቀጠ መድኃኒት እንደጠጣሁ ሸተተኝ ሌላ ጣዕምም ተሰማኝ መድኃኒት መሆኑንም ተረዳሁ ፥ ነገር ግን ባያስታውከኝ ኖሮ ወዲያውኑ እሞት ነበር ።

ይሁን እንጂ መድኃኒቱ ኃይለኛ በመሆኑ ወዲያውኑ በሽታ ተከለብኝ ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ያልደረስሁበት ፀበል የለም ያልሄድሁበት ሐኪም ቤት አይገኝም ሆስፒታሎች እንደመኖሪያ ቤቴ ናቸው የመዳን ተስፋ ግን አላገኘሁም ታድያ ተስፋ ቆርጬ እቤቴ ዘቅምጬ ሳለሁ ባለፈው ክረምት ወራትውስጥ አንድ የንስሐ ልጄ መጥቶ ወደ ሐኪም መለሰ ኼደህ መታከም አለብህ የኔ ልጅ ብዙ ዘመን በበሽታ ስትሰቃይ ነበረች ወደ ሐኪም መለሰ ወስጄ እንድትታከም ስላደረግኋት እነሆ ድና ሙሉ ጤና አግኝታለች ስለዚህ አሁን ተነሥ አብረን እንሂድ ብሎ ይዞኝ መጣ አሁን ሐኪም መለሰ ዘንድ መታከም ከጀመርሁበት ጊዜ ጀምሮ እግዚአብሔር ይክበር ይመስገን በጣም ደህና ነኝ ሕክምና ስጀምር ሐኪም መለሰ ገንዘብ እኮ የለኝም ብላቸው ገንዘብ እንደሌለዎት እኔ አውቃለሁ እዚሁ ከኔ ጋር ሆነው ዝም ብለው ይታከሙ አሉኝ ፥ እነሆ በነፃ እየታከምሁ ነው ያለሁ ከዚያ በፊት በሽታው በጎኔ ቀዶ የሚወጣ ይመስለኝ ነበር ባሁኑ ጊዜ ግን ምንም አይሰማኝም በብዙ ገንዘብ የሚገመት መድኃኒት ይሰጡኛል ፥ መኖሪያየም ምግቤም ከእሳቸው ነው ከመጣሁ አራት ወሬ ነው እንጀራ ቆርሼ ለመብላት አልችልም ነበር ራሴ ተነሥቼ ለመንቀሳቀስ ፥ ለመቀመጥም አይሆንልኝም ነበር ። እንጀራም ምናልባት በሦስት ቀን ውስጥ የእጄን መዳፍ የምታክል ብበላ እንኳ ሥቃዩ ያን ያክል ነበር ልብስ ለመልበስ ፈጽሞ ሰውነቴ አይሠራልኝም ነበር አሁን ግን ራሴ ነው የምለብሰው ጅማቶቼ ፈጽመው አይሠሩም አይንቀሳቀሱም ነበር አሁን ግን እየተፍታቱ ናቸው ያለፉት ፲፰ ዓመታት እንደ ኢዮብ አየረገምኋቸው ነው ከዘመናቱም ጨምሬ አልቈጥራቸውም አሁን ግን እግዚአብሔር ይመስገን እንጂ በሐኪም መለሰ ማሞ አድር ስለፈወሰኝ እጅግ በ[illegible] አመሰግነዋለሁ ። ሐኪም [illegible]ም ዕድሜና ጤና እንዲሰጠው እጸልይለታለሁ

ከመምሬ ተሰማ መኩሪያ ሌላ ወጣት ኃይሉ ግደይ ለአንድ ወር ያህል ዓይኑ ተከልሎ ከኖረ በኋላ ባሁኑ ጊዜ በሐኪም መለሰ ማሞ ታክሞ በተጣራ ሁኔታ ዓይኑ በርቶለት ሙሉ በሙሉ ለማየት በቅቶአል ።

እንዲሁም በከፍተኛ ፳፬ ቀበሌ ፲፫ የቤት ቁጥር ፩፻፳፱፹፫ ነዋሪ የሆኑ ወ/ሮ ሉሲት በዛብህ ዓይናቸው በሞራ ታውሮ ፥ ከአንገት በላይ የራስ ሕመም አድሮባቸው ሲሰቃዩ ከቆዩ በኋላና በሐኪምም ተስፋ አጥተው በችግር ላይ እንዳሉ ፥ እንዲያውም ዶክተሮች ውጭ አገር ኼደው ካልታከሙ ተስፋ የለ ዎትም ተብለው ደብዳቤ ተጽፎላቸው በመዘጋጀት ላይ እንዳሉ የሐኪም መለሰን ዝና ሰምተው ከእርሳቸው ዘንድ በመታከማቸው ለ፲፰ ዓመታት ሲያስቃያቸው የቆየው በሽታ ተነቅሎ ጠፍቶላቸዋል በሞራ ተሸፍኖ ዓይናቸው ለማየት ከልክሎአቸው የነበረውንም ፈጽሞ ጠፍቶላቸው እየተመሩ መጥተው አሁን ፍጹም ብርሃን ተጎናጽፈው እያዩ ያለመሪ ወደ ቤታቸው መመለሳቸውንም በቃላቸው ምስክርነት አረጋግጠዋል ።

በኢሉባቦር ክፍለ ሀገር በገባ አውራጃ ቁጺ ከተማ ቀበሌ ዜሮ ፩ የቤት ቁጥር ፪፻፴፮ ነዋሪ የሆነ ወጣት አበሽ ንጉሤ በሐኪም መለሰ ማሞ ታክሞ ከአዙሪት በሽታ ፈጽሞ ለመዳን በቅቶአል ። በወሎ ክፍለ ሀገር እንደጮ በር ነዋሪ የሆነች ወ/ት ዘነበች እንድሪስ ፲ ዓመት ሙሉ ያሰቃያት የእንቅርት በሽታ ተነቅሎ ጠፍቶላታል ። የአሥር አለቃ ገብሩ አብርሃ በኪንታሮት በሽታ ለሁለት ዓመት ሲሰቃዩ ከቆዩ በኋላ በሃያ ቀን ውስጥ ከሐኪም መለሰ ማሞ ታክመው እንዳልነበረ ሆኖ ጠፍቶላቸዋል ። የምስክርነት ቃላቸውንም በፊርማቸው አረጋግጠዋል ።



በደቡብ ሸዋ አስተዳደር ክልል ነዋሪ የሆነች ወ/ት ሕልፍቴ መዝሚል ለሰባት ዓመታት ሙሉ የበላችው እንጀራ ፥ የጠጣችው ውኃ ከሆድዋ አልውል (አልረጋ) ብሎ ሲያሰቃያት የነበረው የኩላሊትና የጉበት በሽታ ከሐኪም መለሰ ዘንድ መጥቼ ለሃያ ቀናት የተሰጠኝ (የታዘዘልኝ) መድኃኒት እንኳ ሳልጨርስ በ፲፰ ቀናት ውስጥ ከሁለቱ በሽታዎች ልላቀቅና ነፃ ልሆን ችያለሁ ስትል በመዳንዋ የተሰማትን ደስታ ከመግለጽዋም በላይ የምስክርነት ቃልዋንም በፊርማዋ አረጋግጣ ወደቤቷ መመለስዋን በ ዘገበችው ዜና ለሚወቅ ተችሎአል።

ሊ/ትጉሃን ገ/ክርስቶስ ኃ/ማርያም

# የምሥራቅ ሐዋርያ

ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሦስት ዓመት ከሦስት ወር ባስተማረበት ወቅት ሐዋርያት ብሎ የሚጠራቸው ደቀ መዛሙርቱ «ሑሩ ወመሀሩ ውስተ ኵሉ አጽናፈ ዓለም»ሲል ሥልጣን እንደሰጣቸው ወንጌል ይነግረናል በዚሁ ቃል መሠረት ይህን ዓለም በምሥራቅ በምዕራብ በሰሜን በደቡብ ተከፋፍለው የተጣለባቸውን አደራ እስከ ሕቅታ ድረስ ተወጥተዋል ፤ በየጊዜው በእግራቸው እየተተኩ የሚሠሩ ሐዋርያትም እንደዚሁ ፤ ማስተማራቸውን ካለማቋረጣቸው የተነሣ እነሆ የወንጌል ቃል ዳር እስከ ዳር ሲነገር ይኖራል ።

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ባሁኑ ጊዜ ብዙ መምህራነ ወንጌል (ሐዋርያት) አሏት በሀገር ውስጥም ሆነ በውጭ ሀገር ብዙ አብያተ ክርስቲያናት ተክላለች በነዚህም ሥፍራዎች ሊቃነ ጳጳሳትና ኤጲስ ቆጶሳት ሰባክያነ ወንጌልና ካህናት አሉአቸው በውጭ ከሚያገለግሉ ሰባክያነ ወንጌል አንዱ ማዕዶት ለሚያቀርብላቸው ቃለ መጠይቅ የሚሰጡት መልስ እንከታተላለን በመሠረቱ እኚህ ሐዋርያ መምህር ተወልደ መድኅን ገ/ሥላሴ የጅቡቲ ምሥራቀ ፀሐይ ቅ/ገብርኤል ቤ/ክርስቲያን ሰበኬ ወንጌል የነበሩ ናቸው ።

ማዕዶት መምህር ተወልደ መድኅን ገ/ሥላሴ በጅቡቲ ምሥራቀ ፀሐይ ቅ/ገብርኤል ቤ/ክርስቲያን ሰባኬ ወንጌል ሆነው የኼዱት መቸ ነው? በዚያስ ለስንት ወራት ያህል ሠሩ ቢያብራሩልን?

መልስ በህዳር ፰ ቀን ፲፱፻፹፩ እስከ ግንቦት ፰ ቀን ፲፱፻፹፩ ዓ/ም ድረስ ነው በምሥራቀ ፀሐይ ቅ/ ገብርኤል ቤተ ክርስቲያን ጅቡቲ የሠራሁ ፤

ማዕዶት ስለቤተ ክርስቲያኑ የአስተዳደር ሁኔታና የሥራ ተሳትፎ ከመግለጽዎ በፊት ስለጅቡቲ ሪፓብሊክ መልክአምድር አቀማመጥና ስለአስተዳደር ሁኔታዋ ስለሕዝቦቿ አኗኗር ባሕልና ልምድ እንዲሁም የእምነት ጽናት እና ቋንቋ ከብዙ በጥቂቱ ቢነግሩን ?

መልስ የጂቡቲ ሪፓብሊክ የምትገኘው በኢትዮጵያ ምሥራቅ በቀይ ባሕርና በኤደን ባሕረ ሰላጤ መካከል ሲሆን ከተማዋ እ-ኤ-አ-ከ፰፻፹፯—፲፱፻፺/ም እንደተቆረቆረች ይገመታል ሲሉ አንዳንድ የታሪክ መረጃዎች ይገልጻሉ ። የመሬትዋ ስፋት ፳.፩፻፺፰ እስኩዬር ማይልስ ነው ። የሚያዋስናትም በሰሜንና በምዕራብ ከኢትዮጵያ በደቡብ ከሶማሊያ ፥ በምሥራቅ ከቀይ ባሕር ጠረፍ ናቸው ። ጠቅላላ የሕዝቧ ብዛት ከሦሥት መቶ ሃምሣ ሺህ በላይ ሲሆን አንድ መቶ ሰማንያ ሺህ ያህሉ በከተማዋ ነዋሪዎች ናቸው የአየሯ ሁኔታ ሙቀቱ እጅግ ከፍተኛ በመሆኑ አካባቢውን በረሃ ነት ያይለዋል ። የሙቀቱ ኃይል የሚበረታው ከሚያዝያ ወር አጋማሽ ጀምሮ እስከ መስከረም አጋማሽ በመሆኑ ከግንቦት እስከ መስከረም ባሉት የሙቀት መሸጋገሪያ ወራት በኋላ ነፋሻማና ቀዝቃዛ ይሆናል ።

ማዕዶት ለመሆኑ በሀገሩ ላይ ዝናም ይዘንማል ?

መልስ ዝናም ዘወትር ባይሆንም አልፎ አልፎ ይጥላል ። በከተማዋ ነዋሪዎችና ጥረት በመሥሪያ ቤቶችና በግለሰቦች መኖሪያ ግቢ ዛፎች ተተክለው ከተማዋ በአረንጓዴ ተክሎች ልምላሜ ተለውጣለች ፤ በግብርናውም በኩል የአየሩን ጠባይ ሊቋቋሙ የሚችሉ እየተመረጡ ለተጠቃሚው ሕዝብ ሲቀርቡ ተመልክቻለሁ ለመጥቀስም ያህል በቆሎ ፥ ማሽላ ፥ በርበሬ ፤ ቲማቲም ፤ እየተመረቱ ናቸው ይህም ሁሉ በፊት እንዳልነበረ ነዋሪዎቹ ይናገራሉ ።

ማዕዶት ለመሆኑ በሀገሪቱ የሚኖሩ ብሔረ ሰዎች ምን ምን ናቸው ዘራቸውስ ? ብለን

በሀገሪቱ ያሉት ቋንቋቸው ሃይማኖታቸው አክለው ቢያስረዱን ስለመገናኛውም ቢያብራሩልን

መልስ በሀገሪቱ የሚኖሩ ብሔረ ሰቦች ሶማሌ ፤ኢትዮጵያ ፤ አፋርና ኢሣ ፥ከየመን የፈለሱ አረቦች ናቸው ። የሚነገሩ ቋንቋዎችም ፈረንሳይኛ ፥ አረብኛ ፥ ሱማሊኛ ፥ እና በተጨማሪ አማርኛና እንግሊዝኛም በከፊል ይናገራሉ በሃይማኖት በኩል ደግሞ የእስልምና እምነት ተከታዮች ስለሚበዙ መስጊዶች በብዛት ይታያሉ የክርስትና እምነት ተከታዮችም ስለ አሉ የመስጊዱን ያህል ባይሆንም ቤተ ክርስቲያን አለ ።

በጅቡቲ ከተማ የሚገኙ አብያተ ክርስቲያናት የኢ-ኦ-ተ-ቤተ የካቶሊክ ፥ የግሪክ ኦርቶዶክስ ቤተ



www.ethiopianorthodox.org

ክርስቲያንና የፕሮቴስታንት ጸሎት ቤት ናቸው በመገናኛ በኩል ከኢትዮጵያ ጋር የምትገናኝበት የባቡር ሐዲድ መስመርና የመጓጓዣ መንገድ ሲናሯት ከዓለም ሕዝብ ጋር የሚያገናኛትም አንድ የአይሮፕላን ማቢያ እላት በጅቡቲ የሚኖሩ ኢትዮጵያውያንም በልዩ ልዩ የሥራ መስኮች በተለያዩ መሥሪያ ቤቶች ድርጅቶች በግል እየሠሩ የሚተዳደሩ ጠንካራ ዜጎች አሉ ።

ማዕዶት ለመሆን በጅቡቲ ቤተ ክርስቲያናችን በኩል ምን ምን የተሠራ (የተከናወነ) ሥራ አለ?

መልስ ስለጅቡቲ ሪፐብሊክ መልክአ ምድርና ስለሕዝቧ አኗኗር ይህን ያህል ከጠቀስኩ «ያየነውን እንመሰክራለን» የሰማነውን እንናገራለን ነውና ብፁዕ አቡነ ኤልያስ በምድረ ጅቡቲ ምሥራቀ ፀሐይ ቅ/ገብርኤል ቤተ ክርስቲያን የፈጸሟቸውን መልካም እና የተቀደሱ መንፈሳዊ ሥራዎች አጠር ባለ መልኩ ለመግለጽ እሞክራለሁ ።

እኚህ አባት ለቤተ ክርስቲያናችን አንድ ትልቅ አባት ሲሆኑ እንደ አንድ ሠራተኛ መኪና ሳይሹ ፣ የቤ/ክርስቲያኑን የሕንጻ ሥራ ለማስፈጸም ብፀሐዩ ቃጠሎ ፣ በሙቀት ፣ መብርታት ሳይበገሩ ከአንድ መሥሪያ ቤት ወደአንዱ መሥሪያ ቤት ፤ ከአንድ ድርጅት ወደሌላው ድርጅት በመሯሯጥ ለሥራው መሳካት ያደረጓቸውን የትጋት ሥራዎች ለመዘርዘር ቃላት ያጥረኛል ። የሆኖ ሆኖ ሳልጠቅሳቸው ለማለፍ የማልፈልገው አንዳንድ ነጥቦች መካከል የደብሩን የሕንጻ ሥራ ካጠናቀቁ በኋላ «ማኅደር ያለኃዳሪ ፣ ኃዳሪ ያለማኅደር» ለመኖር የማይችል መሆኑን ተገንዝበው በዘመናዊ አቅድ የካህናት መኖሪያ ከነሙሉ ድርጅቱ አቋቁመው አገልግሎት እንዲሰጥ ከማድረጋቸው በላይ ካህናቱ የሚተዳደሩበት በሥርዓት ፣ ገዳም ሕግ ከቤ/ክርስቲያን ገቢወጪ በማድረግ ካህናቱ በአንድነት እንዲመገቡ በማለት ምግብ አዘጋጅና ቤት አጽጂ ሠራተኛ በመቅጠር የካህናቱ ኑሮ በመልካም ሕይወት እንዲጠበቅ አመቺ መንገድ ፈጥረዋል ። በዚህ አኳኋን የምእመናኑም መንፈሳዊ ሕይወት እንዲጠናከር በየጊዜው ትምህርት እንዲሰጥ ሰባክያነ ወንጌል እየጋበዙ በቅዱስ ፓትርያርክ መልካም ፈቃድ እየወሰዱ የክርስቶስ ቅዱስ ቃል በምልአትና በስፋት እንዲዳረስ ያሳዩትና የፈጸሙት ተጋድሎ እጅግ የሚያስመሰግናቸው ነው ብል ማጋነን አይሆንብኝም ።

በመሆኑም እንዲህ ያለው አባት መንፈሳዊ ተጋድሎና የተቀደሰ አገልግሎት የመልካም አርአያ ቅርስነት ከትውልዱ አእምሮ ሊፋቅ የማይችል የታሪክ መዘክር መሆኑ ሊዘነጋ አይገባም እላለሁ

ማዕዶት መምህር ተወልደ መድኅን ወንጌል ለሕዝብ ማን ይስበክ? እንዴትስ ይሰበክ? ብለው ያምናሉ?

መልስ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በዚህ ዓለም እየተመላለሰ ያስተምር በነበረበት ወቅት ቦታና ጊዜ ሳይመርጥ ለድሆችና ለባለጠጎች ለወንዶችና ለሴቶች ለተማሩና ላልተማሩ ሁሉ አመቺ በሆነ መንገድ ሕይወታቸውን የሚመሩበትን ፣ የጽድቅ በር የሚያገኙበትን የፍቅር ሕግ የሚጸናበትን ዘዴ ያስተምር እንደነበረ መጽሐፍ ቅዱስ ባነበብን ቍጥር ይታወሰናል ። በኋላም ሐዋርያትን ሾሞ አልጫ የነበረውን ዓለም በትምህርታቸው እንዲያጣፍጡት ሥልጣን ሰጥቷቸው ነበር ። እነርሱም በዓለም ተዘዋውረው በማስተማራቸው የክርስትና እምነት እንዲስፋፋ የወንጌል ፋና እንዲበራ የተቀደሱ ትሩፋት እንዲሠሩ እና ብዙዎች የክርስቶስ ተከታዮች እንዲሆኑ የወንጌልን ቃል ሰብከው በተቀደሰ ሰማዕትነት አልፈው የተዘጋጁላቸውን የጽድቅ አክሊል እንደተጎናጸፉ ከገድለ ሐዋርያት መረዳት ይቻላል ።

ዛሬም ቤተ ክርስቲያን አደራ የጣለችባቸው የቤተ ክርስቲያን ልጆች ሁሉ የእነርሱን ምሳሌ ተከትለው በየዘመኑ የተነሡ ገወንጌል መምህራን ቅዱስ ቃሉ ለዓለም ሕዝብ እንዲዳረስ ብርዱ ፀሐዩ ሙቀቱ ሐሩሩ [illegible] ቁልቁለቱ ሳያግዳቸው (ሳይበግራቸው) ወንዝ ተሻግረው በረሀ አቋርጠው በመጓዝ የክርስቶስን ቅዱስ ቃል ይመሰክራሉ ። መሆንም ያለበት ይህነው

ማዕዶት እርስዎ ወደ ጅቡቲ ሰባኬ ወንጌል ሆነውእንዲሄዱ ራስዎ ፈልገውወይም መርጠውየሄዱትነው ወይስ በቤተ ክርስቲያን ምርጫነው?

መልስ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ደቀ መዛሙርቱን ሒዱና አስተምሩ ካለ በኋላ የታዘዛችሁትን ከሠራችሁ በኋላ ግን ሥራፈቶች ደካሞች አገልጋዮች ነን በሉ (ሉቃ ፲፯ ፣ ፱—፲፩) ብሎ በነገራቸው መሠረት በብፁዕ አቡነ ኤልያስ በጂቡቲ የኢትዮጵያ ሊቀ ጳጳስ አሳሳቢነት በብፁዕ ወቅዱስ አቡነ መርቆሬዎስ መልካም ፈቃድ ወደ ጅቡቲ ምሥራቀ ፀሐይ ቅ/ገብርኤል ቤ/ ክርስቲያን ኼጄ እንዳስተምር ትእዛዝ ደረሰኝ ።

በትእዛዙ መሠረት ኅዳር ፰ ቀን ፲፱፻፹፩ ዓ/ም ለጉዞ ተነሣሁ እንደሚታወቀው ሁሉ ጽድቅ በጭንቅ ነውና ጅቡቲ ከመድረሴ በፊት ደወሌ ከምትባለው የጂቡቲ ደሴት ወደብ እንደደረስኩ የኬላው ፈታሾች ፓስፖርትህ የጂቡቲ በኢት አምባሳደር ቢዛ ስላልተደረገበት ጉዞውን መቀጠል አትችልም ብለው ለ፵፰ ሰዓታት ያህል በቁጥጥር ሥር ከቆየሁ በኋላ ወደ ኢትዮጵያ ተመልሼ ማስተካከል የምችል መሆኑ ስለተነገረኝ በድሬደዋ በሚገኘው የጂቡቲ ቆንሲል አመልክቼ የአንድ ወር ቢዛ ተሰጥቶኝ ጉዞውን ተያያዝኩት ይሁንና በዚያ የጭንቅ ጊዜ በአእምሮዬ ይመላለስ የነበረው የሐዋርያው ፣ ቃል «በመከራችን ሁሉ እንመካለን» የሚል ሲሆን በልቤ እንዴት ያለግሩም ቃል እያልኩኝ በደስታ ስሜት እንደተሞላሁ መንገዱ ሳይታወቀኝ አልቆ ጂቡቲ ገባሁ ።

የተጠራሁበትን ዓላማ ከግብ ለማድረስወደ ተመደ በኩበት የጂቡቲ ምሥራቀ ፀሐይ ቅ/ገብርኤል ቤ/ ክርስቲያንአመራሁ እንደደረስኩም የደብሩ አስተዳዳሪ መንፈሳዊ ባሕርይ በተላበሰ ፈገግታ ተቀብለው ለደብሩ ካህናት ከተመደበው መኖሪያ ማረፊያ ሰጡኝ ስለደብሩ ካህናትና ምእመናን ትምህርት አቀባበል ገለጻ እንዲያገርጉልኝ ጠይቂአቸው ሲመልሱ የጂቡቲ ክርስቲያን ምንም እንኳ በተለያየ ምክንያት ከሀገሩ ቢወጣም ሃይማኖቱን ወዳድ ሥርዓቱን አክባሪ እምነቱን ጠባቂ ሀገሩን አፍቃሪ መሆኑን ጥሩ አድርገው ስላስረዱኝ አመስግኜ በወሰድኳቸው ጥናቶች ትምህርት የሚሰጥበትን ፕሮግራም አቀድኩ ።



መምህር ተ/መድኅን ገብረ ሥላሴ

እንደተባለውም በጂቡቲ የሚኖረው የኢትዮጵያ ምእመን እምነቱን ጠብቆ የሚኖር የእንግዳ አቀባበል ባሕሉንም ያልረሳ በመሆኑ ብዙም ጊዜ ሳይወስድብኝ በቀላሉ ተግባብቼ ለማስተማር ጀመርኩ ይሁን እንጂ የሰበካው ጉባኤ ተዳክሞ ስለነበር መሟላት የሚገባቸውን አንዳንድ ነገሮች ተሟልተው ባለማየቴ የተዳከመውን የሰበካ ጉባኤ በማጠናከር እና በመመካከር ከኅዳር ፲፩ ቀን ፲፱፻፹፩ ዓ/ም ጀምሮ የሚከተሉትን መርሐ ግብሮች አውጥተን ሕዝቡ እንዲጠቀምባቸው ተደርጓል ።

፩ኛ/ የጠዋት ጸሎት ማለት ጸሎተ ኪዳን እንዲደረስ ዕለቱን በማስመልከት በወንጌል መምህራን ትምህርት እንዲሰጥ ።

፪ኛ/ የሠርክ ጸሎት (በ፲፩ሰዓት) ከአሁን ቀደም ባለመኖሩ አሁን ግን ዘወትር እንዲያረግና በተነበበው ወንጌል ስብከት እንዲጠናናከር ።

፫ኛ/ የወጣቶች ሰንበት ት/ቤት ተቋቁሞ ወጣቱ በመዝሙርና በቅዱስ ቃሉ ራሱን ለመንፈሳዊ አርበኝነት እንዲያዘጋጅ በማድረግ ፤

፬ኛ/ በከብረ በዓል ዕለት ወጣቶች ዩኒፎርም ለብሰው በዓሉን የሚመለከት መዝሙር እንዲዘምሩና ለበዓሉ ድምቀትም ዓውደ ምሕረቱን እየዞሩ ታቦት እንዲያጅቡ በማስተማርና በሥራ እንዲውል በማድረግ ።

፭ኛ/ ቅዱስ ቃሉን ለመስማት የሚሰበሰቡ ምእመናን የሚያርፉበት የተወሰነ ቦታ ስላልነበረ ይህን በማየት ለምእመናን የሚጠቅም ከፀሐይና ከዝናብ የሚከላከል መጠለያ ለማሠራት ይቻል ዘንድ ከእያንዳንዱ ምእመን መቶ ሃምሳ ሺህ የጂቡቲ ፍራንክ በመሰብሰብ በሥራ ላይ እንዲውል ሆኗል ።

፮ኛ/ የታመሙ ወገኖች ከደዌያቸው ስቃይ የሚገላገሉበትን መንገድ በመሻት የጥምቀት ጠበል በማዘጋጀት ብዙ ኢትዮጵያውያን ወገኖቻችን ከደዌያቸው ተፈውሰዋል ።

፯ኛ/ የታመሙ ሁሉ ከደዌያቸው ስቃይ የሚገላገሉበትን መንገድ በመሻት የጥምቀት ጠበል በማዘጋጀት ብዙ ኢትዮጵያውያን ወገኖቻችን ከጌታ የሕይወት ምግብ ርቀው ከቆዩ በኋላ በተሰጠው ትምህርት በመማረክ ሕይወታቸውን በንስሐ አጥበው የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስን ቅዱስ ሥጋና ክቡር ደም የተቀበሉ ብዙዎች ናቸው ።

እንግዲህ ከላይ የጠቀስናቸው መርሐ ግብሮች ካሁን በፊት ያልነበሩ ስለሆነ አሁን ለቤተ ክርስቲያኑ እድገት ከፍተኛ መሻሻልን ለምእመናኑ የእምነት ጽናት እና መንፈሳዊ ጥንካሬን እንደሚያስገኝ እንተማመናለን ።

ስለዚህም ይህንን የመሰለውን መልካም ጉዞ መነሻ በማድረግ ለኅብረተሰቡ ዓላማ መሆን ያስፈልጋል ። በራሳችን ኃይል ይህንን ታላቅ ጉዞ መጓዝ እንደማንችል ግን መገንዘብ ይኖርብናል ።በሐዋርያት ዘመን የነበሩ ክርስቲያኖች ሕይወታቸውን በሙንፈስ ፣ ቅዱስ ቁጥጥር ስር ስላዋሉ የክርስቶስ ፍቅር አስገድዷቸው ለዓለም የሰላምን ወንጌል ሰበኩ ፡ እግዚአብሔርም ምርጥ ዕቃ አድርጎ ተጠቀመባቸው ። ባህርያቸው ተለወጠ ፤ በዚያን ጊዜ የነበሩ ሰዎች መንፈስ ቅዱስ ሕይወታቸውን እንዲቈጣጠረው ስለፈቀዱ ፍርሃትን ከልባቸው የሚያጠፋ ኃይል ተቀበሉ ።

ይህ አምላካዊ ኃይል ለእኛም ጭምር እንጂ ለእነርሱ ብቻ የተሰጠ ባለመሆኑ ከኃጢአት ተለይተን በጎ ምግባር በመሥራት ቃሉን በመስበክ ሕይወታችን ፍሬያማ እንድናደርገው ይገባል

ማዕዶት መጽሔት እንደመምህር ተወልደ መድኅን ገ/ሥላሴ የመሳሰሉት ሁሉ የወንጌል ባለ አደራዎች ስለሆኑ ምእመናንን ለማነጽ ፣ ለመጠበቅና ከተኩላ ነጣቂ ለመጠንቀቅ ይችሉ ዘንድ ምክሩን ይለግሳል መምህር ተወልደ መድኅን ገ/ሥላሴም በኼዱበት ሁሉ በወንጌል አገልግሎትዎ ይበርቱ ይጠንክሩ በጊዜውም ያለ ጊዜው ም የጌታ ቃል በየሥፍራው ይመስክሩ ይላል ።



www.ethiopianorthodox.org